# ለዕብራውያን የተጻፈ መልእክት

## መግቢያ

ይህን መልእክት የጻፈው ማን መሆኑን በውል ለይቶ ለመናገር አስቸጋሪ ሆኖ ተገኝቷል። መልእክቱ የተጻፈው ከ70 ዓ.ም. ጥቂት ቀደም ብሎ እንደሆነ ታውቋል። 'ዕብራውያን' የአይሁድ ሌላው መታወቂያ ስማቸው ነው። መልእክቱ የተጻፈው ለአይሁድ ክርስቲያኖች ሲሆን፥ መሠረተ አሳቡ በክርስቶስ አማካይነት እግዚአብሔር አዲስ ቃል ኪዳን ያቆመ መሆኑን ያመለክታል። አዲሱ ቃል ኪዳን እግዚአብሔር መጀመሪያ በሙሴ አማካይነት ከሕዝቡ ከእሥራኤል ጋር ካደረገው አሮጌ ኪዳን እጅግ የላቀና እጅግ የተሻለ መሆኑ በዚህ መልእክት ውስጥ በሚገባ ተገልጧል። በዚህ በአዲሱ ቃል ኪዳን አማካይነትም ወደ እግዚአብሔር ዘንድ የሚያደርሰን አዲስና ሕያው የሆነ መንገድ መከፈቱን መልእክቱ ያስረዳል። ስለ አዲሱ ቃል ኪዳን የሚያበሥረውን የምሥራች ቃል ለሚንቁና ለሚያቃልሉ ሁሉ፥አምስት እጅግ ከባድ ማስጠንቀቂያዎች በዚሁ መልእክት ውስጥ ተጽፈው ይገኛሉ።

---

## ምዕራፍ 1

1 እግዚአብሔር ባለፉት ዘመናት፥በተለ
ያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ መንገድ፥በራዕይና
በሕልም እየተገለጠ፥በነቢያት አማካይነት
ለአባቶቻችን ተናግሯቸው ነበር።
2 በዚህ ባለንበት በመጨረሻው ዘመን
ግን፥ሁሉን ወራሽ ባደረገውና ዓለማትን በእ
ርሱ አማካይነት በፈጠረው በልጁ ተናግሮ
ናል።
3 ልጁም የእግዚአብሔር የክብሩ ነጸብራ
ቅና የአምላካዊ ባሕርዩ አምሳያ ነው።
ወልድ አምላክ በመሆኑም ይህን ዓለም
በሥልጣኑ ኃይል ይቆጣጠረዋል፤በሥርዓት
እንዲመራም ያደርገዋል። እኛን ከኃጢአት
ለማንጻትና የተመዘገበብንን የበደል ደብዳቤ
ለመደምሰስ ከሞተ በኋላ፥አሁን በአባቱ ጎን
ባለው ከፍተኛ ሰማያዊ የክብር ቦታ ተቀም
ጧል።
4 ልጅ በመባልና መልአክ በመባል መካ
ከል ከፍ ያለ ልዩነት አለ። ክርስቶስ የእግዚ
አብሔር ልጅ በመሆኑ ክብሩም ሆነ ስሙ
ከመላእክት ክብርና ስም ይበልጣል። 5 እግ
ዚአብሔር ከመላእክት ማንንም፥ «አንተ
ልጄ ነህ፤እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» አላለም።
ወይም፥ «እኔ አባት እሆነዋለሁ፤እርሱም
ልጅ ይሆነኛል» የተባለለት መልአክ
የለም። 6 እንዲሁም አብ የበኩር ልጁን
ወደ ዓለም በላከ ጊዜ፥ «የእግዚአብሔር
መላእክት ሁሉ ይስገዱለት» ብሎለታል።
7 ስለመላእክት ሲናገር፥ «እግዚአብሔር
መላእክቱን እንደ ነፋስ ፈጣን፥አገልጋዮቹ
ንም የእሳት ነበልባል ያደርጋቸዋል።»
8 ስለ ልጁ ግን፥ «አምላክ ሆይ ዙፋንህ ከዘ
ላለም እስከ ዘላለም ጸንቶ የሚኖር ነው።
መንግሥትህም ጽድቅን የተሞላች ናት።
9 ጽድቅን ወደድክ፤ዓመፃን ጠላህ፤ስለዚህ
እግዚአብሔር ከጓደኞችህ በላይ አድርጎ
ደስታንና ክብርን ሰጠህ» ይላል።
10 በሌላም ቦታ፥ «ጌታ ሆይ፥አንተ በመ
ጀመሪያ ምድርን ፈጠርክ፤ሰማያትም የእ
ጅህ ሥራዎች ናቸው። 11 ይሁን እንጂ
ሁሉም ያልፋሉ፤ይጠፋሉ፤አንተ ግን ለዘላ
ለም ትኖራለህ። እንደ ልብስ ያረጃሉ፤
12 እንደ ብትን ጨርቅም ትጠቀልላቸዋለህ፤
እንደ አሮጌ ልብስም ይለወጣሉ፤አንተ ግን
ምን ጊዜም ያው አንተ ነህ፤አትለወጥም፤
አታረጅም» ብሎለታል።
13 እግዚአብሔር፥ «ጠላቶችህን ድጋ
አመድ አድርጌ ከእግርህ ሥር እስካውላ
ቸው ድረስ በቀኜ በክብር ተቀመጥ» ብሎ
ከመላእክት ወገን ስለማን ተናገረ? ከልጁ
በስተቀር ስለ ማንም እንዲህ ብሎ አልተናገ
ረም። 14 መላእክትማ የሚድኑትን ሰዎች
ለመርዳትና ለመጠበቅ ከእግዚአብሔር የሚ
ላኩ አገልጋይ መናፍስት ናቸው።

## ምዕራፍ 2

1 እነዚህን የሰማናቸውን እውነተኛ ነገ
ሮች በጥንቃቄ ሳንጠብቃቸው ቀርተን ከእ

ምነታችን ተንሸራተን እንዳንወድቅ መጠን
ቀቅ ይገባናል። 2 በመላእክት አማካይነት
የተላለፈው መልእክት ሁሉ በሰዎች በኩል
ተቀባይነት ባጣ ቁጥር፥ቅጣት ሲያስከትል
መኖሩ መቼም የተረጋገጠ ነው። 3 በመላእ
ክት አማካይነት ለተላለፈው መልእክት አን
ታዘዝም ያሉ ሰዎች ከቅጣት አላመለጡም።
እኛም የእግዚአብሔር ልጅ በመጀመሪያ
ራሱ፥ ቀጥሎም ከእንደበቱ የሰሙ ተከታ
ዮቹ፥አረጋግጠው ያስተላለፉትን ታላቅ የደ
ኅንነት ቃል ከምንም የማንቆጥረው ከሆነ፥
የሚጠብቀን ቅጣት የባሰ እንደሚሆን መገን
ዘብ ይኖርብናል።
4 እግዚአብሔርም በየጊዜው ምልክቶ
ችን፥ድንቅ ነገሮችንና ለትንግርት የሚታዩ
ልዩ ልዩ ተአምራትን በማሳየት፥ለሚያምኑ
ትም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን እንደ
ፈቃዱ በማደል፥ ስለ ደኅንነት የተነገሩት
ቃሎች ሁሉ የታመኑ መሆናቸውን አረጋግ
ጦልናል።
5 እንዲሁም እዚህ ላይ አንሥተን የምን
ናገርለትን የወደፊቱን ዓለም፥ በመላእክት
ሥልጣን ሥር እንዲውል እግዚአብሔር አላ
ደረገም። 6 ይህም ይታወቅ ዘንድ ዳዊት
በመዝሙሩ፥ «አቤቱ፥ይህን ያህል የምታስ
ብለት ሰው ምንድነው? ከፍ ከፍ አድርገህ
የምታከብረው የሰው ልጅስ ማነው?
7 ምንም እንኳ ለአጭር ጊዜ ከመላእክት
ብታሳንሰውም፥ እነሆ የምስጋናና የክብር
ዘውድ አቀዳጀኸው። 8 ሁሉንም ነገር ከሥ
ልጣኑ ሥር አዋልክለት» ብሎለታል። እግ
ዚአብሔር ሁሉን ነገር ከእግሩ ሥር ሲያው
ልለት፥ ያላስገዛለት ምንም ነገር የለም።
ሆኖም፥ ባሁኑ ጊዜ ሁሉም ነገር ሙሉ
በሙሉ እንደተገዛለት አናይም።
9 ነገር ግን ለአጭር ጊዜ ከመላእክት
አንሶ የነበረው ኢየሱስ፥ ስለ ኃጢአታችን
በመሞቱ እነሆ አሁን የድልና የክብር አክ
ሊል ተቀዳጅቶ እናየዋለን። ይህም የሆነው
በመላው ዓለም ላሉ ሁሉ በእግዚአብሔር
ጸጋ የሞትን ጽዋ መቅመስ ስለነበረበት
ነው። 10 ማንኛውንም ነገር ለራሱ ክብር
የፈጠረው እግዚአብሔር፥ኢየሱስን በሥቃይ
እንዲፈተን ማድረጉ አስፈላጊ ሆነ። እንዲህ
በማድረጉም ቁጥር ስፍር የሌላቸው ወገ
ኖቹ ወደ መንግሥቱ እንዲገቡ እድል ሰጥ
ቶአቸዋል። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር፥
ኢየሱስን በሥቃዩ ሰዎችን ለደኅንነት የሚ
ያበቃ እውነተኛ መሪ አድርጎታል።
11 የቀደሳቸው እርሱና የተቀደሱት እነ
ርሱ ከአንድ የተገኙ ስለሆኑ፥እነርሱን «ወን
ድሞቼ» ብሎ መጥራት አላሳፈረውም።
12 ዳዊትም፥ «ስምህን ለወንድሞቼ እነግራ
ቸዋለሁ፥ ምዕመናን በሚሰበሰቡበት ጊዜ
በመዝሙር አመሰግንሃለሁ» ብሎ ተናግሮለ
ታል። 13 በሌላም በታ፥ «እምነቴን በእርሱ
ላይ እጥላለሁ» ይላል። ደግሞም፥ «እነሆ፥
እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች»
ብሏል።
14 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን የምን
ጠራ ተፈጥሮአችን ከሥጋና ከደም እንደሆነ
ሁሉ፥ ኢየሱስም የሞት ባለቤት የሆነውን
የዲያብሎስን ሥልጣን በመስቀሉ ሞት
ይሽር ዘንድ፥እንደ እኛ ሰው ሆነ። 15 በዚ
ህም፥ ባለ ዘመናቸው ሁሉ በሞት ፍርሃት
ተይዘው ባርያ ሆነው ይገዙ የነበሩትን ነፃ
አወጣ።
16 አመጣጡም የአብርሃምን ዘሮች ለመ
ርዳት እንጂ መላእክትን ለመርዳት አይደ
ለም። 17 ስለ እኛ በእግዚአብሔር ፊት የታ
መነ ሊቀ ካህናት ሆኖ ለማገልገልና የኃጢ
አትን ይቅርታ ለማስገኘት በሁሉም መን
ገድ እኛን ወንድሞቹን መምሰሉ አስፈላጊ
ሆነ። 18 እርሱ ራሱ መከራ የተቀበለና የተ
ፈተነ በመሆኑ፥የመከራን አስቃቂነት፥የፈተ
ናን ከባድነት በሚገባ ያውቃልና መከራ
የሚቀበሉትንና የሚፈተኑትን ሊረዳ ይች
ላል።

## ምዕራፍ 3

1 የእግዚአብሔርን ጥሪ የተቀበላችሁ
ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችን ሐዋርያና
ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስን አስቡ።
2 ሙሴ የእግዚአብሔርን ቤት በታማኝ
ነት እንዳገለገለ ሁሉ ኢየሱስም ሊቀ ካህ
ናት አድርጎ የሾመውን እግዚአብሔር በታ
ማኝነት አገልግሏል። 3 ቤቱን የሠራው ሰው
ከቤቱ ይልቅ የበለጠ ክብር እንዳለው ሁሉ፥
የኢየሱስም ክብሩ ከሙሴ ክብር የበለጠ
ነው። 4 እያንዳንዱ ቤት የራሱ ሠሪ አለው።
ማናቸውንም ነገር የሠራ ግን እግዚአብሔር
ነው።
5 ሙሴ በመጪው ዘመናት ሊነገር
ላለው ቃል ምስክር ይሆን ዘንድ፥በእግዚአ
ብሔር ቤት ሁሉ ላይ እንደ አገልጋይ
ታማኝ ነበር። 6 የክርስቶስ ታማኝነቱም ሆነ
አገልግሎቱ ግን ከዚህ የተለየ ነው። የእግዚ
አብሔርን ቤት ያገለገለው እንደ ሙሴ በአገ
ልጋይነት ሳይሆን፥በእግዚአብሔር ልጅነቱ
ነው። የእግዚአብሔር ቤት የተባልን ማደሪ

ያውም እኛ ነን። ማደሪያው ሆነን ወደፊት
የምንዘልቀውም የምንመካበትንና የምንተማ
መንበትን ተስፋ አጽንተን ይዘን ስንገኝ
ነው።
7-8 እንግዲህ ክርስቶስ ከሙሴ ይህን
ያህል የበለጠ ከሆነ፥የእሥራኤል ልጆች በበ
ረሃ እየተፈታተኑ እንዳስቆጡት፥እኛም ዛሬ
የእግዚአብሔርን ድምፅ ሰምተን እንዳናስቆ
ጣው መንፈስ ቅዱስ አበክሮ ያስጠነቅቀ
ናል። 9 በዚያን ጊዜ ጌታ እሥራኤልን ለአ
ርባ ዓመት ታገሣቸው። እነርሱ ግን ተፈታ
ተኑት እንጂ ትዕግሥቱን ከምንም አልቆጠ
ሩለትም። ይህም ሁሉ ሆኖ፥ጌታ ታላላቅ
ተአምራትን እያደረገ ከማሳየት ወደ ኋላ
አላለም። 10 በመጨረሻም እግዚአብሔር፥
«እነዚህ ሰዎች ልባቸው እንደ ተልባ ስፍር
በየጊዜው እየተንሸራተተ የሚከዳኝና ትእዛ
ዜንም የማይፈጽሙ፥እኔ የማሳያቸውንም
መንገድ የማይከተሉ በመሆናቸው በጣም
ተቆጣኋቸው» አለ።
11 ከመቆጣቱ የተነሣም ወደ ዕረፍቱ
ቦታ እንደማያገባቸው በመወሰን ራሱን በመ
ሐላ አሠረ። 12 ወንድሞቼ ሆይ፥እናንተም
ይህን አይታችሁ ልባችሁ ክፉኛ የማያምን
ሆኖ ከሕያው እግዚአብሔር አንድነት እንዳ
ይለያችሁ ተጠንቀቁ። 13 አሁንም ጊዜው
ያላለፈ በመሆኑ፥በኃጢአት ተታሎ ልቡ
በክህደት የሚደነድን ሰው እንዳይኖር ይህን
ጉዳይ በየዕለቱ እያነሣችሁ ተወያዩበት፤አን
ዱም ሌላውን ያበረታታው። 14 የክርስትናን
እምነት መጀመሪያ በተቀበልን ጊዜ በእግዚ
አብሔር ላይ የነበረንን መታመን እስከ
መጨረሻው ካዘለቅነው፥የክርስቶስ የሆነ
ውን ሁሉ እንወርሳለን።
15 «የእሥራኤል ሕዝብ በበረሃ ሳሉ ጌታ
በተናገራቸው ጊዜ ድምፁን ሰምተው ልባ
ቸውን እንዳደነደኑ፤እናንተም ዛሬ ድምፁን
ሰምታችሁ ልባችሁን እንዳታደነድኑ»
ተብሎ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ በታላቅ
ጥንቃቄ ጠብቁት።
16 ለመሆኑ እነዚያ የጌታን ድምፅ ሰም
ተው ያመጹበት እነማን ነበሩ? በሙሴ
መሪነት ከምድረ ግብፅ የወጡት የእሥራ
ኤል ሕዝብ አይደሉምን? 17 አርባ ዓመት
ሙሉ ሲያስቆጡት የነበሩትስ እነማን
ነበሩ? ባለመታዘዛቸው ምክንያት ሬሳቸው
በበረሃ ወድቆ የቀረው እነዚሁ እሥራኤላው
ያን አይደሉምን? 18 «አወርሳችኋለሁ»
ብሎ አስቀድሞ ተስፋ ከሰጣቸው በኋላ፥
መልሶ፥ «በጭራሽ አይገቡባትም» ሲል
በመሐላ የተናገረውስ እነማንን ይመስላች
ኋል? እንታዘዝም ብለው በእምቢተኝነታ
ቸው የጸኑትን እነዚሁኑ ሰዎች አይደለ
ምን? 19 እንግዲህ እነዚህን ነገሮች አንድ
ባንድ ስንመለከት የእሥራኤል ሕዝብ ወደ
ተስፋይቱ ምድር ሊገቡ ያልቻሉት፥በእግዚ
አብሔር ሳይታመኑ በመቅረታቸው መሆኑን
እንገነዘባለን።

## ምዕራፍ 4

1 ስለዚህ ወደ ዕረፍቱ እንድንገባ የተሰ
ጠን ተስፋ አሁንም እንደተጠበቀ ነው።
ይህም ስለሆነ ከእናንተ መካከል ማንም
ከራሱ ጥፋት የተነሣ ተስፋ ወደ ተሰጠው
የዕረፍት ቦታ ለመግባት ሳይችል እንዳይቀር
መፍራትና መጠንቀቅ ይገባዋል። 2 በሙሴ
ዘመን ለነበሩት እሥራኤላውያን የተነገረው
የምሥራቹ ቃል፥እንደዚያን ጊዜ ሁሉ
ዛሬም ለእኛ ተነግሮናል። ነገር ግን እሥራ
ኤላውያን ያን ጊዜ የሰሙትን ቃል በእም
ነት ስላልተቀበሉት ጥቅም አላገኙበትም።
3 እኛ ግን በእግዚአብሔር ቃል መሠረት፥
ስለምናምን ወደ ዕረፍቱ ቦታ እንገባለን።
እግዚአብሔር፥ «ወደ አዘጋጀሁላቸው የዕረ
ፍቴ ቦታ አይገቡም ብዬ በቁጣዬ ምያለሁ»
ብሎ ቢናገርም፥የዕረፍቱን ሥፍራ ግን
ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ዝግጁ አድ
ርጎ ይጠብቃቸው እንደነበር ግልጽ ነው።
4 ምክንያቱም በአንድ ሥፍራ ስለሰባተ
ኛው ቀን ሲናገር፥ «እግዚአብሔር ፍጥረ
ትን ሁሉ ፈጥሮ ካበቃ በኋላ በሰባተኛው
ቀን ዐረፈ» ይላል።
5 እንደዚሁም ቀደም ሲል እንደተጠቀ
ሰው፥ «ወደ አዘጋጀሁላቸው የዕረፍቴ ቦታ
አይገቡም» ብሎ ተናግሯል። 6 የምሥራቹ
ቃል በቅድሚያ የተሰበከላቸው እነዚያ
በሙሴ መሪነት ከምድረ ግብፅ የወጡት
እሥራኤላውያን ባለማመናቸው ምክንያት
ቢታገዱም፥ወደ ዕረፍቱ ገና የሚገቡ
ሌሎች አሉ።
7 ዳዊት «ዛሬ ድምፁን ስትሰሙ ልባች
ሁን እንዳታደነድኑት» ሲል መናገሩ ቀደም
ሲል ተጠቅሷል። እንግዲህ፥ «ዛሬ» የሚ
ለው ቃል፥እግዚአብሔር ከብዙ ዘመን
በኋላ በዳዊት አንደበት ሆኖ በመናገር እን
ደገና በውል ቀን መወሰኑን ያሳያል።
8 ከፍ ብሎ የተነገረለት የዕረፍት ቦታም
እሥራኤላውያን በኢያሱ መሪነት የገቡባ
ትን አገር ብቻ የሚመለከት አይደለም። ያን
ብቻ የሚመለከት ቢሆንማ ኖሮ፥ጌታ ከስ

ንት ጊዜ በኋላ «ዛሬ» ብሎ በውል ለይቶ
ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረም ነበር። 9 ይህም
የሚያስረዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያር
ፍበት ሌላ ፍጹም ዕረፍት ገና እንዳለ
ነው። 10 እግዚአብሔር ፍጥረትን ሁሉ
ፈጥሮ ካበቃ በኋላ በሰባተኛው ቀን እንዳ
ረፈ ሁሉ፣ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት የሚ
ገባ ማንኛውም ሰው ከሥራው ሁሉ ያር
ፋል። 11 ካለመታዘዛቸው የተነሣ ወደ ዕረ
ፍቱ መግባት ያልቻሉትን የእሥራኤላውያ
ንን መጥፎ አርአያ በመከተል እንዳንጠፋ፣
ወደዚያ ዕረፍት የምንገባበትን አስፈላጊውን
ትጋት ሁሉ እናሳይ።
12 የእግዚአብሔር ቃል ሕያውና የሚ
ሠራ ነው። በሁለት በኩል ስለት ካለው
ሰይፍ የበለጠ ይቆራርጣል። ስለዚህም
በሠራ አካላችን ጠልቆ በመግባት፣ ልባችን
የሚያስበውን፣ መንፈሳችን የሚያውጠነጥነ
ውን ማናቸውንም ነገር የመመርመር ኃይል
አለው። 13 እግዚአብሔር የማያውቀው አን
ዳችም ነገር የለም። ከራስ ጠጉራችን እስከ
እግር ጥፍራችን ያለው የሠራ አካላችን
በሙሉ፣ የውስጡም የውጭውም ለጌታ
ዓይን የተጋለጠ በመሆኑ፣ ከእርሱ ተሰውሮ
ሊቀር የሚችል ምንም ነገር አይኖርም።
አንድ ቀንም እፊቱ ቆመን ለሠራነው ነገር
ሁሉ ምላሽ እንሰጣለን።
14 እንግዲህ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየ
ሱስ፣ እኛን ለመርዳት ወደ ሰማይ የወጣ
ታላቅ ሊቀ ካህናት ስለሆነ፣ እስከ መጨረ
ሻው ሳናወላውል እርሱን በማመን እንጽና።
15 ይህም የእኛ ሊቀ ካህናት፣ ኃጢአት ካለ
መሥራቱ በቀር እንደ እኛ ሰው ሆኖ በሁ
ሉም ነገር የተፈተነ በመሆኑ ደካማነታች
ንን በቀላሉ ተረድቶ ይራራልናል። 16 ስለዚ
ህም ምሕረቱን ለመቀበልና በችግራችን
ጊዜ የሚረዳንን ጸጋውን ለመታደል እንድን
ችል፣ ያለ ፍርሃት ወደ ጸጋው ዙፋን ፊት
እንቅረብ።

## ምዕራፍ 5

1 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት ሰዎችን በመ
ወከል ስለ ኃጢአታቸው መሥዋዕትንና
መባን ለእግዚአብሔር እንዲያቀርብ ከመመ
ረጡ በስተቀር ከሌሎቹ ሰዎች የሚለይበት
ሌላ ነገር የለም። 2 እርሱም እንደ ሌላው
ሁሉ ሥጋ የለበሰ ደካማ ፍጡር መሆኑን
ስለሚገነዘብ፣ ሰዎች በቀላሉ ሊሳሳቱና ባለማ
ወቅም ኃጢአት ሊሠሩ እንደሚችሉ ስለሚ
ያውቅ ርኅራኄ ሊያሳያቸው ይችላል። 3 ስለ
ዚህም ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው መሥ
ዋዕት ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን ስለ
ራሱም ኃጢአት ጭምር ነው።
4 አንድ ሰው እርሱ ራሱ ስለፈለገ ብቻ
ራሱን በራሱ ሊቀ ካህናት አድርጎ ሊሾም
አይችልም። እንደዚህ ላለው ክብር ለመብ
ቃት እንደ አሮን በእግዚአብሔር መመረ
ጥን ይጠይቃል።
5 እንደዚሁም ክርስቶስ የሊቀ ክህነትን
ማዕርግ ያገኘው፣ ከራሱ ሳይሆን፣ «አንተ
ልጄ ነህ፤ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ» ካለው ከእ
ግዚአብሔር ነው። 6 በሌላም ሥፍራ፣ እግዚ
አብሔር፣ «እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘ
ላለም ካህን አድርጌ መርጬሃለሁ» ብሎ
ታል።
7 ክርስቶስ በሥጋ ተገልጦ በዚች ምድር
ላይ በተመላለሰበት ጊዜ፣ ነፍሱ ተጨንቃ
እንባውን እያፈሰሰ ካለጊዜው ከመሞት
ሊጠብቀው ወደሚችለው አባት በጸሎት
ልመናውን አቅርቧል። ፍጹም ትሑት ሆኖ
በመታዘዙም ጸሎቱ ተሰሚነትን አግኝ
ቷል።
8-9 ምንም እንኳ ክርስቶስ የእግዚአብ
ሔር ልጅ ቢሆንም፣ መከራን በመቀበል
መታዘዝ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ለማ
ወቅ በቅቷል። እርሱም መከራን ተቀብሎ
ፍጹምነትን ከተቀዳጀ በኋላ፣ ለሚታዘዙት
ሁሉ የዘላለም ደኅንነትን ይሰጥ ዘንድ ብቁ
ሆኖአል።
10 ስለዚህም እግዚአብሔር እንደ መልከ
ጼዴቅ ሊቀ ካህናት አድርጎ ሾሞታል።
11 ስለዚህ ጉዳይ በሰፊው መናገር ይቻል
ነበር። ነገር ግን በጥሞና የምትከታተሉት
መስሎ ስለማይታይ ብነግራችሁስ እንዴት
አድርጋችሁ ልትረዱት ትችላላችሁ?
12-13 እንደምታውቁት የክርስትናን እም
ነት ከተቀበላችሁ አያሌ ዓመታት አልፈ
ዋል። በእነዚህ ዓመታት ውስጥ እናንተ
መምህራን ሆናችሁ ሌሎችን ማስተማር ሲገ
ባችሁ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ከሥር 'ሀ'
ብሎ እንደገና የሚያስተምራችሁ ሰው የም
ትፈልጉ ሆናችሁ ተገኝታችኋል። ይህ እንግ
ዲህ፣ በክርስትና እምነት ተኰትኩታችሁ
አድጋችሁ ዳቦ ለመገርደም፣ ጥሬ ለመቆር
ጠም ከበቃችሁ በኋላ፣ ወደ ኋላ ተመልሳ
ችሁ እንደሚድህ ሕፃን፣ «ወተት ጋቱን፤
ጡጦ አጉርሱን» እንደ ማለት የሚቆጠር
ነው። እንደ ሕፃን ልጅ ወተት ብቻ ስንጋት
እንኑር ማለት ደግሞ፣ በክርስትና እምነት
አለመብሰልንና እውነትን ከሐሰት ለይቶ

አለማወቅን ያሳያል።
14 ጠንካራ የሆነ መንፈሳዊ ምግብ የሚስ
ማማው ግን፥ትክክለኛውንና ስሕተት የሆነ
ውን ነገር ለይቶ የማወቅ ልምድ ላላቸው
በመንፈስ ጐልማሶች ለሆኑ ነው።

## ምዕራፍ 6

1-2 የክርስትናን እምነት መሠረታዊ ትም
ህርት አልፋችሁት የመጣችሁ ስለሆነ፥ከእን
ግዲህ ወዲህ ያንኑ እየደጋገምን ልናስተም
ራችሁ አይገባንም። ወደ ሌላ ቁም ነገር
በመሸጋገር፥በእምነቱ ጠንካራ የሆነ ክርስቲ
ያን ሊኖረው የሚገባ ሰፊና የበሰለ አስተሳ
ሰብ ሊኖረን ያስፈልጋል። ከእንግዲህ
ወዲህ፥ንስሐ ገብቶ ከኃጢአት ስለመመለስ፥
በእግዚአብሔር ስለ ማመን፥ስለ ጥምቀቶች፥
እጆችን ጭኖ ስለመጸለይ፥ስለ ሙታን ትን
ሣኤና ስለ ዘላለም ፍርድ፥መልሰን መላል
ሰን ልንነግራችሁ አያስፈልግም።
3 ይህን ትተን ቁም ነገር ወዳዘሉ ወደ
ሌሎች ጉዳዮች እንድንተላለፍ የእግዚአብ
ሔር ፈቃድ ነው።
4-6 የምሥራቹን ቃል ከተረዱ፥የሰማያዊ
ውን በረከት ጣዕም ከቀመሱ፥የመንፈስ ቅዱ
ስን ስጦታ ከተቀበሉና የእግዚአብሔርን
ቃል መልካምነት ካወቁ፥የሚመጣውን
ዓለም ታላቅ ኃይል ምንነት ከተገነዘቡ
በኋላ፥እግዚአብሔርን ክደው ከተገኙ፥እነር
ሱን በንስሐ ለመመለስ አይቻልም። ለገዛ
ጥፋታቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ዳግመኛ
በመስቀል ላይ ይሰቅሉታል፤ ለውርደትና
ለመዘባበቻም አሳልፈው ይሰጡታል።
7 ዘወትር በሚዘንብባት ዝናብ የምትረ
ካና ለአራሾቿ የሚጠቅም ፍሬ የምታፈራ
ምድር፥ከእግዚአብሔር በረከትን ትቀበላ
ለች። 8 የዘሩባትን ትታ እሾህና አሜከላ
ብታበቅል ግን ጠፍ ተብላ ተረግማ በመጨ
ረሻም ትቃጠላለች።
9 ወዳጆቼ ሆይ፥ምንም እንኳ እንደዚህ
ብልም፥የተናገርኩት ነገር እናንተን ይመለ
ከታችኋል ማለቴ አይደለም። ምክንያቱም
ከደኅንነታችሁ ጋር ያገኛችሁት በረከት
መልካም ፍሬ በማፍራት ላይ በመሆኑ፥
10 እግዚአብሔር ድካማችሁንና አገልግሎታ
ችሁን በከንቱ የሚያስቀረው አይደለም።
በፊትም ሆነ አሁን ቅዱሳንን በመርዳት ስለ
ስሙ ያሳያችሁትን ፍቅር ከቶ ሊረሳው አይ
ችልም። 11 አሁንም የታሰበላችሁ ወሮታ
እስከሚከፈላችሁ እስከ መጨረሻው ጊዜ
ድረስ፥በዚሁ ፍቅራችሁና አገልግሎታችሁ
ጸንታችሁ እንድትኖሩ እንመክራችኋለን።
12 በእምነትና በታላቅ ትዕግሥት ጸን
ተው በመገኘታቸው እግዚአብሔር የሰጣቸ
ውን ተስፋ የፈጸመላቸውን ሰዎች ምሳሌ
ተከተሉ እንጂ ዳተኞች አትሁኑ።
13-14 እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ
በሰጠው ጊዜ፥ይህንኑ እንደሚፈጽምለት
በራሱ ምሎ አረጋግጦለታል። በራሱ መማ
ሉም፥ከእርሱ በላይ የሆነ ማንም ወይም
ምንም ነገር ባለመኖሩ ነበር። ጌታ ለአብር
ሃም የሰጠው ተስፋ፥«በእውነት እባርክሃ
ለሁ፤ ዘርህንም አበዛዋለሁ» የሚል ነበር።
15 አብርሃምም የተሰጠውን ይህን ተስፋ
በትዕግሥት በመጠባበቁ፥ልጁን ይስሐቅን
አግኝቷል።
16 አንድ ሰው ከራሱ በላይ የሆነ ስም
ጠርቶ የተናገረውን ቃል በመሐላ ያጸናል።
እንዲህ የሚያደርገውም፥ያንን ተስፋ የገባ
ውን ቃል አስገድዶ የሚያስፈጽመውና ሳይ
ፈጽም ቢቀር ደግሞ፥ይዞ የሚቀጣው
ኃይል መኖሩን ለማረጋገጥ ነው። አንድ
ጉዳይ በመሐላ ከተዘጋ በኋላ ዳግመኛ ለክር
ክር አይቀርብም። 17 እንደዚሁም እግዚአብ
ሔር ተስፋ ለሰጣቸው ሰዎች የተናገረውን
ቃሉን ምን ጊዜም የማያጥፍ መሆኑን በእር
ግጥ አውቀው በትዕግሥት እንዲቆዩ ቃሉን
በመሐላ አረጋግጦላቸዋል።
18 ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር ተስፋ
ውንና ቃል ኪዳኑን ሰጥቶናል። እግዚአብ
ሔር መዋሸት ስለማይችል በተስፋውና
በቃል ኪዳኑ የማይናወጥ እምነት ሊኖረን
ይገባል። ስለዚህ የሰጠንን ተስፋ ለመጨበጥ
ወደ እርሱ የቀረብን ሁሉ በዚህ ደስ ሊለ
ንና ልንጽናና ይገባናል። ምክንያቱም እግዚ
አብሔር ስለ ደኅንነት የሰጠው ተስፋ ምን
ጊዜም አይታጠፍም።
19-20 ይህ ተስፋም ነፍሳችንን ከተቀደ
ሰው መጋረጃ በስተጀርባ ካለው ከእግዚአብ
ሔር ጋር የሚያገናኛት አስተማማኝ መል
ሕቅ ነው። ክርስቶስም የመልከ ጼዴቅን
ማዕርግና ክብር በመቀዳጀት ሊቀ ካህናት
ሆኖ ቀድሞን ወደሰማይ በመግባት፥ዘወትር
ለእኛ ይማልድልናል።

## ምዕራፍ 7

1 መልከ ጼዴቅ የሳሌም ንጉሥና የል
ዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። አብርሃም
በዙርያው የነበሩትን ነገሥታት ድል አድ
ርጎ ሲመለስ፥መልከ ጼዴቅ ወጥቶ ተቀብሎ
ባረከው። 2 አብርሃምም ድል አድርጎ ከማረ

ከው ሀብት ፣ አንድ አሥረኛውን አሥራት
አውጥቶ ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው። «መልከ
ጼዴቅ» የጽድቅ ንጉሥ ማለት ነው። «የሳ
ሌም ንጉሥ» ደግሞ ፣ «የሰላም ንጉሥ»
ማለት ነው።
3 ስለ መልከ ጼዴቅ ወላጆች ወይም ስለ
ትውልድ ሐረጉ በጽሑፍ የሠፈረ ነገር
የለም። የተወለደበትም ሆነ የሞተበት ጊዜ
በውል ተለይቶ አይታወቅም። በዚህም
እንደ እግዚአብሔር ልጅ ለዘላለም ካህን
ሆኖ ይኖራል።
4 ከከበሩት ይልቅ የከበረ ፣ ከተመረጡት
ይልቅ የተመረጠ የትውልድ ሐረጋችን
መገኛ የሆነው አብርሃም ፣ ድል ካደረጋቸው
ነገሥታት ማርኮ ካገኘው ሀብት አሥራት
አውጥቶ ከሰጠው ፣ መልከ ጼዴቅ የቱን
ያህል ታላቅ ሰው መሆኑን መገመት አያዳግ
ትም። 5 የክህነትን ሥራ እንዲያከናውኑ የተ
መደቡት የሌዊ ተወላጆች ፣ እንደ እነእርሱ
የአብርሃም ዘር የሆኑት ወገኖቻቸው ከሚያ
ፈሩት ሀብት ፣ አሥራት እንዲቀበሉ የሙሴ
ሕግ ያዝላቸዋል። 6 መልከ ጼዴቅ ግን
ትውልዱ ከሌዊ ወገን አልነበረም። ሆኖም
አብርሃም አሥራት አውጥቶ ሰጥቶታል።
ይሁን እንጂ መልከ ጼዴቅ እግዚአብሔር
ተስፋ የሰጠውን አብርሃምን ሲባርከውና
ከምርኮውም አሥራት ሲቀበል እናያለን።
7 አንዱ ባራኪ ሌላው ተባራኪ እስከ
ሆኑ ድረስ ፣ ባራኪው ከተባራኪው መብለጡ
የሚያከራክር ነገር አይደለም።
8 በአንድ በኩል አሥራት የሚቀበሉት ፣
እንደ ማንኛውም ሰው ሟች የሆኑት ሌዋ
ውያን ሲሆኑ ፣ በሌላ በኩል ግን አሥራት
የሚቀበለው ለዘላለም ሕያው ሆኖ እንደሚ
ኖር የተነገረለት መልከ ጼዴቅ ነው።
9-10 ከዚህ የተነሣም አብርሃም ለመልከ
ጼዴቅ አሥራት አውጥቶ ከከፈለ ፣ በሙሴ
ሕግ አሥራት እንዲቀበል የተፈቀደለት
ሌዊም ገና ሳይወለድ ፣ በአብርሃም አብራክ
እያለ ለመልከ ጼዴቅ አሥራት አውጥቶ
ከፍሏል ማለት ይቻላል።
11 የሌዊ ክህነትና የኦሪት ሕግ እኛን
ለማዳን ብቃት ቢኖራቸው ኖሮ ፣ ክህነቱ
እንደ አሮን ክህነት ሳይሆን ፣ እንደ መልከ
ጼዴቅ ክህነት የሆነው ክርስቶስ መምጣት
ባላስፈለገውም ነበር።
12 መቼም የክህነቱ ሥርዓት መለወጥ
የሕጉን መለወጥ ማስከተሉ እንደማይቀር
ግልጽ ነው። 13-14 የክርስቶስ ትውልድ ከይ
ሁዳ ነገድ እንጂ የክህነትን አገልግሎት እን
ዲያከናውኑ ከተመደቡት ከሌዊ ነገድ አልነ
በረም። ከይሁዳ ነገድ ተወልዶ ካህን ሆኖ
የክህነትን አገልግሎት ያከናወነ አንድም
ሰው የለም። ሙሴም ይህን ተግባር እንዲያ
ከናውኑ አልደለደላቸውም። 15-16 የክርስ
ቶስ ክህነት የተገኘው ከሌዊ ነገድ በመወ
ለድ ሳይሆን ፣ ወሰን በሌለውና በማይጠፋ
ሕይወት ኃይል በመሆኑ ፣ ይህ ራሱ መልከ
ጼዴቅን የሚመስል ሌላ ካህን መነሣቱን
ቁልጭ አድርጎ ያሳያል። 17 ዳዊት በመዝ
ሙሩ ፣ «የመልከ ጼዴቅን ማዕርግ የተቀዳ
ጀህ የዘላለም ካህን ነህ» ብሎ ስለ ክርስቶስ
ተናግሮለታል።
18-19 የሌዊን ነገድ ብቻ የሚመለከተው
የቀድሞው የክህነት ሥርዓት ፣ ጥቅም ያለው
ሆኖ ባለመገኘቱና ማንንም ፍጹም ማድረግ
ባለመቻሉ ፣ ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን
በሚችለው የተሻለ ተስፋ ተተክቷል።
20-21 በመጽሐፍ እንደተጻፈው ፣ «እግዚ
አብሔር በመሐላ አንድ ጊዜ ተናግሯል ፣
ቃሉን ምን ጊዜም አያጥፍም፤ እንደ መልከ
ጼዴቅ ለዘላለም ካህን ነህ» ብሎ እግዚአብ
ሔር የሾመው ልጁን ክርስቶስን ብቻ
እንጂ ፣ ሌላ ማንኛውንም ካህን ሲሾም አል
ማለም። 22 ይህ በመሆኑም ክርስቶስ ሊቀ
ካህናት ሆኖ በመሐላ ለተሾመበት አዲስ
ኪዳን መተማመኛ ሰጥቶናል።
23 ቀድሞ በነበረው ኪዳን መሠረት አገ
ልግሎት የሚሰጡ ብዙ ካህናት ነበሩ።
ይህም የሆነው ፣ ካህናቱ ሟቾች ስለሆኑ
አንዱ ሲሞት ሌላው እየተተካ እንዲያገለ
ግል ነበር። 24 ክርስቶስ ግን ለዘላለም የሚ
ኖር በመሆኑ ክህነቱ የማይለወጥ ነው።
25 ለዘላለም ሕያው ሆኖ ስለሚኖርም ሁል
ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ እየማለደ
በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚመ
ጡትን ሁሉ በደሙ ፍጹም አድርጎ ያድና
ቸዋል።
26 ክርስቶስ ቅዱስ ፣ ነውርና ነቀፋ የማይ
ገኝበት ፣ የኃጢአት ጉድፍ ያልነካውና በኃ
ጢአተኞች ርኩሰት ያልተበከለ ፣ ከሰማያት
በላይ ከፍ ያለ በመሆኑ ለእኛ የሚጠቅመን
እንደዚህ ያለው ሊቀ ካህናት ነው። 27 በመ
ጀመሪያ ስለ ራሳቸው ኃጢአት ፣ ቀጥሎም
ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት በዕለት መሥዋ
ዕት እንደሚያቀርቡት ቀድሞ እንደነበሩት
ሊቃነ ካህናት አይደለም፤ምክንያቱም ክርስ
ቶስ ፣ ራሱን በመስቀል ላይ ባቀረበበት ጊዜ
አንድ ጊዜ ለዘላለም የኃጢአታችንን መሥ
ዋዕት ከፍሏልና። 28 በሙሴ ሕግ ሊቀ ካህ

ናት ሆነው ይሾሙ የነበሩት ከኃጢአትና
ከስሕተት የተነፃ ደካሞች ነበሩ። በመጨ
ረሻ ግን ከሕግ በኋላ እግዚአብሔር ከኃጢ
አት ፣ ከነውርና ከነቀፋ ንጹሕ የሆነውን
ልጁን በመሐላ ሾሞታል።

## ምዕራፍ 8

1-2 ስለ ክህነቱ ደጋግመን የተናገርንለት
ክርስቶስ ሊቀ ካህናችን ሆኖ በሰማይ በእግ
ዚአብሔር የክብር ዙፋን ቀኝ ተቀምጧል።
ሊቀ ካህናት ሆኖ የሚያገለግለውም እንደ
አይሁድ ካህናት በሰው እጅ በተሠራች
መቅደስ ሳይሆን፣በእግዚአብሔር እጅ በተ
ሠራችው በእውነተኛይቱ ቤተ መቅደስ
ነው።
3 እያንዳንዱ ሊቀ ካህናት መባና መሥዋ
ዕት ለማቅረብ እንደ ተሾመ ሁሉ፣ክርስቶ
ስም ሊቀ ካህናት በመሆኑ የሚያቀርበው
ነገር መኖር ነበረበት። 4 በአይሁድ የክህነት
ሥርዓት መሠረት መሥዋዕት የሚያቀርቡ
ብዙ ካህናት ስለነበሩ፣ክርስቶስ በዚያን ጊዜ
በምድር ላይ ቢኖር ኖሮ፣ካህን ሆኖ መሾም
ባላስፈለገው ነበር። 5 የምድራውያን ካህናት
አገልግሎት የሰማያዊው ድንኳን ምሳሌና
ጥላ በሆነችው ምድራዊት ቤተ መቅደስ
ውስጥ ነበር። ሙሴ የመገናኛውን ድንኳን
ለመሥራት በተነሣ ጊዜ፣ልክ በሲና ተራራ
ላይ በተገለጠለት ምሳሌ መሠረት በጥንቃቄ
እንዲሠራ የታዘዘው በዚህ ምክንያት ነበር።
6 ክርስቶስ ማዕከላዊ አስፈጻሚ የሆነበት
አዲስ ኪዳን ግን፣ከቀድሞው ኪዳን በበለ
ጠና በተሻለ ተስፋ ላይ የተመሠረተ በመ
ሆኑ፣ለእርሱ የተሰጠው አገልግሎት ለአሪት
ካህናት ከተሰጠው አገልግሎት የተሻለ
ነው።
7 ከዚህ በፊት የነበረው ኪዳን ጉድለት
ባይገኝበት ኖሮ በሥፍራው የሚተካ ሌላ
ኪዳን ባላስፈለገም ነበር። 8-9 ከዚህ በፊት
በተሰጠው ኪዳን አገልጋዮች ውስጥ ጉድ
ለት መኖሩን ጌታ ራሱ አመልክቷል።
«እነሆ፣ከእሥራኤልና ከይሁዳ ሕዝብ ጋር
አዲስ ቃል ኪዳን የማደርግበት ጊዜ ይመ
ጣል። ይህም አዲስ ቃል ኪዳን፣ከዚህ
በፊት አባቶቻቸውን ከግብፅ ምድር ሳወጣ
ያደረግሁትን ኪዳን የመሰለ አይደለም። አባ
ቶቻቸው በቀድሞው ኪዳን መሠረት መኖር
ስላልቻሉ፣ እኔም በበኩሌ ተውኳቸው።
10 ከእሥራኤል ሕዝብ ጋር የማደርገው
አዲስ ቃል ኪዳን ይህ ነው፤ሕጌን በአዕምሮ
አቸው ውስጥ አኖረዋለሁ፣ በልባቸውም
ውስጥ እቀርጸዋለሁ፣እኔ አምላካቸው እሆና
ለሁ፤እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ። 11 ስለዚህ
ማንም ቢሆን ወንድሙን ወይም ወዳጁን፣
‘ጌታን ዕወቅ’ በማለት አያስተምረውም።
ምክንያቱም ከትንሹ አንስቶ እስከ ትልቁ፣
ሁሉም ያውቁኛልና። 12 በደላቸውንም
ሁሉ ይቅር እላለሁ። ኃጢአታቸውንም አላ
ስብባቸውም።»
13 እግዚአብሔር ይህን ኪዳን «አዲስ»
ብሎ በመጥራቱ፣ ከዚህ በፊት የነበረው
ኪዳን «አሮጌ» መሆኑን አረጋግጧል። እያ
ረጀና እያፈጀ የሚሄድ ማንኛውም ነገር
ደግሞ፣በፍጥነት ከጥቅም ውጪ ይሆናል።

## ምዕራፍ 9

1 በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የነ
በረው የመጀመሪያው ቃል ኪዳን የመንፈ
ሳዊ አገልግሎት ሥርዓትና ምድራዊ መቅ
ደስ ነበረው። 2 መቅደሱም በመጋረጃ የተ
ለዩ ሁለት ክፍሎች ነበሩት። ከወርቅ የተ
ሠራ መቅረዝና የመሥዋዕቱ ሕብስት የሚቀ
መጥበት ጠረጴዛ የነበረበት የመጀመሪያው
ክፍል «ቅድስት» ይባል ነበር። 3 ከመጋረ
ጃው ወዲያ የሚገኘው ውስጠኛው ክፍል
ደግሞ «ቅድስተ ቅዱሳን» ይባል ነበር።
4 በቅድስተ ቅዱሳኑም ውስጥ ከወርቅ የተ
ሠራ ማዕጠንትና ሁለንተናው በወርቅ የተለ
በጠ የቃል ኪዳኑ ታቦት ነበሩበት። በቃል
ኪዳኑ ታቦት ውስጥ ደግሞ መናው የሚቀ
መጥበት፣የወርቅ መሶብ፣የለመለመችው የአ
ሮን በትርና አሥሩ ትእዛዛት የተጻፉባቸው
ሁለቱ ጽላቶች ነበሩ። 5 ከታቦቱም በላይ፣
የኃጢአት ስርየት ይገኝ የነበረበትን ሥፍራ
ኪሩቤል የሚባሉ መላእክት በክንፋቸው
ይሸፍኑት ነበር። ዋናው ዓላማችን ግን ይኽ
ስላይደለ፣ ስለነዚህ ነገሮች መዘርዘሩ ይብ
ቃን።
6 ማናቸውም ነገር በዚህ ዓይነት ከተዘ
ጋጀ በኋላ፣ካህናት አገልግሎታቸውን ለመ
ፈጸም ወደ ድንኳኒቱ የመጀመሪያ ክፍል
በየዕለቱ ይገባሉ። 7 ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ
የሚገባው ግን ሊቀ ካህናቱ ብቻ ነበር።
የሚገባውም በዓመት አንድ ጊዜ ሲሆን፣
ይኸውም እርሱና ሕዝቡ ባለማወቅ በስህ
ተት ላደረጉት ኃጢአት ስርየት፣የሚቀርበ
ውን ደም ይዞ ነበር።
8 የመጀመሪያይቱ ድንኳንና ሥርዓቷ
ጸንቶ እስካለ ድረስ የእግዚአብሔር ክብር
ወዳለበት ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚወስ
ደው መንገድ ለተራው ሕዝብ ገና ያልተከ

ፊት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ በምሳሌ ያስረ
ዳናል። 9 በዚህ ዓይነት የሚቀርበው መባና
መሥዋዕት ሁሉ ፥ የአቅራቢውን ሕሊና
ንጹሕ ሊያደርገውና ውስጣዊ ሕይወቱን
ፍጹም ሊያደርገው የማይችል መሆኑን ያስ
ገነዝበናል። 10 አሮጌው ኪዳን መብልና
መጠጥን እንዲሁም ውጫዊ የሆኑ የንጽሕና
ሥርዓቶችን ይመለከት ነበር። ይህም ኪዳን
በጊዜው የነበሩትን ሰዎች ይጠቅም የነበ
ረው ክርስቶስ አዲስና የተሻለ ሥርዓት ይዞ
እስከመጣበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነበር።
11 ክርስቶስ ለተሻለው የአዲሱ ኪዳን
ሊቀ ካህናት ሆኖ መጥቶልናል። በሰው እጅ
ወዳልተሠራችውና ከዚህ ዓለም ወዳልሆነ
ችው ታላቂቱ ሰማያዊት ቤተ መቅደስም
ገብቶአል። 12 ወደ ቅድስተ ቅዱሳኑ የገባ
ውም የፍየልና የኮርማ ደም ይዞ ሳይሆን፥
አንድ ጊዜ ለዘላለም የራሱን ደም ይዞ በመ
ሆኑ ዘላለማዊ ደኅንነትን አስገኝቶልናል።
13-14 እንግዲህ የኮርማዎችና የፍየሎች
ደም እንዲሁም ለመሥዋዕት የተቃጠለችው
ጊደር አመድ በውጫዊ ሥርዓት መሠረት
እርኩስ የሆኑትን የሚያነጻ ከሆነ፥የክርስቶስ
ደምማ የቱን ያህል ልባችንን ያነጻው! ክር
ስቶስ ዘላለማዊ በሆነው መንፈስ ቅዱስ
ራሱን ነውርና ነቀፋ የሌለበት መሥዋዕት
አድርጎ ስላቀረበ «ይህን አድርግ፤ይህን አታ
ድርግ» ብላ ከምታስጨንቀን ከቀደመችው
ሥርዓት ነፃ አድርጎ ሕያው እግዚአብሔርን
ለማገልገል ያስችለናል። 15 የተጠሩት ሁሉ፥
የእግዚአብሔር ተስፋ ተሳታፊዎች እንዲ
ሆኑ ክርስቶስ የአዲሱ ኪዳን ማዕከላዊ አስፈ
ጻሚ ሆኖ ወደዚህ ዓለም መጣ። ከመጣም
በኋላ ከአሮጌው ኪዳን ሥር በነበሩበት ጊዜ
በሠሩት ኃጢአት ምክንያት ሊደርስባቸው
ከሚችለው ቅጣት ሊያድናቸው ሲል ሞተ።
16-17 አንድ ሰው ንብረቱን በኑዛዜ ለተወ
ሰኑ ሰዎች ቢያወርስ፥ኑዛዜው ተፈጻሚነት
የሚኖረው ተናዛዡ ከሞተ በኋላ እንጂ
እርሱ በሕይወተ ሥጋ እያለ አይደለም።
ስለዚህ ማንም ሰው፥ተናዛዡ መሞቱ ሳይረ
ጋገጥ፥ንብረቱ ይገባኛል ማለት አይችልም።
18 ስለዚህ መጀመሪያ የነበረው ኪዳን
እንኳን ያለ ደም የጸና አልነበረም።
19 ሙሴ የሕጉን ትእዛዛት ለሕዝቡ ከተናገረ
በኋላ የፍየሎችና የኮርማዎችን ደም ከውኃ
ጋር ቀላቅሎ፥በሂሶጵና በቀይ የበግ ጠጉር
መጽሐፉንና ሕዝቡን ሁሉ ረጨ። 20 እንዲ
ህም በሚያደርግበት ጊዜ፥ «ይህ ደም፥በእግ
ዚአብሔርና በእናንተ መካከል የተደረገው
ቃል ኪዳን ማረጋገጫ ነው። እግዚአብሔ
ርም ይህን ቃል ኪዳን እንድትጠብቁ አዝዞ
አል» ብሎ ይናገር ነበር። 21 በዚሁ መን
ገድ ደሙን በተቀደሰችው ድንኳን ላይ
ብቻ ሳይሆን በውስጧ በሚገኙት የአምልኮ
ዕቃዎች ሁሉ ላይ ይረጭ ነበረ። 22 በእርግ
ጥም በአሮጌው ቃል ኪዳን መሠረት አብዛ
ኛው ነገር ይነጻ የነበረው በደም ከተረጨ
በኋላ ነበር። ምክንያቱም ደም ሳይፈስ ስር
የት የለምና።
23 በሰማያዊ ነገሮች ምሳሌነት የተሠራ
ችው ምድራዊቷ ድንኳንና በውስጧም
ይገኙ የነበሩት ዕቃዎች፥በሙሴ እጅ በእን
ስሳት ደም መንጻት ነበረባቸው። ሰማያዊና
እውነተኛ የሆኑት ነገሮች ግን ከዚህ እጅግ
በጣም በሚበልጥ መሥዋዕት ይነጻሉ።
24 ስለዚህም ክርስቶስ የሰማያዊት መቅ
ደስ ምሳሌ ወደ ሆነችውና በሰው እጅ ወደ
ተሠራችው «ቅድስተ ቅዱሳን» ሳይሆን፥
በእኛ ምትክ በእግዚአብሔር ፊት ለመቅ
ረብ ወደ ሰማይ ገብቶአል። 25 የአይሁድ
ሊቀ ካህናት የእንስሳ ደም ይዞ ወደ ቅድ
ስተ ቅዱሳን በየዓመቱ እንደሚገባ፥ክርስቶስ
ወደ ሰማይ የገባው በተደጋጋሚ ራሱን
መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ አይደለም።
26 በተደጋጋሚ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ
ማቅረብ የሚያስፈልገው ቢሆን ኖሮ፥ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ በየጊዜው መሠቃየትና
መሞት ነበረበት ማለት ነው። ነገር ግን የዘ
መኑ ፍጻሜ ሲደርስ ለአንድና ለመጨረሻ
ጊዜ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረቡ
ኃጢአታችንን ደመሰሰልን።
27 ሰው አንድ ጊዜ ለመሞት ተወስኖበ
ታል ፤ ከሞተ በኋላም ለፍርድ ይቀርባል።
28 እንደዚሁም ክርስቶስ የብዙዎችን ኃጢ
አት ለማስወገድ መሥዋዕት ሆኖ በመቅረብ
አንድ ጊዜ ሞቶአል። ዳግመኛ ግን ፥ ስለ
ኃጢአት መሥዋዕት ሆኖ ለመሞት ሳይ
ሆን ፥ እርሱን በተስፋ የሚጠባበቁትን ለማ
ዳን ይመጣል።

## ምዕራፍ 10

1 የኦሪት ሕግ ወደፊት የሚመጣውን
መልካም ነገር እንደ ጥላ ሆኖ የሚያመለ
ክት እንጂ ፥ እርሱ ራሱ ጥላውን የሚያጠ
ላው አካል አይደለም። ስለዚህም ባመት
ባመቱ እየተደጋገመ የሚቀርበው መሥዋ
ዕት ሕዝቡን ሊያድናቸው አልቻለም።
2 ሊያድናቸው የሚችልማ ቢሆን ኖሮ አንድ
ጊዜ በሚያቀርቡት መሥዋዕት ኃጢአታ

ቸው ተደምስሶ ንጹሕ በሆኑ ነበር። ከሕ
ሊና ወቀሳም ነፃ ስለሚሆኑ፥ደግመው ደጋ
ግመው መሥዋዕት ማቅረብ ባላስፈለጋቸ
ውም ነበር።
3ነገር ግን በየዓመቱ የሚያቀርቡት
መሥዋዕት ኃጢአታቸውን በማስወገድ
ፈንታ፥በየጊዜው እንዲያስታውሱትና እንዲ
ያስቡት አደረጋቸው። እንዲያስቡት ስለሚ
ያደርጋቸውም ምን ጊዜም ከሕሊና ወቀሳ
ነፃ አልነበሩም። 4የኮርማዎችና የፍየሎች
ደም ኃጢአትን ሊያስወግድ አይችልም።
5ክርስቶስ ወደዚች ዓለም በመጣበት ጊዜ፥
«መሥዋዕትንና ስጦታዎችን አልወደድ
ክም፤ ስለዚህም የእኔን ሰውነት አዘጋጀህ።
6በመሠዊያው ላይ ስለ ኃጢአት በሚቀርብ
የእንስሳት መሥዋዕት አልተደሰትክም።
7ስለዚህም እንደዚህ አልኩ፥ 'በመጽሐፍ
ስለ እኔ እንደ ተጻፈው፥ እነሆ ፈቃድህን
ለመፈጸም መጥቻለሁ'» ሲል ተናገረ።
8ክርስቶስ በመጀመሪያ፥ «መሥዋዕትንና
ስጦታዎችን አልወደድክም፤ በመሠዊያው
ላይ ስለ ኃጢአት በሚቀርብ የእንስሳት
መሥዋዕትም አልተደሰትክም» ካለ በኋላ፥
9«እነሆ ፈቃድህን ለመፈጸም መጥቻለሁ»
አለ። ስለዚህም የተሻለውን አዲስ ኪዳን
መሥርቶ ቀድሞ የነበረውን አሮጌ ኪዳን
ሠረዘው። 10ክርስቶስ በማያዳግም ሁኔታ
ሰውነቱን መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ የእ
ግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸሙ፥ኃጢአታ
ችን ሁሉ ተደምስሶልን ንጹሕ ለመሆን በቅ
ተናል። 11በአሮጌው ኪዳን ዘመን እያንዳ
ንዱ የአይሁድ ካህን ምንም እንኳ ዕለት በዕ
ለት በመሠዊያው አጠገብ ቆሞ መሥዋዕት
ቢያቀርብም ፥ የሚያቀርበው መሥዋዕት
ኃጢአትን ጨርሶ ለመደምሰስ አይችልም
ነበር። 12-13ክርስቶስ ግን ለኃጢአታችን
ራሱን በማያዳግም ሁኔታ መሥዋዕት አድ
ርጎ ካቀረበ በኋላ፥ጠላቶቹ እግሩ ሥር እስ
ኪወድቁ ድረስ በእግዚአብሔር ቀኝ በክብር
ተቀመጠ። 14በማያዳግም ሁኔታ ራሱን
መሥዋዕት አድርጎ በማቅረብ ከኃጢአት
ያነጻቸውንና የቀደሳቸውን ፍጹማን አድርጓ
ቸዋል።
15መንፈስ ቅዱስም ስለዚሁ ነገር የሚከ
ተለውን ምስክርነት ይሰጠናል፤ 16«ከእነ
ርሱ ጋር ወደፊት የማደርገው ኪዳን ይህ
ነው። ሕጌን በልባቸው ውስጥ አኖራለሁ፥
በአእምሮአቸውም ውስጥ እቀርጸዋለሁ።
17ኃጢአታቸውንና ክፉ ሥራቸውንም ዳግ
መኛ አላስብባቸውም።»
18ስለዚህም ኃጢአት አንድ ጊዜ እስከወ
ዲያኛው ከተደመሰሰና ከተረሳ በኋላ ስለ
ኃጢአት የሚቀርብ መሥዋዕት አይኖርም።
19-20ወንድሞቼ ሆይ ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ
ደሙን በማፍሰስ ኃጢአታችንን ለዘላለም
በመደምሰሱ ፥ በሥጋው መጋረጃነት አዲስ
የሕይወት ጐዳና ስለ ከፈተልን ፥ ቅድስተ
ቅዱሳን ወደ ሆነው የእግዚአብሔር ማደሪያ
ለመግባት የሚያስችል መብት አግኝተናል።
መጋረጃውን ቀዶ በከፈተልን አዲስ ጐዳ
ናም ወደ እግዚአብሔር መቅረብ እንችላ
ለን። ይህ ወደ እግዚአብሔር እንድንቀርብ
የቀደደው መጋረጃ የሚያመለክተው የራሱን
አካል ነው።
21-22የእግዚአብሔርን ቤት በሙሉ
ሥልጣን የሚያስተዳድር እንዲህ ያለ ታላቅ
ሊቀ ካህናት ስላለን ፥ ልባችንን ተረጭተን
ስለነጻንና ሰውነታችንን በንጹሕ ውኃ የታ
ጠብን ስለሆን፥እንደሚቀበለን ሙሉ በሙሉ
ተማምነን ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ።
23ተስፋ የሰጠን እርሱ ቃሉን የማያጥፍ
ስለሆነ፥የተናገረውን እንደሚፈጽም በአንድ
ልብ በማመን ፥ እሰጣችኋለሁ ያለንን ደኅን
ነት እንጠባበቃለን። 24ስለዚህ እርስ በርሳ
ችን በመተሳሰብ ፥ በፍቅርና በመረዳዳት ፥
ለበጎ ሥራም በመሽቀዳደም ደስ እናሰኘው።
25አንዳንድ ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን
የመሄድ ልምዳቸውን እንደተዉት እኛም
እንደ እነርሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄዱ
ንና መንፈሳዊ ስብሰባችንን መተው አይገባ
ንም። ይልቁንም ጌታ የሚመጣበት ቀን እየ
ተቃረበ የሚሄድ መሆኑን በማስተዋል እርስ
በርስ መበረታታትና መተራረም ያስፈልገ
ናል።
26እውነትን ካወቅን በኋላ መድኃኒታ
ችን ክርስቶስን በመናቅና በማቃለል ሆን
ብለን በድፍረት ኃጢአት ብንሠራ፥እንዲህ
ያለውን ኃጢአት የክርስቶስ ሞት አይሸፍነ
ውም ፥ ይህን ለማስወገድም የሚቀርብልን
ሌላ መሥዋዕት አይኖርም። 27የሚጠብቀን
ነገር ቢኖር የሚያስፈራው የእግዚአብሔር
ቁጣና ፍርድ ፥ እንዲሁም ተቃዋሚዎቹን
ሊያቃጥል የተዘጋጀው እሳት ብቻ ነው።
28የሙሴን ሕግ የተላለፈ ሰው ሁለት
ወይም ሦስት ምስክሮች ከመሰከሩበት
የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ይገደል ነበር።
29እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ልጅ የና
ቀና ያቃለለ፥ከኃጢአት ያነጻውን የክርስቶ
ስን ደም እንደ ተራ ነገር የቆጠረና ያረከሰ፥
ጸጋ የሚሰጠውንም መንፈስ ቅዱስ የተሳ

ደበ ፥ የሚጠብቀው ፍርድ እጅግ ከባድ
ነው።
30 «በቀል የእኔ ነው ፤ እኔ ለእያንዳንዱ
እንደ ሥራው እመልስለታለሁ» ያለውና
እንዲሁም ፥ «ጌታ በሕዝቡ ላይ ይፈርዳል»
ሲል የተናገረው ማን መሆኑን እናውቃለን።
31 ስለዚህም በሕያው እግዚአብሔር እጅ
መውደቅ እጅግ የሚያስፈራ ነገር ነው።
32 የእግዚአብሔር ብርሃን ከበራላችሁ
በኋላ ፥ ኢየሱስን ያወቃችሁበትንና ያን ሁሉ
መከራ ታግሣችሁ ያሳለፋችሁበትን ጊዜ
አትርሱ። 33 በአደባባይ መዘባበቻ ሆናች
ኋል ፤ ተንገላታችኋል። መከራ ከሚቀበሉ
ትም ጋር መከራን አብራችሁ ተቀብላች
ኋል። 34 ከታሠሩት ጋር በመንፈስ አብራ
ችሁ ተሠቃያችሁ። ያለ የሌለ ሀብታችሁን
ዘርፈው በወሰዱባችሁ ጊዜም ፥ የሚበልጥና
እስከወዲያኛው የማይጠፋ ሀብት በሰማይ
ቤት እንደሚጠብቃችሁ አውቃችሁ ደስ
አላችሁ።
35 ስለዚህ ምንም ነገር ቢደርስባችሁ ፥
ከፍ ያለ ዋጋ የምታገኙበት በጌታ ላይ ያላ
ችሁ ይህን የመሰለው መታመናችሁ እንዳይ
ቀዘቅዝ አደራ እላችኋለሁ። 36 እግዚአብ
ሔር የገባላችሁን ተስፋ እንዲፈጽምላችሁ
የምትሹ ከሆነ ፥ በትዕግሥት ፈቃዱን
ፈጽሙ። 37 «ሊመጣ ያለው ጌታ በቶሎ
ይመጣል ፤ አይዘገይምም። 38 ጻድቅ ግን ፥ በእ
ምነት ይኖራል። ወደኋላ ቢያፈገፍግ በእ
ርሱ ደስ አይለኝም» ተብሎ ተጽፏል።
39 እኛ ግን አምነው ከሚድኑት ወገን እንጂ
ወደኋላ አፈግፍገው ከሚጠፉት ወገን አይ
ደለንም።

## ምዕራፍ 11

1 እምነት ምንድን ነው? እምነት ገና
ያላየነውን ነገር ፥ «ይሆናል» ብለን ተስፋ
የምናደርግበትና ተስፋ ያደረግነውም ነገር
እንደሚፈጸም የምንረዳበት ማረጋገጫ
ነው። 2 በጥንት ዘመን የነበሩ አባቶችም የተ
መሰከረላቸው በእግዚአብሔር ላይ በነበራ
ቸው እምነት ነው።
3 ዓለማትና በውስጣቸውም የሚኖሩ
ማናቸውም ነገሮች ሁሉ በእግዚአብሔር
ቃል መፈጠራቸውንና የምናየውም ነገር
ከማይታይ ነገር የተገኘ መሆኑን በእምነት
እናውቃለን።
4 አቤል ፥ ቃየል ካቀረበው ይልቅ ያማረና
የተወደደ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእም
ነት አቀረበ። መሥዋዕቱንም እግዚአብሔር
ስለ ተቀበለለት ጻድቅ መሆኑ ተመሰከረ
ለት። አቤል ከሞተ ዘመናት አልፈዋል።
ከመልካም ምሳሌነቱ ትምህርት ስለምናገኝ
በት እስከዛሬ ስሙ በእምነቱ ምክንያት
ሲነሣ ይኖራል።
5 ሄኖክ እግዚአብሔርን ካመኑና ደስ ካሰ
ኙት ሰዎች አንዱ ነው። በእምነቱም እግዚ
አብሔርን ደስ ያሰኘው መሆኑ በመጽሐፍ
ተነግሮለታል። ስለዚህም ሳይሞት በሕይ
ወተ ሥጋ እንዳለ እግዚአብሔር ወደ ሰማይ
ወስዶታል። 6 ማንም ሰው ያለ እምነት እግ
ዚአብሔርን ደስ ሊያሰኘው አይችልም።
ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ሁሉ ፥ በእግዚ
አብሔር መኖር ማመን አለበት። ይህ
ብቻም በቂ አይደለም። እግዚአብሔር አበክ
ረው ለሚፈልጉት ሁሉ ዋጋቸውን የሚከፍ
ላቸው መሆኑንም ማመን ያስፈልጋል።
7 በእግዚአብሔር ከሚያምኑት ሰዎች
መካከል አንዱ ኖኅ ነበር። ኖኅ የጥፋትን
ውኃ ምልክት ሳያይ እግዚአብሔር አስጠን
ቅቆ የነገረውን ብቻ አምኖ ወዲያውኑ መር
ከብ በመሥራቱ ፥ ቤተ ሰቡን ከጥፋት ውኃ
ለማዳን በቃ። ኖኅ አምኖ በመታዘዙ ጽድ
ቅን ሲወርስ በኃጢአት የተተበተበውና
እምነት የለሹ ዓለም ግን ፥ የኖኅ እምነት
ተጻራሪ ምሳሌው ሆኗል።
8 እንዲሁም አብርሃም ፥ «አገርህን
ተውና እኔ ወደማወርስህ ምድር ሂድ»
ብሎ እግዚአብሔር በጠራው ጊዜ ፥ የሚወር
ሰውን አገር የሚጓዝበትን መንገድ ሳያ
ውቅ ፥ «እሺ» ብሎ በእምነት ታዘዘ። 9 ወደ
ተስፋው ምድር ከደረሰ በኋላም ፥ እንደ እን
ግዳ ባይተዋር ሆኖ በእምነት በድንኳን
ኖረ። እንደ እርሱ ያችን ምድር ለመውረስ
ባለተስፋ የሆኑት ልጆቹ ይስሐቅና ያዕቆ
ብም እንደዚሁ በድንኳን ዕድሜያቸውን
ፈጅተዋል። 10 አብርሃም በዚህ ዓይነት የኖ
ረው በእግዚአብሔር ጥበብ አምራ ወደ
ተሠራችው ሰማያዊት አገር ለመግባት የማ
ይናወጥ እምነት ስለ ነበረው ነው።
11 ሚስቱ ሣራም የመውለድ ዕድሜዋ
አልፎ ካረጀችና ካፈጀች በኋላ እግዚአብ
ሔር የሰጣትን ተስፋ እንደሚፈጽምላት
በእምነት ባገኘችው ኃይል ፀንሳ ልጅ ለመ
ውለድ በቃች። 12 ስለዚህም ከእርጅናው
የተነሣ ልጅ ይወልዳል ተብሎ ከማይጠበ
ቀው ከአንዱ ከአብርሃም እንደ ሰማይ ከዋክ
ብትና እንደ ባሕር አሸዋ ተቆጥሮ የማያ
ልቅ ዘር ተገኘ።
13 ከፍ ብሎ ያነሣኋቸው የእምነት

ሰዎች ሁሉ ፥ በሕይወት ዘመናቸው የተሰጣ
ቸውን ተስፋ እውን ሆኖ ማየት ባይች
ሉም ፥ የሞቱት ከእምነታቸው ሳይናወጡ
ነው። ሆኖም ይህች ዓለም የዘላለም መኖ
ሪያ ቤታቸው ሳትሆን የእንግድነት ማረፊያ
ቸው መሆኗን ስለተረዱ ፥ የተሰጣቸውን
ተስፋ በሩቁ ለማየት በመቻላቸው የልብ
ደስታ አልተለያቸውም። 14 ይህቺ ዓለም
የእንግድነት ማረፊያቸው መሆኗን የሚና
ገሩ ሁሉ ፥ በተስፋ የሚጠባበቋት ሌላ ሰማያ
ዊት አገር እንዳለቻቸው ይገልጻሉ፤
15 የዚችን ዓለም ተድላና ደስታ እንደ
ሌሎቹ ፈልገው ቢሆን ኖሮ ባላጡም ነበር።
16 እነርሱ ግን ለዚች ዓለም ተድላና ደስታ
ግድ ስላልነበራቸው ቀንም ሌትም የሚናፍ
ቋት ሰማያዊት አገራቸውን ነበር። እግዚአ
ብሔርም ተስፋ ያደረጓትን ያችን አገር አዘ
ጋጅቶ ያስቀመጠላቸው በመሆኑ «አምላካ
ቸው» ተብሎ በመጠራቱ አያፍርባቸውም።
17-18 እግዚአብሔር አብርሃምን ሊፈት
ነው ፈልጎ ፥ «ልጅህን ሠዋልኝ» ባለው
ጊዜ ፥ ዘሩ በእርሱ አማካይነት የሚበዛለት
መሆኑን በማመን አስቀድሞ በተስፋው
መሠረት ያገኘውን ልጁን በእምነት ለመሠ
ዋት አላመነታም። 19 ስለዚህም እግዚአብ
ሔር ከሞት ሊያስነሣለት እንደሚችል
አምኖ አንድ ልጁን ይስሐቅን ለመሥዋዕት
ነት አቀረበው። እንዳመነውም ሆኖለት
ልጁ ከሞት ዳነ። 20 ይስሐቅም እግዚአብሔ
ርን በማመን ወደፊት ስለሚሆነው ነገር
ልጆቹን ያዕቆብንና ዔሳውን ባረካቸው።
21 ያዕቆብ በሞት አፋፍ ላይ ሳለ ፥ እግዚ
አብሔር ለሁለቱ ልጆቹ የሚያደርግላቸውን
አምኖ ዘንጉን ተመርኩዞ ባረካቸው።
22 ዮሴፍ እግዚአብሔር ሕዝበ እሥራኤ
ልን የኋላ ኋላ ከጭቆና አገዛዝ ነፃ አውጥቶ
«አወርሳችኋለሁ» ብሎ ተስፋ ወደ ሰጠው
ምድር እንደሚያገባቸው ቢያምን ፥ ከዚያ
በሚወጡበት ጊዜ አጽሙን ትተው እንዳይ
ወጡ አዘዛቸው።
23 የሙሴ ወላጆች እግዚአብሔር መልከ
መልካም የሆነ ልጅ በሰጣቸው ጊዜ ፥ የንጉ
ሡን ትእዛዝ ሳይፈሩ ሕፃኑን ለሦስት
ወራት የደበቁት እግዚአብሔርን ስላመኑ
ነበር።
24-26 ሙሴም ባደገ ጊዜ ፥ የፈርዖን የልጅ
ልጅ ተብሎ በመጠራት ተቀማጥሎና ተንደ
ላቆ ከመኖር ይልቅ ከወገኖቹ ጋር መከራ
መቀበልን በእምነት መረጠ። የኋላ ኋላ እግ
ዚአብሔር ከፍ ያለ ዋጋ እንደሚሰጠው
አምኖ ፥ ከግብፅ ብዙ ሀብት ይልቅ የተስፋ
ቃል ስለ ተነገረለት ስለ ክርስቶስ መከራ
መቀበል እጅግ የተሻለ መሆኑን ተገነዘበ።
27 የንጉሡን ቁጣ ሳይፈራ የግብፅን አገር
ለቆ እስከ መሄድ የደረሰውም ፥ እግዚአብሔ
ርን በማመኑ ብቻ ነበር። የማይታየውንም
አምላክ እንዳየው ያህል አድርጎ በእምነቱ
ጸና። ስለዚህም ወደ ፊት ገሠገሠ። 28 የፋሲ
ካን በግ አርደው ደሙን በራፋቸው
ቢረጩ ፥ የሞት መልአክ የግብፃውያንን የበ
ኩር ልጆች ሲቀስፍ ፥ የወገኖቹን ልጆች እን
ደማይገድልባቸው ሙሴ በማመኑ ፥ ይህንኑ
እንዲያደርጉ አዘዛቸው።
29 እንዲሁም እሥራኤላውያን ቀይ ባሕ
ርን ሲሻገሩ ውኃው ግራና ቀኝ እንደ ግድ
ግዳ ቆሞላቸው በእምነት በደረቅ ምድር
አለፉ። የሚከታተሏቸው ግብጻውያን ግን
ለመሻገር ሲሞክሩ ባሕሩ አሰጠማቸው።
30 እሥራኤላውያን ፥ የኢያሪኮ ከተማ የታ
ጠረችበትን ግንብ ሰባት ቀን ከዞሩዋት በኋላ
ለመፍረስ የበቃችው ይህንኑ እንዲያደርጉ
ጌታ የተናገራቸውን ቃል በማመናቸው
ነው። 31 ሴተኛ አዳሪ የነበረችው ረዓብም
ሰላዮቹን ተቀብላ በቤቷ በመሸሸግዋ የቀ
ሩት የኢያሪኮ ከተማ ነዋሪዎች ሲያልቁ እር
ስዋ ሳትሞት የቀረችው እግዚአብሔር እንደ
ሚያድናት በማመኗ ነው።
32 እረ ስንቱ ተነግሮ ያልቃል? ስለ ጌዴ
ዎን ፥ ስለባርቅ ፥ ስለ ሶምሶን ፥ ስለ ዮፍታሔ ፥
ስለ ዳዊት ፥ ስለ ሳሙኤልና ስለ ነቢያት ሁሉ
ታሪካቸውን በዝርዝር ማቅረብ ይቻል
ነበር። ብቻ ጊዜ ያጥረኛልና እንዲሁ ልለ
ፈው። 33 እነዚህ ሁሉ እግዚአብሔርን በማ
መናቸው መንግሥታትን ተዋግተው ድል
አድርገዋል፤ ሕዝባቸውን በትክክል አስተዳ
ድረዋል፤ ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር የሰ
ጣቸውን ተስፋ ፈጽሞላቸዋል። እንዲበጫ
ጭቋቸው ወደ አንበሶች ጉድጓድ ተጥለው
የአንበሶችን አፍ በእምነት የዘጉ ፥ 34 እንዲ
ቃጠሉ በሚነድ እሳት ውስጥ ተወርው
ረው ፥ እግዚአብሔርን በማመናቸው የእሳቱ
ወላፈን እንዲት ጠጉራቸውን እንኳ ያልነካ
ባቸው አሉ። ደግሞም ከሰይፍ ስለት ያመ
ለጡ ፥ ደካሞች ሆነው ሳሉ እግዚአብሔርን
በማመናቸው ብርታት ያገኙ አሉ። እንደዚ
ሁም እግዚአብሔርን በማመናቸው በጦር
ሜዳ ተሰልፈው ጠላቶቻቸውን መድረሻ
ያሳጡ አሉ። 35 አንዳንድ ሴቶችም በማመና
ቸው ምክንያት የሞቱ ዘመዶቻቸው ሲነሡ
ላቸው ችለዋል። አንዳንዶችም ቢሞቱ

እንኳ እግዚአብሔር ከሞት እንደሚያስነሣ
ቸው በማመን ‘እግዚአብሔርን፥አንክድም’
ብለው እስከሞት ድረስ መከራ መቀበልን
መርጠዋል።
36 በእምነታቸው ምክንያት መሳቂያ
መሣለቂያ የሆኑት፥ጀርባቸው በጅራፍ ተተ
ልትሎ በወህኒ የማቀቁት፥ 37 በድንጋይ ተወ
ግረው የሞቱት፥በመጋዝ የተሰነጠቁት፥በሳ
ንጃ ተወግተው ሕይወታቸውን ያጡት ጥቂ
ቶች አይደሉም። ድሆችና ስደተኞች ሆነው
የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው በየአገሩ የተን
ከራተቱም ብዙ ናቸው። 38 ይህቺ ዓለም
ለእነርሱ የተገባች አልነበረችምና መኖሪያ
ቸው በምድረ በዳ፥በተራራ፥በዋሻና በጉድ
ጓድ ውስጥ ሆነ። 39 ታዲያ እነዚህ ሁሉ
ስለ እምነታቸው የተመሰከረላቸው ቢሆ
ንም፥ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ተስፋ
አላገኙም። 40 እንዲህ የሆነበትም ምክን
ያት፥ጌታ ለእኛ ሲል ያዘጋጀውን የተሻለ
ስጦታ በተስፋ እንዲጠብቁ ስለፈለገ ነው።

## ምዕራፍ 12

1-2 እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች
በዙሪያችን እንዳሉ ይኸው ከዚህ በላይ
ተመልክተናል። ስለዚህ እንቅፋትና ሸክም
የሚሆንብንን ነገር ሁሉ፥በተለይም አሥሮ
የሚይዘንን የኃጢአት ትብታብ ከላያችን
አውርደን ጥለን በትዕግሥት እየሮጥን የእም
ነታችን ጀማሪና ፈጻሚ የሆነውን ኢየሱስ
ክርስቶስን እንከተለው። እርሱም ወደፊት
የሚጠብቀውን ደስታ ብቻ በማየት የመስቀ
ሉን ሞትና ውርደቱንም ጭምር ከምንም
ሳይቆጥር በትዕግሥት ተቀብሎ፥በእግዚአብ
ሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል። 3 እንግዲህ
እናንተም በሚደርስባችሁ መከራ ተሸንፋ
ችሁ እንዳትገኙ፥ኃጢአተኞች ያን ሁሉ
መከራ ሲያደርሱበት በትዕግሥት የጸናውን
ኢየሱስን አስቡት። 4 እስካሁን ደማችሁን
እስከ ማፍሰስ ድረስ እምቢ ብላችሁ ከኃጢ
አትና ከፈተና ጋር ገና አልታገላችሁም።
5-6 ልጆቹ በመሆናችሁ እግዚአብሔር
እንዲህ ሲል የነገራችሁን የማበረታቻ ቃል
ረስታችኋል ማለት ነው? «ልጄ ሆይ፥የጌ
ታን ቅጣት እንደ ቀላል ነገር አትመልከት፤
ስለሚገስጽህም ተስፋ አትቁረጥ፤ ምክንያ
ቱም ጌታ የሚቀጣው የሚወደውን ነው።
ልጄ ነው የሚለውን ሁሉ ይቀጣዋልና።»
7 አባት የሚወደውን ልጁን እንደሚቀጣ
እግዚአብሔርም እንደዚሁ የሚወዳቸውን
ልጆቹን ይቀጣቸዋል። በጥፋቱ አባቱ የማይ
ቀጣው ልጅ ማን ነው? 8 እግዚአብሔርም
ልክ እንደ መልካም አባት ሆኖ ካልቀጣ
ችሁ ዲቃሎች እንጂ እውነተኛ ልጆቹ አይ
ደላችሁም ማለት ነው። 9 ወላጅ አባቶቻችን
ሲቀጡን፥ለምን ቀጡን ብለን አንጠላቸ
ውም፤አንንቃቸውም። ይህ ሁሉ ሆኖ እነር
ሱን የምናከብራቸው ከሆነ፥መንፈሳዊ አባታ
ችን የሆነውን እግዚአብሔር አምላካችንንማ
እንዴት አብልጠን አናከብረውም።
10 ወላጅ አባቶቻችን መልካም መስሎ
እንደታያቸው ለተወሰነ ጊዜ ይቀጡናል።
እግዚአብሔር የሚቀጣን ግን የቅድስናው
ተካፋዮች እንድንሆን ለእኛው ጥቅም
ነው። 11 እርግጥ ነው ማናቸውም ቅጣት
ለጊዜው ደስ እንደማይል ግልጽ ነው። ነገር
ግን ከተቀጣን በኋላ ጠባያችን እየታረመ
በጽጋም እያደግን ስንሄድ የሚያስገኘውን
ጥቅም ለመረዳት እንችላለን።
12 ስለዚህ የላሉ እጆቻችሁንና የደከሙ
እግሮቻችሁን አበርቱ። 13 አንካሳ የሆነው
እግር እንዲድን እንጂ የባሰ እንዳይናጋ ቀጥ
ተኛ በሆነው መንገድ ተራመዱ። በእምነት
ጐዳና ላይ አብረዋችሁ ከሚጓዙት ሰዎች
መካከል ደካሞች ቢኖሩም እንዲበረቱ
እንጂ ተሰናክለው እንዳይወድቁ ቀናውን
መንገድ ቀይሱላቸው።
14 ከማንም ሰው ጋር ተስማምታችሁ በሰ
ላም ኑሩ። ቅድስና የተሞላበትንም ሕይወት
ለመኖር ፈልጉ። ምክንያቱም ያለ ቅድስና
ሕይወት ጌታን ለማየት ፈጽሞ አይቻል
ምና። 15 ማንም ከእግዚአብሔር ጸጋ ርቆ
እንዳይኖር እርስ በእርሳችሁ ተሳሰቡ። መራ
ርነት ሥር ሰድዶና በልባችሁ ውስጥ በቅሎ
ችግር እንዳይፈጥር፥ሌሎችንም እንዳይመ
ርዝ ተጠንቀቁ። 16 ከእናንተ ማንም ለፍት
ወት አይገዛ። ብኩርናውን ለጊዜው ብቻ
ደስ በሚያሰኘው መብል እንደ ሸጠ እንደ
ዔሳው ጊዜያዊ ነገር ለማግኘት ስትሉ ለዘላ
ለም የሚሆነውን ተስፋችሁን እንዳታጡ
በጥንቃቄ አስቡ። 17 ዔሳው ብኩርናውን
ለመብል ከሸጠ በኋላ ተጸጽቶ አልቅሷል።
ይሁን እንጂ ጸጸቱና ልቅሶው፥አንዴ የሸጠ
ውን ብኩርና መልሶ ሊያስገኝለት አልቻ
ለም።
18-19 እናንተ እንደ ቀድሞዎቹ እሥራኤ
ላውያን በጭጋግ፥በእሳት ጢስና በጨለማ
ወደ ተሸፈነበት፥ነጐድጓድና አውሎ ነፋሱ
ምድሩን ወደናወጠበት፥ኃይለኛ የሆነው
የመለከቱ ድምፅ ወደሚያስተጋባበት፥የሚና
ገረው ድምፅ ወደሚሰማበት ወደ ሲና

ተራራ አልደረሳችሁም። እነዚያ ያንን
ድምፅ ሲሰሙ ፥ «ከእንግዲህ ወዲህ ሙሴ
ይናገረን እንጂ እግዚአብሔር አይናገረን»
ሲሉ እስከ መለመን ደርሰዋል። 20 ምክንያ
ቱም ፥ «እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ በድ
ንጋይ ተወግሮ ይሙት» የሚለው ትእዛዝ
ብቻ እንኳ ከባድ ነበርና። 21 በዚያ ተራራ
የታየው ድርጊት እጅግ የሚያስፈራ በመ
ሆኑ ሙሴ እንኳ በፍርሃት እስከ መንቀጥ
ቀጥ ደርሷል።
22 እናንተ ወደዚህ ተራራ ሳይሆን የሕ
ያው እግዚአብሔር ከተማ ወደ ሆነችው
ወደ ጽዮን ተራራ ቀርባችኋል። ይህችም
ስፍር ቁጥር የሌላቸው መላእክት የተሰበሰ
ቡባት ሰማያዊት ኢየሩሳሌም ናት። 23 እን
ዲሁም ስሞቻቸው በሰማይ የተመዘገቡላ
ቸው ምዕመናን በደስታ ወደ ተሰበሰቡበትና
የሁሉም ፈራጅ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብ
ሔር ፥ ፍጹማን ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን
ነፍሳት ቀርባችኋል። 24 እንዲሁም ደግሞ
ደሙን አፍስሶ ከእግዚአብሔር ጋር በማስታ
ረቅ ለአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደ ሆነው
ወደ ኢየሱስ ቀርባችኋል። ከኃጢአት የሚያ
ነጻው የጌታ ደም ድምፅ ፥ ከአቤል ደም
ድምፅ እጅግ ልቆ ይሰማል።
25 ስለዚህ የሚናገራችሁን ያንን የጌታን
ድምፅ ለመስማት እምቢ እሻፈረኝ እንዳ
ትሉ ተጠንቀቁ። እነዚያ ከምድር ሆኖ የተ
ናገራቸውን የሙሴን ድምፅ አንሰማም
ያሉት ካላመለጡ ፥ እኛማ ከሰማይ የመጣል
ንን መልእክት እንቀበልም ፥ አንሰማም
ብንል ከፍርዱ እንዴት ልናመልጥ እንችላ
ለን? 26 በሲና ተራራ ላይ ሆኖ በተናገረ
ጊዜ ድምፁ ምድርን አናውጧል። ዳግመኛ
በሚናገርበት ጊዜ ፥ «ምድርን ብቻ ሳይሆን
ሰማያትንም ጭምር እናውጣለሁ» ሲል
ቃል ገብቶአል። 27 ይህም ፥ ጊዜያዊ የሆኑት
ነገሮች ሁሉ ተወግደው ጽኑ መሠረት ያላ
ቸው ነገሮች ብቻ እንደሚቀሩ ያመለክ
ታል።
28 እንግዲህ እኛ የማትናወጠውን መንግ
ሥት ስለምንወርስ እግዚአብሔርን እናመስ
ግነው። እንዲሁም ጌታ የሚደሰትበትን
ቅዱስ ፈቃዱን እየፈጸምን በአክብሮትና
በፍርሃት እናገልግለው። 29 ምክንያቱም
አምላካችን የሚያቃጥል እሳት ነውና።

## ምዕራፍ 13

1 በእውነተኛ የወንድማማችነት ፍቅር
እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ። 2 እንግዶችን ተቀ
ብላችሁ ማስተናገድንም አትርሱ። አንዳንድ
ሰዎች ማንነታቸውን ሳያውቁ መላእክትን
እንኳ በእንግድነት ተቀብለው እስከማስተና
ገድ ደርሰዋልና። 3 የታሠሩትን እንደራሳ
ችሁ በመቁጠር ርኅራኄ አድርጉላቸው።
መከራ የሚቀበሉትንም ሰዎች ፥ በእነርሱ
ላይ የደረሰባቸው መከራ ልክ በእናንተ ላይ
እንደ ደረሰ በመቁጠር አስቡአቸው።
4 ጋብቻ በሁሉም ዘንድ መከበር እንዳለ
በት ታውቆ ፥ ባል ለሚስቱ ፥ ሚስትም ለባልዋ
ታማኝ መሆን ይገባቸዋል። ምክንያቱም
የዝሙት ሥራ የሚፈጽሙትንና የጋብቻን
ቃል ኪዳን የሚያረክሱትን እግዚአብሔር
ይቀጣቸዋልና።
5 የገንዘብ ፍቅር አይግዛችሁ ፤ ባላችሁ
ነገር ረክታችሁ ለመኖር ጣሩ። ምክንያቱም
እግዚአብሔር ፥ «ምን ጊዜም ቢሆን በችግራ
ችሁ እደርስላችኋለሁ ፤ ምን ጊዜም ቢሆን
አልተዋችሁም» ብሎ ተናግሮአልና። 6 ስለ
ዚህ እኛም ያለ ምንም ፍርሃት ፥ «እግዚአ
ብሔር ረዳቴ ስለሆነ ምንም ነገር አልፈ
ራም ፤ ሰው ምንም ሊያደርገኝ አይችልም»
ማለት እንደፍራለን።
7 የእግዚአብሔርን ቃል ያስተማሩአች
ሁን መሪዎቻችሁን አትርሱዋቸው። አናኗ
ራቸውንና መልካሙን ሥራቸውን በማየት
እናንተም እንደ እነርሱ በጌታ ላይ ፅኑ እም
ነት ይኑራችሁ።
8 ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት ፤ ዛሬና ለዘላ
ለም ያው ነው ፤ አይለወጥም። 9 ስለዚህ ልዩ
ልዩ በሆነ አዲስና እንግዳ ትምህርት ምክን
ያት ከእውነተኛው መንገድ እንዳትወጡ
ተጠንቀቁ። መንፈሳዊ ሕይወታችን ፥ 'ይህን
ብላ ፥ ያን አትብላ' በምትል ባለፈችው ሥር
ዓት ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም። እን
ዲህ ያለው አስተሳሰብ እኛን ይቅርና ሥርዓ
ቱን ለመፈጸም የሞከሩትንም አልጠቀማቸ
ውም። ስለዚህ መንፈሳዊ ሕይወታችን በእግ
ዚአብሔር ጸጋ ላይ ብቻ መመሥረት አለ
በት።
10 እኛ ክርስቶስ በሞቱ ያስገኘልን መሠ
ዊያ አለን። ለኦሪት ሕግ በመታዘዝ ደኅን
ነት እናገኛለን ብለው የሚያስቡ ፥ ከዚህ
መሠዊያ ሊሳተፉ መብት የላቸውም።
11 የአይሁድ ሊቀ ካህናት የኃጢአት ይቅ
ርታ የሚያስገኘውን የእንስሳት ደም ይዞ
ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ ፥ የእንስሳዎቹ
ሥጋ ግን ከሠፈሩ ውጪ እንዲቃጠል ይደ
ረግ ነበር። 12 እንዲሁም ኢየሱስ ደሙን
በማፍሰስ እኛን ለመቀደስ ሲል ከኢየሩሳ

ሌም ከተማ ውጭ መከራ ተቀብሎልናል።
13 ስለዚህ እኛም ከሠፈሩ ውጭ ወዳለው
ወደ እርሱ በመሄድ የውርደቱ ተካፋዮች
እንሁን። 14 ይህች ዓለም ዘላለም የምንኖር
ባት የመጨረሻ መኖሪያችን አይደለችም።
ዘላለማዊ ቤታችንስ ልባችን በተስፋ ሞልቶ
የምንጠባበቃት ሰማያዊት ከተማ ናት።
15 እንግዲህስ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚ
አብሔር የምስጋና መሥዋዕት ዘወትር እና
ቅርብ። የምስጋና መሥዋዕት ማለትም ከአን
ደበታችን የምትወጣና እርሱን ከፍ ከፍ
የምታደርገው የውዳሴ ቃል ናት። 16 እንዲ
ሌላው መልካም ነገር ማድረግና እርስ በእ
ርስ መረዳዳት እንዳለባችሁም አትርሱ።
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መሥዋ
ዕት እንዲህ ያለው በጎ አድራጎት ነው።
17 ለመንፈሳዊ መሪዎቻችሁ በመታዘዝ፥የሚ
ሰጡአችሁን ምክር ሁሉ በሥራ ላይ ልታ
ውሉት ይገባል። እነርሱ የሚጠየቁበት ኃላ
ፊነት ስላለባቸው መንፈሳዊ ሕይወታችሁ
ጤነኛ እንዲሆን ይተጋሉ። ብትታዘዟቸው
ሥራቸውን በደስታ ያከናውናሉ። ያለበለ
ዚያ ግን ታሳዝኗቸዋላችሁ። እናንተም እነ
ርሱን በማሳዘናችሁ የምታተርፉት አንዳ
ችም ጥቅም አይኖርም።
18 ለእኛም ደግሞ ጸልዩልን። ትክክለኛ
የሆነውን ነገር ለማድረግ በሚቻለን ሁሉ
የደከምን በመሆኑ ከሕሊና ወቀሳ ነጻ ነን።
19 በተለይም እኔ ወደ እናንተ በፍጥነት
ለመምጣት እንድችል ተግታችሁ ጸልዩ
ልኝ።
20-21 በእግዚአብሔርና በእናንተ መካ
ከል በክርስቶስ ደም ጸንቶ ለቆመው ዘላለ
ማዊ ቃል ኪዳን አማካይ የሆነውን ታላቁን
የበጎች እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሞት ያስ
ነሣው የሰላም አምላክ፥ ፈቃዱን ለመፈጸ
ምና የመልካም ነገር ሁሉ ባለቤቶች ለመ
ሆን ያብቃችሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ አማካ
ይነትም በእናንተ ውስጥ ደስ የሚያሰኘውን
ሁሉ ያድርግ። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘላ
ለም እስከ ዘላለም የተመሰገነ ይሁን።
አሜን!
22 ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ የጻፍኩላችሁ
ደብዳቤ አጭር ስለሆነ በጥሞና አንብቡት።
23 ጢሞቴዎስ ከእሥር ቤት መውጣቱን ስነ
ግራችሁ ደስ ይለኛል። በቶሎ ወደ እኔ
ከደረሰም፥አብረን ወደ እናንተ እንመጣለን።
24 ለመሪዎቻችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ ወን
ድሞቻችሁ ለሆኑት ሁሉ ሰላምታችንን አቅ
ርቡልን። እዚህ በኢጣሊያ አገር ያሉ ወን
ድሞች ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። 25 የእግዚ
አብሔር ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

# የሐዋርያው ያዕቆብ መልእክት

## መግቢያ

የዚህ መልእክት ጸሐፊ የሆነው ያዕቆብ፥የጌታ ወንድም ነው። እርሱም በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ውስጥ የኢየሩሳሌም ቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። ይህን መልእክት በ45 እና በ50 ዓ.ም. መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ፥ተበትነው ለነበሩት ለአይሁድ ክርስቲያኖች ጽፎላቸዋል። የመልእክቱ መሠረተ አሳብ እግዚአብሔርን አምነው ጥበብንና ትዕግሥትን ገንዘባቸው ያደረጉ ምዕመናን፥ እምነታቸውን በበጎ ሥራ መግለጥ፥እንደ ፈቃዱ እየኖሩም ለቃሉ መታዘዝ የሚገባቸው መሆኑን፥እንዲገነዘቡት ማድረግ ነው።

---

## ምዕራፍ 1

1 በዓለም ሁሉ ተበታትነው ለሚኖሩ የአ
ይሁድ ወገን ለሆኑ ክርስቲያኖች። የእግዚአ
ብሔርና የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይ
ከሆነው ከያዕቆብ የተላከ መልእክት። ሰላም
ለእናንተ ይሁን።
2 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ልዩ
ልዩ መከራና ፈተና በሚደርስባችሁ ጊዜ
ደስ ይበላችሁ። 3 ምክንያቱም እምነታችሁ
በተለያዩ መከራዎች በሚፈተንበት ጊዜ
በትዕግሥት የመቋቋምን ልምምድ ታገኙበ
ታላችሁና። 4 ምንም እንከን ሳይኖርባችሁ
በሕይወት የበሰላችሁና ፍጹማን ትሆኑ

ዘንድ በፈተናችሁ ሁሉ ትዕግሥት የበዛላ
ችሁ ሁኑ።
5 ከመካከላችሁ ጥበብ የጐደለው ሰው
ቢኖር እግዚአብሔርን በጸሎት ይለምን።
እግዚአብሔር ለሚለምኑት ሁሉ ቅር ሳይ
ሰኝ በደስታ የሚሰጥ ቸር አምላክ ስለሆነ፥
ለእርሱም የለመነውን ጥበብ ይሰጠዋል።
6 ሆኖም አንድ ነገር እንዲደረግላችሁ በም
ትለምኑበት ጊዜ፥እግዚአብሔር የለመኑትን
የማይነሣ የነገሩትን የማይረሳ መሆኑን እው
ቃችሁ ፥ ሳትጠራጠሩ በእምነት ስጠን
በሉት። ምክንያቱም የሚጠራጠር ሰው በነ
ፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባሕር
ሞገድ ነውና። 7-8 እንዲህ ዓይነቱ ልቡ በሁ
ለት አሳብ የሚዋልልና አቋም የለሽ ሰው፥
ከእግዚአብሔር አንዳችም ነገር አገኛለሁ
ብሎ ተስፋ አያድርግ።
9 ሀብት የሌለው ክርስቲያን አጣሁ
ነጣሁ ብሎ አይዘን። እግዚአብሔር የማይ
ጠፋ ሀብት ስለሰጠው ደስ ይበለው።
10-11 ሀብታም የሆነ ክርስቲያንም የዚህ
ዓለም ሀብት በበጋ ፀሐይ ጠውልጎ እንደሚ
ረግፍ አበባ መሆኑን ተገንዝቦ ፥ እግዚአብ
ሔር ሀብቱን ቢነሳውም አይከፋው። የሣር
አበባ ጠውልጎ ውበቱ እንደሚረግፍ ሁሉ፥
ባለጸጋም ላይና ታች ብሎ ያከማቸውን
ሀብት ትቶ ያልፋል።
12 በሚያጋጥመው ፈተና ውስጥ በትዕግ
ሥት የሚያልፍ ሰው የተባረከ ነው። በፈተ
ናው ውስጥ ጸንቶ በመገኘቱ፥እግዚአብሔር
ለወዳጆቹ ያዘጋጀውን የሕይወት አክሊል
ይቀዳጃል። 13 ማንም ሰው በፈተና ላይ
በወደቀ ጊዜ ፥ «ፈተናውን ያመጣብኝ እግ
ዚአብሔር ነው» አይበል። እግዚአብሔር
በክፉ ነገር አይፈተንም። ሰዎችም ክፉ
ነገር እንዲያደርጉ አይፈትናቸውም።
14 እያንዳንዱ ሰው የሚፈተነው ከራሱ ክፉ
ምኞት የተነሣ ተታሎ ከወጥመድ ሲወድቅ
ነው። 15 ክፉ ምኞት ኃጢአትን ይወል
ዳል። ኃጢአትም ሲያድግ ሞትን ይወል
ዳል። 16 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ፥ ስለዚህ
ተታላችሁ ስሕተት ላይ እንዳትወድቁ ተጠ
ንቀቁ።
17 በጎና ፍጹም የሆኑ ስጦታዎች ሁሉ
የሚመነጩት ፥ ምን ጊዜም ከማይለወጠውና
የብርሃናት ሁሉ ፈጣሪ ከሆነው ከላይ ከእግ
ዚአብሔር ዘንድ ነው። 18 እርሱ በክርስቶስ
ላዳናቸው አዲስ ፍጥረቶች ሁሉ የመጀመሪ
ያዎቹ እንድንሆን በገዛ ፈቃዱ በእውነት
ቃል ልጆቹ አደረገን።
19 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ለመስ
ማት የፈጠናችሁ፥ለንግግርና ለቁጣ ግን የተ
ቆጠባችሁ ሁኑ። 20 ምክንያቱም ቁጣ፥እግ
ዚአብሔር የሚደሰትበት ቅዱስ ፈቃዱ እን
ዳይፈጸም፥እንቅፋት ይሆናል።
21 ስለዚህ ርኩሰትንና የክፋትን ቅሪት
ሁሉ አስወግዳችሁ ፥ እግዚአብሔር በልቦና
ችሁ ውስጥ ለተከለውና ነፍሳችሁን ማዳን
ለሚችለው ቃሉ ተገዙ።
22 የሚነገረንን የእግዚአብሔር ቃል ሰም
ተን በሥራ ላይ እናውለው እንጂ፥ሰሚዎች
ብቻ በመሆን ራሳችንን አናታልል።
23-24 ቃሉን ሰምቶ በሥራ ላይ የማያውል
ሰው ፥ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው
ይመስላል። እንዲህ ያለው ሰው ፥ መስተዋ
ቱን አይቶ ዞር ሲል የገዛ ፊቱ ምን እንደሚ
መስል ወዲያው ይረሳዋል። 25 ነገር ግን ነፃ
የሚያወጣውን ፍጹሙን የእግዚአብሔር
ቃል ሰምቶ ሳይረሳ በልቡ ውስጥ በማሰላ
ሰል በሥራ ላይ የሚያውለውን ሰው፥በሚያ
ደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር ይባርከ
ዋል።
26 ከአንደበቱ የሚወጣውን ነገር ሳይቆጣ
ጠር ‘ሃይማኖተኛ ነኝ’ የሚል ሰው ራሱን
ያታልላል ፤ ሃይማኖቱም ዋጋ ቢስ ነው።
27 በእግዚአብሔር አብ ፊት ነውርና ነቀፋ
የሌለበት ሃይማኖት ማለት ፥ አባትና እናት
የሞቱባቸውን ልጆች ፥ እንዲሁም ባሎቻ
ቸው የሞቱባቸውን መበለቶች፥በችግራቸው
መርዳትና ራስንም ከዓለም ርኩሰት በንጽ
ሕና መጠበቅ ማለት ነው።

## ምዕራፍ 2

1 ወንድሞቼ ሆይ፥የክብር ጌታ በሆነው
በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የምታምኑ
በመሆናችሁ ፥ ሀብታሞችን በማክበር ድሆ
ችን በመናቅ በሰዎች መካከል ልዩነት አታ
ድርጉ።
2 በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰብስባችሁ
ሳለ ፥ ሁለት ሰዎች ይመጣሉ ፤ አንዱ ሀብ
ታም ፥ ሌላው ድሀ። ሀብታሙ በውድ ዋጋ
በተገዛ የሚያምር ልብስ ተሽቀርቅሯል፤በወ
ርቅ ቀለበትም አጊጧል። ድሀው ግን ድሪቶ
ለብሷል። 3 ሀብታሙን በአክብሮት ተቀብላ
ችሁ በማለፊያ ወንበር ላይ በክብር ቦታ
ታስቀምጡታላችሁ። ድሀውን ግን፥ «መቀ
መጫህ ከዚህ አይደለም፤ከዚያ ጥግ ቁም።
ከፈለግህም በወለሉ ላይ ተቀመጥ» ትሉታላ
ችሁ። 4 ይህን የመሰለ ልዩነት የምታደርጉ
ከሆነ መለኪያችሁ ያልተስተካከለ፥ አድል

ዎን የሚፈጽም ዳኛ መሆናችሁ አይሰማች
ሁም?
5 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥እግዚአ
ብሔር የዚህ ዓለም ድሆች በእምነት በልጽ
ገው፥ለሚወዱት ሁሉ ተስፋ የሰጣቸውን
መንግሥተ ሰማያትን እንዲወርሱ የመረጣ
ቸው መሆኑን ልብ በሉ። 6 እናንተ ግን ሀብ
ታሞችን በማክበር ድሆችን በመናቅ ልዩ
ነት ታደርጋላችሁ። ኸረ ለመሆኑ የሚጨቁ
ኗችሁና በየፍርድ ቤቱ እየከሰሱ የሚያንገላ
ቷችሁ ሀብታሞቹ አይደሉምን? 7 የተጠራ
ችሁበትን የክርስቶስን ክቡር ስም የሚያዋር
ዱስ እነርሱ አይደሉምን?
8 ዋናው ቁም ነገር፥ «ማንኛውንም
ሰው እንደራስህ አድርገህ ውደድ»
ተብሎ በመጽሐፍ የተነገረውን የከበረ
ሕግ መፈጸም ነው። 9 እናንተ ግን በሰ
ዎች መካከል ልዩነት በማድረግ ሀብታሞ
ችንና ድሆችን በእኩል ዓይን ስለማታይዋ
ቸው ሕግን ታፈርሳላችሁ። እንዲህ
ያለው አድራጎት ኃጢአት በመሆኑ ሕጉ
ራሱ ይፈርድባችኋል።
10 ሌላውን ሕግ በሙሉ ጠብቆ እንዲ
ቱን ነጥብ ግን የሚያፈርስ፥ሁሉንም እንዳ
ፈረሰ ይቆጠራል። 11 ጌታ፥ «አታመንዝር»
ብቻ አላለም። ነገር ግን «አትግደል»
ደግሞ ብሏል። ስለዚህ ከዝሙት ሥራ
ተጠብቀህ በንጽሕና ብትኖር፥በሌላ በኩል
ግን የሰውን ነፍስ ብታጠፋ የእግዚአብሔ
ርን ሕግ አፍርሰሃል፤ኃጢአትም ሠርተ
ሃል።
12 ሰዎችን ነፃ በሚያደርገው በጌታ ሕግ
እንደሚፈረድባችሁ በማወቅ፥ በምትናገሩ
ትም ሆነ በምታደርጉት ሁሉ ጥንቃቄ ይኑ
ራችሁ። 13 ምክንያቱም ለሰዎች ምሕረት
የማያደርገውን ሰው እግዚአብሔርም ያለ
ምሕረት ይፈርድበታልና። ምሕረት ምን
ጊዜም ፍርድን ድል ያደርጋል።
14 የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥አንድ
ሰው እምነት አለኝ ቢል፥ነገር ግን እምነ
ቱን በበጎ ሥራው ባያስመሰክር ምን ፋይዳ
አለው? እንዲህ ያለው እምነት ሊያድነው
ይችላልን? 15 ከክርስቲያን ወገኖቻችን መካ
ከል፥አንድ ወንድም ወይም አንዲት እህት
የዕለት ጉርስ የዓመት ልብስ የሌላቸው ያጋ
ጥሟችኋል እንበል። 16 እነዚህን ሰዎች፥ከእ
ናንተ መካከል አንዱ፥ «በሉ እንግዲህ ይቅ
ናችሁ፤ብርድ አይንካችሁ፤ረሃብ አይድረስባ
ችሁ» በማለት፥አንዳችም እርዳታ ሳያደርግ
ላቸው ቢሸኛቸው ጥቅሙ ምንድን ነው?
17 እምነትም እንደዚሁ ነው። በበጎ
ሥራ የማይገለጥ እምነት ነፍስ እንደተለየ
ችው ሥጋ የሞተ ነው።
18 ከመካከላችሁ አንዱ፥ «አንተ እምነት
ብቻ አለህ፤ እኔ ደግሞ በጎ ሥራ ብቻ
አለኝ» የሚል ሰው ይኖር ይሆናል። መልሱ
ቀላል ነው። ወንድሜ ሆይ፥ ይህን ካልክ
አንተ በጎ ሥራ የሌለበት እምነትህን አሳ
የኝ። እኔ ግን እምነቴን በበጎ ሥራዬ አሳይ
ሃለሁ።
19 አንድ እግዚአብሔር እንዳለ ታምናለ
ህን? የምታምን ከሆነ መልካም። ለማመን
ለማመኑማ አጋንንትም እግዚአብሔር መኖ
ሩን ያምናሉ። እንዲያውም እርሱን በመ
ፍራት ይንቀጠቀጣሉ። 20 አንተ ሞኝ!
በበጎ ሥራ የማይገለጥ እምነት ፋይዳ ቢስ
መሆኑን መገንዘብ ይኖርብሃል። 21 አባታ
ችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን መሥዋ
ዕት አድርጎ ባቀረበ ጊዜ፥ ባሳየው በጎ
ሥራ የጸደቀ መሆኑን አታውቁምን? 22 በዚ
ህም፥ እምነትና በጎ ሥራ የማይነጣጠሉ
መሆናቸውን ታያላችሁ። አብርሃም በፈጸ
መው በጎ ሥራ እምነቱ ሙሉ መሆኑን አስ
መሰከረ። 23 ከዚህም የተነሣ፥ «አብርሃም
እግዚአብሔርን አመነ፤ እምነቱም ጽድቅ
ሆኖ ተቆጠረለት» ተብሎ በመጽሐፍ ተነገ
ረለት። 'የእግዚአብሔር ወዳጅ' የተባለ
ውም በዚሁ ምክንያት ነው። 24 ይህንን ስን
መለከት፥ሰው የሚጸድቀው በእምነት ብቻ
ሳይሆን በበጎ ሥራም ጭምር መሆኑን ልንገ
ነዘብ እንችላለን።
25 ረዓብ የተባለችው ሴተኛ–አዳሪ የፈጸ
መችው በጎ ሥራ ሌላ ምሳሌ ሊሆነን ይች
ላል። ረዓብ የእሥራኤልን መልእክተኞች
በቤቷ ተቀብላ፥የሚፈልጓቸው ሰዎች ሳያገ
ኟቸው እንዲያመልጡ ረድታቸዋለች። በእ
ምነት ባደረገችው በዚህ በጎ ሥራዋም
እንደ ጻድቅ ተቆጥራለች። 26 ነፍስ የተለየ
ችው ሥጋ በድን እንደሆነ ሁሉ፥በጎ ሥራ
የሌለውም እምነት የሞተ ነው።

## ምዕራፍ 3

1 ወንድሞቼ ሆይ፥የቃሉ አስተማሪዎች
የሆኑ ከሌሎች ይልቅ ፍርዳቸው የጠበቀ
ስለሚሆን ሁላችሁም አስተማሪዎች ለመ
ሆን አትፈልጉ። 2 ሁላችንም በብዙ ነገር
እንሳሳታለን። ከአንደበቱ የሚወጣውን ቃል
መቆጣጠር የሚችል ግን፥እርሱ መላ ሰውነ
ቱን መቆጣጠር የሚችል ፍጹም ሰው

ያደርጋችኋል።
11 ወንድሞች ሆይ፥እርስ በርሳችሁ አት
ነቃቀፉ። አንዱ ሌላውን ክፉ አይናገረው።
እንዲህ ማድረግ፥ «እርስ በርሳችሁ ተፋ
ቀሩ» የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ መፃ
ረር ነው። ሕግን መፃረር ማለት ልንፈጽ
መው በተሰጠን ሕግ ላይ ፈራጅ ዳኛ
መሆን ማለት ነው። 12 የሕጉ ባለቤትና ትክ
ክለኛውን ፍርድ ሰጪ እግዚአብሔር ብቻ
ነው። ሊያጠፋም ሊያድንም የሚችል
እርሱ ነውና። ታዲያ በሌላው ላይ የምትፈ
ርድ አንተ ማነህ?
13 «ዛሬ ወይም ነገ እንዲህ ካለ አገር
ሄደን አንድ ዓመት በመቆየት ከፍተኛ
ትርፍ የሚያስገኝ የንግድ ሥራ እናቋቁማ
ለን» የምትሉ ሁሉ እስቲ አድምጡ።
14 ለመሆኑ ነገ የሚሆነውን ነገር ታውቁታ
ላችሁ? ሕይወታችሁ ለአንድ አፍታ ታይቶ
ወዲያው እንደሚረግፍ ጤዛ ነው። 15 ለወደ
ፊቱ አንድ ነገር ስታቅዱ፥ «የእግዚአብሔር
ፈቃዱ ሆኖ በሕይወተ ሥጋ ለመኖር ቢያበ
ቃን፥ እንዲህ ያለውን ነገር እናደርጋለን»
ከማለት አትለፉ። 16 እናንተ ግን ሁሉ ነገር
በእጃችሁ ያለ ይመስል በራሳችሁ ትመካላ
ችሁ። እንዲህ ያለው ትምክህት ደግሞ ክፉ
ነው።
17 ስለዚህም ማድረግ የሚገባውን በጎ
ነገር እያወቀ የማያደርግ ሰው፥እርሱ ኃጢ
አተኛ ነው።

## ምዕራፍ 5

1 እናንተ ሀብታሞች አድምጡ። አስቃቂ
መከራ ስለሚጠብቃችሁ እየዬ ብላችሁ አል
ቅሱ። 2 ሀብታችሁ ሁሉ በስብሶ ተበላሽ
ቷል፤የክት ልብሳችሁንም ብል በልቶታል።
3 ያከማቻችሁት ብርና ወርቅም ዝጓል። ዝገ
ቱም ከሳሽና ወቃሽ ይሆንባችኋል፤ ይኸ
ለመጨረሻው መጥፊያችሁ ያከማቻችሁ
ትም ሀብት፥ሥጋችሁን እሳት ሆኖ ያቃጥለ
ዋል። 4 የሠራተኞቻችሁን የድካም ዋጋ ስላ
ልከፈላችኋቸው መራራ ልቅሶአቸውንና
ጩኸታቸውን ያሰማሉ። ልቅሶና ጩኸታቸ
ውም ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ጆሮ
ደርሷል።
5 ለሰውነታችሁ ደስ የሚያሰኘውን ሁሉ
በመፈጸም ምድራዊ ሕይወታችሁን ተንደላ
ቃችሁ አሳልፋችሁታል። ሰውነታችሁንም
ለእርድ እንደ ተዘጋጀ ቀልብ ሠንጋ አድል
ባችሁታል። 6 ራሳቸውን ሊከላከሉ፥ሊቋቋ
ሚችሁም አቅም በሌላቸው ንጹሐን ላይ
ፈርዳችሁ ገድላችኋቸዋል።
7 ወንድሞቼ ሆይ! ገበሬ፥ዝናብ ወቅቱን
ጠብቆ እስኪዘንብ፥የመከር ወራትም ደርሶ
አዝመራውን እስኪሰበስብ እንደሚታገሥ፥
እናንተም የጌታን መምጣት እንደዚሁ በት
ዕግሥት ተጠባበቁ። 8 ጌታ የሚመጣበት
ጊዜ ቅርብ ስለሆነ በትዕግሥትና በተስፋ
ጸንታችሁ ኑሩ።
9 ወንድሞቼ ሆይ፥እስከዚያ ግን፥እርስ
በርሳችሁ አትነቃቀፉ፤አንዱ በሌላው ላይም
አያፍረድ። እነሆ በሁሉ ላይ ፈራጅ የሆ
ነው ጌታ ከደጅ ቆሟል።
10 ወንድሞቼ ሆይ፥መከራና ችግር በሚ
ያጋጥማችሁ ጊዜ ትዕግሥትን ገንዘብ ለማድ
ረግ በጌታ ስም ያስተማሩትን ነቢያት
ምሳሌ ተከተሉ። 11 ያ ሁሉ መከራ ሲደርስ
ባቸው በትዕግሥት የጸኑትን ብሩካን እንላቸ
ዋለን። ኢዮብ የደረሰበትን መከራ እንዴት
አድርጎ በትዕግሥት እንደተቀበለው ሰምታ
ችኋል። ትዕግሥቱን ቀጥሮ እግዚአብሔር
ያደረገለትን በጎ ነገርም ታውቃላችሁ። እግ
ዚአብሔር ምሕረትንና ርኅራኄን የተሞላ
አምላክ ነው።
12 ወንድሞቼ ሆይ! ከሁሉም በላይ፥በሰ
ማይ ወይም በምድር ወይም በማናቸውም
ነገር ቢሆን አትማሉ። ንግግራችሁን ማጽ
ናት ስትፈልጉ «አዎን» ወይንም «አይደ
ለም» በሉ እንጂ ፈጽሞ አትማሉ። ከዚህ
ውጪ የምትናገሩት ቃል ኃጢአት ሆኖ የእ
ግዚአብሔርን ፍርድ እንዳያስከትልባችሁ
ተጠንቀቁ።
13 ከመካከላችሁ በመከራ ውስጥ የሚገኝ
ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ ያለው ካለም
ደግሞ ያም እግዚአብሔርን በዝማሬ ያመስ
ግን። 14 የታመመ ቢኖር የቤተ ክርስቲያኒ
ቱን ሽማግሌዎች ወደ ቤቱ ይጥራ። እነር
ሱም በጌታ ስም ዘይት ቀብተው ይጸልዩ
ለት። 15 በእምነት የተደረገ ጸሎትም በሽተ
ኛውን ያድነዋል፤ጌታም ከሕመም አልጋው
ላይ ያስነሣዋል፤ኃጢአት ሠርቶም እንደሆን
ይቅር ይለዋል።
16 ስለዚህ እንድትፈወሱ ኃጢአታችሁን
እርስ በርሳችሁ ተናዘዙ፤አንዱም ለሌላው
ይጸልይለት፤የጻድቅ ሰው ጸሎት ኃይል ስላ
ለው ታላቅ ነገርን ያደርጋል። 17 ኤልያስ
እንደኛ ሥጋ የለበሰ ፍጡር ነበር። ዝናብ
እንዳይዘንብ ከልቡ በጸለየ ጊዜ፥ ለሦስት
ዓመት ተኩል በምድር ላይ ዝናብ ጠብ አላ
ለም። 18 እንዲዘንብ እንደገና በጸለየ ጊዜ
ደግሞ፥ሰማይ ዝናቡን አወረደው፤ምድርም

ፍሬዋን ሰጠች።
19 ወንድሞቼ ሆይ፥ከእናንተ አንዱ ከእ
ውነት መንገድ ቢወጣ ሌላው ወንድም
ወደ እውነተኛው መንገድ ይመልሰው።
20 ይህን የሚያደርግ ወንድም፥ ያን ሰው
ነፍሱ ከሞት እንድትድንና የብዙ ኃጢአቷ
ንም ይቅርታ እንድትቀበል ከስሕተት መን
ገዱ መልሶታል።

የናንተው
ያዕቆብ

# የሐዋርያው ጴጥሮስ የመጀመሪያው መልእክት

## መግቢያ

ሐዋርያው ጴጥሮስ ከመጀመሪያዎቹ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነው። ይህ መልእክት በ63 ዓ.ም. እንደተጻፈ ይገመታል። ሐዋርያው ይህን መልእክት በዚያን ዘመን ጳንጦስ፥ገላትያ፥ቀጳዶቅያ፥ቢታንያ ወዘተ. ተብለው በሚታወቁ፥ዛሬ ግን ከሞላ ጎደል በቱርክ መንግሥት አስተዳደር ሥር በተጠቃለሉ ልዩ ልዩ ግዛቶች፥ተበታትነው ለሚኖሩ የአይሁድ ክርስቲያኖች ጽፎ ሰዶላቸዋል። የመልእክቱ መሠረተ አሳብ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት ለተቀበሉት የእግዚአብሔር ጸጋ እስከ ወዲያኛው የማይጠፋ ተስፋ የሚያድላቸው መሆኑን ማብሠር ነው። ይህም ብቻ አይደለም፤ምዕመናን ስለ ክርስቶስ ብለው መከራና ሥቃይ ሲቀበሉ፥በእሳት ሲቃጠሉ፥ጸጋው በድል አድራጊነት እንደሚያወጣቸው ያስረዳል።

---

## ምዕራፍ 1

1 የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ ከሆነው
ጴጥሮስ፥ በስደት ወጥተው በጳንጦስ፥ በገላ
ትያ፥ በቀጳዶቅያ፥በእስያና በቢታንያ ተበታ
ትነው ለሚኖሩ ክርስቲያኖች የተላከ መልእ
ክት። 2 ወዳጆቼ ሆይ፥ እግዚአብሔር አብ
አስቀድሞ እንዳወቃችሁ መርጧችኋል።
ይህም በእናንተ አድሮ ሥራውን በሚሠ
ራው በመንፈስ ቅዱስ፥ ለኢየሱስ ክርስቶስ
እንድትታዘዙና በደሙ እንድትነጹ ነው።
የተትረፈረፈ ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ።
3 ዳግመኛ ተወልደን ያእግዚአብሔር
ቤተሰብ እንድንሆን፥በኢየሱስ ክርስቶስ ትን
ሣኤ ምክንያት የዘላለምን ሕይወት ተስፋ
እንድናደርግ፥ወሰን በሌለው ምሕረቱ ለዚህ
ያበቃን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት የሆነው
አንድ አምላክ ፥ ስሙ የተባረከ ይሁን።
4 በዚህ ጊዜ ያልፋል በዚህ ጊዜ ይቀራል
የማይባል፥ነውር ነቀፋ የማይገኝበት፥ዋጋው
በወርቅ በብር ሊተመን የማይችል የዘላለም
ሕይወት ለእናንተ በሰማይ ተዘጋጅቶ ይቆያ
ችኋል። 5 እርሱን በማመናችሁም በመጨረ
ሻው ዘመን ሊገለጥ የተዘጋጀውን መንግ
ሥት በይፋ እስክትወርሱ ድረስ በመለኮ
ታዊ ኃይሉ ከማናቸውም ክፉ ነገር ይጠብ
ቃችኋል። 6 በዚች ዓለም ላይ ያለው የሕይ
ወት ጉዳና ለጊዜው አስቸጋሪና ፈተና የሞ
ላበት ቢሆንም እንኳን፥ፍጹም የሆነ ተድ
ላና ደስታ ስለሚጠብቃችሁ በዚህ ደስ ሊላ
ችሁ ይገባል።
7 የወርቅ ጥራቱ የሚታወቀው በእሳት
ከተፈተነ በኋላ ነው። ከወርቅ ይልቅ የከበ
ረች እምነታችሁ ጥራትና ጥንካሬም የሚለ
ካው ፥ በደረሱባችሁ በእነዚህ ፈተናዎች
ነው። ስለዚህ ፈተናዎቹን አልፋችሁ፥በእ
ምነታችሁ ጸንታችሁ ከተገኛችሁ ክርስቶስ
ዳግመኛ በሚመለስበት ጊዜ ከፍ ያለ ምስጋ
ናና ክብር ይጠብቃችኋል።
8 ጌታ ኢየሱስን በዓይነ ሥጋ ሳታዩት
ወዳችሁታል፥አምናችሁበታልም። ይህ በመ
ሆኑም አሁኑኑ እንኳ በቃላት ሊገለጥ በማ
ይችል ሰማያዊ ደስታ ተሞልታችኋል፤
9 ወደ እምነታችሁ ፍጻሜ የሚያደርሳችሁ
ንም የነፍሳችሁን ደኅንነት አግኝታችኋል።
10 ለእናንተ ሊገለጥ ስላለው ጸጋ ነቢያት
ትንቢት ተናገሩ፤እነዚህም ነቢያት ስለዚህ
የመዳን ጸጋ አያሌ ጥያቄዎችን በማንሣት
ሁኔታውን በልባቸው አውጥተው አወረዱ።
11 በእነርሱም አድሮ የነበረው የእግዚአብ

ሔር መንፈስ፥ስለ ክርስቶስ መከራና ይጠብ
ቀውም ስለነበረው ክብር የተናገረው ትን
ቢት ፍጻሜው መቼና እንዴት እንደሆነም
ለማወቅ ጣሩ።
12 በመጨረሻ ግን ይህ ሁሉ ነገር የሚፈ
ጸመው እነርሱ በነበሩበት ዘመን ሳይሆን
በእናንተ ዘመን መሆኑ ተገልጦላቸዋል።
ጊዜው ሲደርስም የምሥራቹ ቃል ይኸው
ለሁላችንም በግልጽ ተሰብኮልናል። የሰበኩ
ልንም ሰዎች ይህን የምሥራች ቃል የተናገ
ሩት ከሰማይ በተላከው በመንፈስ ቅዱስ
አማካይነት ነው። ይህም ነገር የሰማይ መላ
እክት ሳይቀሩ መጨረሻውን ለማወቅ የጓጉ
ለት በመሆኑ ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ነው።
13 ስለዚህ አስተዋዮችና ራሳችሁን ለመቆጣ
ጠር የምትችሉ ሆናችሁ በክርስቶስ ዳግም
ምፅአት ጊዜ የሚገለጠውን የእግዚአብሔ
ርን ቸርነት በተስፋ ተጠባበቁ።
14 ቀድሞ እውነትን ባለማወቅ ታደር
ጉት የነበረውን ክፉ ሥራ ሁሉ ከእንግዲህ
ወዲህ እርግፍ አድርጋችሁ ተዉት። ለእግ
ዚአብሔር መታዘዝን እንደ ልማድ አድርጋ
ችሁ ያዙት። 15 የጠራችሁ እግዚአብሔር
ቅዱስ እንደሆነ እናንተም በአድራጎታችሁ
ሁሉ ቅዱሳን ሁኑ፤ 16 «እኔ ቅዱስ ስለ
ሆንኩ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ» ብሏልና።
17 ሰማያዊ አባታችሁ በአድልዎ የማይፈ
ርድ መሆኑን አስታውሱ። ስለዚህ የሚፈር
ድላችሁም ሆነ የሚፈርድባችሁ በትክክል
በመሆኑ፥ከአሁኑ ጀምሮ በዙፋኑ ፊት እስከ
ምትቀርቡበት ጊዜ ድረስ በፍርሃትና በአክ
ብሮት ኑሩ።
18-19 ከአባቶቻችሁ ከተማራችሁት ከንቱ
የሕይወት ጉዳና እግዚአብሔር መልሶ ያዳ
ናችሁ ዋጋ ከፍሎ ነው። የተከፈለላችሁም
ዋጋ፥እንደምታውቁት የሚጠፋ ብር ወይም
ወርቅ ሳይሆን፥የኃጢአት እድፍና ጉድፍ
ያላረፈበት የእግዚአብሔር በግ የሆነው የክ
ርስቶስ ክቡር ደም ነው። 20 ይህንንም የማ
ዳን ተግባሩን እንዲያከናውን የተመረጠው
ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ሲሆን በዚህ በመ
ጨረሻው ዘመን ግን ስለ እናንተ ተገል
ጧል።
21 ከሞት ባስነሣውና ታላቅ ክብር ባጐና
ጸፈው በክርስቶስ በኩል እግዚአብሔርን
ታምናላችሁ። ስለዚህም እምነታችሁንም
ሆነ ተስፋችሁን በእግዚአብሔር ላይ ጥላች
ኋል ማለት ነው። 22 ለእውነት በመታዘዝ
ራሳችሁን በማንጻታችሁ ለወንድሞቻችሁ
ባገኛችሁት ከልብ የሆነ ፍቅር፥እርስ በእር
ሳችሁ አጥብቃችሁ የምትዋደዱ ሁኑ።
23 እነሆ አዲስ ሕይወት አግኝታችኋል።
ያገኛችሁትም አዲስ ሕይወት ከወላጆቻ
ችሁ በልደተ ሥጋ እንዳገኛችሁት ሕይወት
ከሚጠፋው ዘር ሳይሆን፥ሕያውና ዘላለማዊ
ከሆነው ከማይጠፋው ከእግዚአብሔር ቃል
ነው። 24 መጽሐፍ ይህን አስመልክቶ፥
«ማናቸውም ሰው እንደ ሣር ነው፥ክብሩም
ሁሉ እንደ አበባ ነው። ሣር እንደሚደርቅ
ይደርቃል። አበባ እንደሚረግፍም ይረግ
ፋል። 25 የጌታ ቃል ግን እንደዚህ አይደ
ለም፤ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል» ይላል።
ለእናንተ የተሰበከላችሁም ቃሉ ይኸው
ነው።

## ምዕራፍ 2

1 ከእንግዲህ ክፋትንና ማታለልን፥ማስመ
ሰልንም አስወግዱ። ቅናትና ሐሜትንም
ከእናንተ አርቁ። 2-3 ጌታ ለእናንተ የቱን
ያህል ቸር መሆኑን የቀመሳችሁት ስለሆነ
ደኅንነታችሁ ከፍጹምነት ደረጃ እንዲደ
ርስ፥ሕፃን ወተት ለማግኘት እንደሚጓጓ
እናንተም እንደዚሁ የቃሉን መንፈሳዊ
ወተት ለማግኘት ልትጓጉ ይገባል። 4 እግዚ
አብሔር በእርሱ መሠረትነት ላይ ሕንፃውን
የሚያቆምበት ሕያው ድንጋይ ወደሆነው
ወደ ክርስቶስ ቅረቡ። ክርስቶስ፥ሰዎች
ንቀው የጣሉት እግዚአብሔር ግን ከማንም
በላይ የመረጠውና ያከበረው የማዕዘን ድን
ጋይ ነው።
5 እናንተም እግዚአብሔር ለሚሠራው
መንፈሳዊ ቤት ሕያዋን የካብ ድንጋዮች
ሆናችኋል። እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
መሥዋዕት ታቀርቡ ዘንድም ለክርስቶስ ኢየ
ሱስ ቅዱሳን ካህናት ናችሁ። 6 መጽሐፍ፥
«የመረጥኩትን ክቡር የሆነ የመሠረት ድን
ጋይ በጽዮን አኖራለሁ። እርሱን የሚያምኑ
ትን ሁሉ አላሳፍራቸውም» ይላል።
7 ይህ በመሆኑም ለምታምኑበት ለእና
ንተ ክርስቶስ ክቡር ሲሆን፥ለማያምኑበት
ግን ግንበኞች እንደማይጠቅም ቆጥረው የና
ቁት ድንጋይ ነው። 8 መጽሐፍ፥ «እርሱ
አንዳንድ ሰዎችን የሚያደናቅፍ ድንጋይ፥
አሰናክሎ የሚጥልም ዓለት ነው» ይላል።
ተደናቅፈው የሚወድቁበትም ምክንያት
የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ስለማይታ
ዘዙ ሲሆን መጨረሻቸው ውድቀት መሆ
ኑም የሚያስደንቅ አይደለም።
9 እናንተ ግን እንደዚህ አይደላችሁም።
እናንተ የንጉሥ ካህናት ናችሁ። ይህ

ብቻም አይደለም። ቅዱስና ንጹሕ እንዲ
ሁም የተለየ ወገን አድርጎ ለራሱ የመረጣ
ችሁ ናችሁ። ይህንን ማድረጉም ከጨለማ
ድንቅ ወደ ሆነው ብርሃኑ ያወጣችሁ መሆ
ኑን ለሌሎች እንድትናገሩለት ነው።
10 ቀድሞ እናንተ ወገኖቹ አልነበራችሁም፤
ዛሬ ግን ወገኖቹ ናችሁ። ቀድሞ የእግዚአ
ብሔር ምሕረት አልነበራችሁም። አሁን
ግን መላ ሕይወታችሁ በምሕረቱ ተለውጣ
ለች።

11 ወዳጆቼ ሆይ፤ በዚች ዓለም ላይ የም
ትኖሩት በእንግድነት መሆኑን አትዘንጉ።
እውነተኛይቱ መኖሪያችሁ በሰማይ ስለሆ
ነች ከዚህ ዓለም ከንቱ ደስታ እንድትርቁ
አደራ እላችኋለሁ። ከነፍሳችሁ ጋር ጦርነት
ገጥማ ጥፋት ከምታስከትልባችሁ ክፉ
ምኞት ተጠበቁ።

12 ክርስቶስን ካላመኑ ሰዎች ጋር በምት
ኖሩበት ጊዜ ሁሉ፤ ስለ እናንተ በጎ አመለካ
ከት ባይኖራቸውና ክፉ ነገር ቢያደርጉባ
ችሁ ጠባያችሁ አይለወጥ። በክፉ ፈንታ
ክፉ አትመልሱ። ምክንያቱም ክርስቶስ
እኛን ለመጐብኘት በሚመጣበት ጊዜ መል
ካም አኗኗራችሁን በማስታወስ እግዚአብሔ
ርን ያመሰግኑታልና። 13 ስለ ጌታ ብላችሁ
ማናቸውንም የመንግሥት ሕግ አክብሩ።
ለርዕሰ ብሔሩና ለባለሥልጣኖች ሁሉ
ታዘዙ። 14 በርዕሰ ብሔሩ የተሾሙት አስተ
ዳዳሪዎች፤ የሚያጠፉትን ለመቅጣት የሚያ
ለሙትን ለማስደሰት የተላኩ ስለሆነ ታዘዙ
አቸው። 15 ነገሩን ሳይረዱት በጭፍን ተነ
ሥተው ወንጌልን የሚቃወሙትን ሰዎች
በመልካም አድራጎታችሁ አፋቸውን እንድ
ታስይዟቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።
16 እናንተ ነጻ ሕዝብ ናችሁ። እንዲህ ስለተ
ባለም ክፉ ነገር ለማድረግ የሚያስችል ነጻ
ነት አላችሁ ማለት አይደለም። በማናቸ
ውም ጊዜ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች
ሆናችሁ በነጻነት ኑሩ እንጂ ነጻነታችሁን
የክፋት መሸፈኛ አታድርጉት።

17 ለማንም ሰው የሚገባውን ክብር
ስጡት። ክርስቲያኖችን ሁሉ ውደዷቸው።
እግዚአብሔርን ፍሩ። በሥልጣን ላይ ያለ
ውን መንግሥት አስተዳደር አክብሩ።

18 እናንተ አገልጋዮች ሆይ፤ ለአስተዳዳሪ
ዎቻችሁ ታዘዙ። የምትታዘዙትም ደጎች
ለሆኑት ብቻ ሳይሆን ለክፉዎቹም ጭምር
መሆን አለበት። 19 ደግ ነገር በማድረጋችሁ
መከራ ቢደርስባችሁ እግዚአብሔርን አመስ
ግኑት። 20 ጥፋት አጥፍታችሁ መከራ ደርሶ
ባችሁ ብትታገሡ በዚህ ዋጋ አታገኙበ
ትም። ነገር ግን ጥፋትና በደል ሳይኖርባ
ችሁ መከራ ሲደርስባችሁ በትዕግሥት ብት
ቀበሉት እግዚአብሔርን ደስ ታሰኙታላ
ችሁ።

21 የተጠራችሁትም ስትበደሉና በግፍ
መከራን ስትቀበሉ እንድትታገሡ ነው። ስለ
እናንተ መከራ የተቀበለው ክርስቶስም ዱካ
ውን እንድትከተሉ ምሳሌነቱን ትቶላች
ኋል። 22 አስተውሉ! ክርስቶስ ምንም ዓይ
ነት ኃጢአት አላደረገም፤ በአንደበቱም
ሐሰት አልተገኘበትም። 23 ሲሰድቡት
መልሶ አልተሳደበም፤ ሲያሠቃዩትም ትክክ
ለኛ ፈራጅ ለሆነው አምላክ ውሳኔውን ተወ
ለት እንጂ አልዛተም። 24 እኛ ከኃጢአት
ተለይተን በጽድቅ እንድንኖር እርሱ ራሱ
በሥጋው ኃጢአታችንን በመስቀል ላይ ተሸ
ከመ። እናንተም በእርሱ ቁስል ፈውስን አግ
ኝታችኋል። 25 ከዚህ በፊት ከመንጋው ተለ
ይቶ እንደጠፋ በግ ተቅበዝብዛችሁ ከአምላ
ካችሁ ርቃችሁ ነበር። አሁን ግን ከማናቸ
ውም አደጋ ሊጠብቃችሁ ወደሚችለው የነ
ፍሳችሁ ሁነኛ ጠባቂ ወደ ሆነው ወደ እግ
ዚአብሔር ተመልሳችኋል።

## ምዕራፍ 3

1-2 ሚስቶች ሆይ፤ የማያምኑ ባሎቻችሁ
ስለ ጌታ በምትመሰክሩላቸው ጊዜ ምናልባ
ትም ለመስማት አይፈልጉ ይሆናል። ይሁን
እንጂ በተግባር የሚገለጠው ክርስቲያናዊ
ሕይወታችሁ ከቃላት የበለጠ መናገር ስለ
ሚችል፤ ትሑትና ሰው አክባሪ በሆነው ተወ
ዳጅ ባሕርያችሁ እንዲማረኩ አድርጓቸው።
3 ለሰው በሚታዩ ብልጭልጭ ነገሮች
ለማጌጥ፤ በውድ ዋጋ በተገዙ ልብሶች ለመ
ሽሞንሞን፤ ወይም የጸጉራችሁን አሠራር
በየጊዜው በመለዋወጥ ውጫዊ ውበታችሁን
ለመንከባከብ ይህን ያህል አትጨነቁ።
4 ነገር ግን ውበታችሁ በእግዚአብሔር ፊት
ዋጋው እጅግ በከበረና በማይጠፋ ጌጥ
ማለት በገርነትና በጭምትነት መንፈስ
ያጌጠ ውስጣዊ ውበት ይሁን። 5 እንዲህ
ባለውም ውስጣዊ ውበት በቀድሞ ዘመን
የነበሩ፤ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው፤ የባ
ሎቻቸውን ፈቃድ የፈጸሙ ቅዱሳን ሴቶች
አጊጠውበት አልፈዋል።

6 እዚህ ላይ ሣራን እንደ ምሳሌ አድር
ገን እናንሣት። ሣራ የቤቱ ምሰሶ የነበረውን
ባሏን አብርሃምን ታከብረው፤ ትታዘዘው
ነበር። እናንተም በዚሁ ዓይነት ባሎቻች

ሁን ብታከብሯቸውና ብትታዘዙላቸው በእ
ርሱ እግር ተተክታችሁ ደግ ሥራ መሥራ
ታችሁ ስለሆነ፥በባሎቻችሁ ፊት መሽቆጥቆ
ጥና መርበትበት አይኖርባችሁም።
7 እናንተም ባሎች፥ሚስቶቻችሁ የእግዚ
አብሔርን በረከት ከእናንተ ጋር እኩል የሚ
ካፈሉ ስለሆነ የተፈጥሮ ደካማነታቸውን
በመረዳት ተገቢ የሆነውን ጥንቃቄና እንክ
ብካቤ አድርጉላቸው። ይህን ካደረጋችሁ
ጸሎታችሁ እንዳይደመጥ መሰናክል የሚ
ሆን ነገር ሊያጋጥማችሁ አይችልም።
8 በመጨረሻም፥ ሁላችሁም እርስ በርስ
በመተሳሰብ፥ በቅን ልቦናና በትሕትና ሆና
ችሁ፥ እንደ አንድ ቤተሰብ በመፈቃቀርና
በመስማማት ተዛዝናችሁ ኑሩ። 9 እከሌ እን
ዲህ አድርጎ በድሎኛልና መልሼ ልበድ
ለው፥ አጥቅቶኛልና መልሼ ላጥቃው በማ
ለት በክፉ ፈንታ ክፉ አትመልሱ። ስማች
ሁን እንሥተው በከንቱ ሲያጠፉት፥ ስማች
ንን አጥፍተውታልና እኛም ስማቸውን እን
ሥተን እናጥፋው የሚል መንፈስ አይደርባ
ችሁ። ይልቁንስ እነዚህ ሰዎች እንዲህ
ካለው መጥፎ ባሕርይ እንዲገላገሉ ልትጸል
ዩላቸው ይገባል። የእግዚአብሔርን በረከት
የምንቀበለው ለሚፈጽሙብን በደል አጸፋ
ውን በመመለስ ፈንታ በደግነት መንፈስ
ተመልከተን መልሰን በጎ ስናደርግ ነው።
10 ስለዚህ፥ደስ ብሏችሁ መኖር እንድትችሉ
መልካምንም ዘመን እንድታዩ አንደበታች
ሁን ተቆጣጠሩት ፤ ሐሰትንም አትናገሩ።
11 ከክፉ ነገር ሽሹ፥ መልካሙን ግን አድ
ርጉ። ከሰዎች ጋር በሰላም ተግባብታችሁ
ኑሩ። ሁልጊዜም ሰላምን የምትፈጥሩ ሁኑ።
12 ምክንያቱም እግዚአብሔር ልጆቹን ይመ
ለከታቸዋል፥ጸሎታቸውንም ይሰማል። የእግ
ዚአብሔር የቁጣ ፊት ግን በክፉ አድራጊ
ዎች ላይ ነው።
13 መልካም ነገር ለማድረግ በምትነሡ
በት ጊዜ የሚጐዳችሁ ማን ነው? 14 መል
ካም ነገር አደረጋችሁ በማለት መከራ ቢያ
ደርሱባችሁ ግን፥ጌታ ዋጋችሁን ይከፍላችኋ
ልና ብሩካን ናችሁ። 15 ጌታችሁን ኢየሱስ
ክርስቶስን ከልባችሁ አክብሩት። ስለ እምነ
ታችሁ የሚጠይቃችሁ ካለም፥ጭምት በሆ
ነና ትሕትና በተመላበት መንፈስ ተገቢውን
መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሁኑ።
16 ምን ጊዜም ቢሆን በጎ ሕሊና ይኑራ
ችሁ። በክርስቶስ ኢየሱስ ያላችሁን መል
ካም ጠባይ ሰዎች ቢቃወሙና ስማችሁን
ቢያጠፉት፥የኋላ ኋላ እውነቱ ሲወጣ ማፈ
ራቸው የማይቀር ነው። 17 የእግዚአብሔር
ፈቃድ ቢሆን ግን፥በደል ሠርቶ መከራ ከመ
ቀበል ይልቅ፥መልካም ሥራ ሠርቶ መከራ
መቀበሉ ይመረጣል። 18 ክርስቶስ ታዲያ
መከራ የተቀበለው ኃጢአት ሠርቶ፥በደል
ፈጽሞ አይደለም። እርሱ ግን እኛን ለማዳ
ንና ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርበን፥አንድ
ጊዜ ለሁላችን ኃጢአት ሞተ። በሥጋ ሞተ
በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ግን ተመልሶ
ሕያው ሆነ። 19 በመንፈስም ወደ ሲኦል
ወርዶ በዚያ ለሚገኙ ነፍሳት ሰበከላቸው።
20 እነዚህ በሲኦል የነበሩ ነፍሳትም ቀድሞ
ኖኅ መርከብ ሲሠራ እግዚአብሔር ንስሐ
እንዲገቡ ጊዜ ሰጥቶ በትዕግሥት ይጠባበቃ
ቸው የነበሩ ሰዎች ነፍሳት ናቸው። እነርሱ
ግን በእምቢተኛነታቸው ጸኑ እንጂ ቃሉን
ሊቀበሉ አልፈለጉም። ታዲያ በዚያን ጊዜ
እምቢተኞቹ ሲጠፉ በመርከቧ ውስጥ ገብ
ተው ከጥፋት ውኃ የዳኑት ስምንት ሰዎች
ብቻ ነበሩ።
21 ይህም ውኃ የጥምቀትን ምንነት በም
ሳሌነቱ ያሳየናል። በጥምቀትም ከሞትና
ከኩነኔ በክርስቶስ ትንሣኤ መዳናችንን እን
መሰክራለን። ይህም ጥምቀት ሰውነትን
በውኃ ታጥቦ ከእድፍ ማንጻት ማለት ሳይ
ሆን፥በንስሐ ከኃጢአት በነጻ ሕይወት በበጎ
ሕሊና ለመገኘት እግዚአብሔርን መማጠን
ማለት ነው።
22 ክርስቶስ ወደ ሰማይ ወጥቶ በእግዚአ
ብሔር አብ ቀኝ በክብር ተቀምጧል። በዚ
ያም መላእክትና ኃይላት ፥ ሥልጣናትም
ሁሉ ይሰግዱለታል፤ይታዘዙለታልም።

## ምዕራፍ 4

1-2 ክርስቶስ በሥጋው መከራ የተቀበለ
ስለሆነ እናንተም መከራን ለመቀበል የተዘ
ጋጃችሁ ሁኑ። መከራ በምትቀበሉበትም
ጊዜ ኃጢአት ሊሰለጥንባችሁ ስለማይችል
ዕድሜ ልካችሁን በክፉ ምኞት ስትቃጠሉ
አትኖሩም። አሳባችሁም ምኞታችሁም የእ
ግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ቆርጦ የተ
ነሣ ይሆናል። 3 በጌታ ከማመናችሁ በፊት
ስታመነዝሩ፥በፍትወተ ሥጋ ስትቃጠሉ፥
ስትሰክሩ፥ዳንኪራ ስትረግጡ፥ልዩ ልዩ ጣዖ
ታትን ስታመልኩ ፥ ሌላም ሌላም የክፉ
ኃጢአት ስትሠሩ ያሳለፋችሁት የዓለማዊ
ነት ዘመን ይበቃል።
4 መቼም ይህን ሁሉ የኃጢአት መንገድ
እርግፍ አድርጋችሁ ስትተዉት፥በቅብጠቱ
ጊዜ ቀድሞ የሚያውቋችሁ ወዳጆቻችሁ

በክፉ አድራጎታቸው ባለመተባበራችሁ
መሳቂያ መሳለቂያ እንደሚያደርጓችሁ፥እን
ደሚንቋችሁና እንደሚያንቋሽሿችሁ የታ
ወቀ ነው። 5 ነገር ግን በሕያዋንና በሙታን
ላይ የሚፈርድ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ የሥ
ራቸውን ዋጋ የሚያገኙ መሆኑን አትርሱ።
6 የወንጌል ቃል ለሙታን እንኳን ሳይቀር
የተሰበከላቸው ለዚህ ነው። እንደማንኛውም
ሰው በሥጋ ለሠሩት ሁሉ እንዲፈረድባ
ቸው፤በመንፈስ ግን እንደ እግዚአብሔር
ሕያው ባሕርይ ዘላለማዊ ሆነው መኖር እን
ዲችሉ ነው።

7 የዓለም ፍጻሜ እየተቃረበ በመምጣቱ
ተግታችሁና ነቅታችሁ መጸለይ እንድት
ችሉ፥ራሳችሁን በመቆጣጠርና በማስተዋል
ኑሩ። 8 ፍቅር የሰውን ብዙውን ኃጢአት
መሸከም ስለሚያስችል፥ ከሁሉም በላይ
እርስ በርሳችሁ ከልብ ተፋቀሩ። 9 ያለመሰ
ልቸት እንዳችሁ ሌላውን በደስታ በቤታ
ችሁ ውስጥ አስተናግዱ።

10 እግዚአብሔር በጸጋው ለያንዳንዳችሁ
ልዩ ልዩ ስጦታዎችን አድሎአችኋል። ስለ
ዚህ እንዱ የሌላውን ሕይወት በመገንባት
የእግዚአብሔርን በረከት በሚያስገኝ መን
ገድ የተቀበለውን የመንፈስ ስጦታ በሚገባ
ጥቅም ላይ ያውል። 11 የሚያስተምር እግዚ
አብሔር በእርሱ አንደበት ቃሉን እንደሚና
ገር አድርጎ በመቁጠር ያስተምር። ለመር
ዳት የተጠራም እግዚአብሔር በሚሰጠው
ኃይልና ጉልበት ሁሉ ሌሎችን ከመርዳት
ወደ ኋላ አይበል። እናንተ ይህን በምታደር
ጉበት ጊዜ እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስ
ቶስ አማካይነት ይመሰገንበታል። ክብርና
ሥልጣን ከዓለም እስከ ዘላለም ድረስ ለእ
ርሱ ይሁን፤አሜን።

12 ወዳጆቼ ሆይ፤የሚደርስባችሁ ማናቸ
ውም መከራና ፈተና በእናንተ ላይ ብቻ
የመጣና ያልተለመደ ነገር ሆኖ ሊያስደንቃ
ችሁ አይገባም። 13 ይልቁንስ ለዚህ ዕድል
በቅታችሁ የክርስቶስ የመከራው ተካፋዮች
በመሆናችሁ ደስ ሊላችሁ ይገባል። ምክንያ
ቱም በዚህ ዓለም የመከራው ተካፋዮች
በመሆናችሁ፥እርሱ በሚገለጥበት ጊዜ የክ
ብሩ ተካፋዮች ትሆናላችሁና።

14 ክርስቲያን በመሆናችሁ ቢረግሟች
ሁም ሆነ ቢሰድቧችሁ ደስ ይበላችሁ እንጂ
አይከፋችሁ። ምክንያቱም በሚረግሟች
ሁም ሆነ በሚሰድቧችሁ ጊዜ የጌታ መን
ፈስ በእናንተ ላይ በክብር ይገለጣልና።
15 መከራ ቢደርስባችሁ፥ በነፍሰ ገዳይነት፥
በሌብነት፥ በወንጀለኛነት፥ ወይም በሰው
ነገር ጣልቃ ገብነት ምክንያት ሊሆን አይገ
ባም። 16 በተረፈማ ክርስቲያን በመሆናችሁ
መከራ ብትቀበሉ ምን ያሳፍራል? ይልቁ
ንም የክርስቶስ ቤተሰብ ለመሆን ስለተመረ
ጣችሁና በዚህ በተከበረ ስም ለመጠራት
ስለበቃችሁ አመስግኑት። 17 ፍርድ የሚጀ
መርበት ጊዜ ቀርቧል። ፍርዱ የሚጀመረ
ውም በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ይሆናል።
ታዲያ ፍርድ የሚጀመረው ከእኛ ከክርስቲ
ያኖቹ ከሆነ፥በጌታ ያላመኑትማ የሚጠብቃ
ቸው ፍርድና ቅጣት የቱን ያህል ይሆን?
18 ጻድቅ በጭንቅ የሚድን ከሆነ፥ ኃጢአተ
ኛውማ እንዴት ሊሆን ይሆን?

19 ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ
መከራን የሚቀበሉ ሁሉ ለፈጠራቸው የታ
መነ አምላክ ራሳቸውን አደራ በመስጠት
በበጎ ሥራቸው ወደ ፊት ይግፉበት።

## ምዕራፍ 5

1 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ለሆናች
ሁት አንዲት ቃል ላሳስባችሁ እወዳለሁ።
እኔም እንደ እናንተው የቤተ ክርስቲያን
ሽማግሌ ስሆን፥የክርስቶስ መከራና ሥቃይ
ምስክር ነኝ። ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜም
የክብሩና የምስጋናው ተካፋይ እንደምሆ
ንም አውቃለሁ። እንግዲህ አደራ የምላ
ችሁ፥ 2 በእናንተ ኃላፊነት ሥር ያሉትን፥
የእግዚአብሔር መንጋ የሆኑ ምዕመናንን
ተግታችሁ እንድትጠብቋቸው ነው። የምት
ጠብቋቸውም፥ግዴታን ለመወጣት ሳይሆን
በፈቃደኝነት፥ ሥጋዊ ጥቅምን ለማግኘት
ሳይሆን ጌታን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላ
ጎት መሆን አለበት።

3 በላያቸው በመሠልጠን ሳይሆን መል
ካም ምሳሌነታችሁን አይተው እንዲከተሏ
ችሁ አድርጓቸው። 4 ይህን ብታደርጉ የእረ
ኞች አለቃ የሆነው ክርስቶስ በሚገለጥበት
ጊዜ፥ዘላለማዊውን የክብር አክሊል ትሸለማ
ላችሁ።

5 ጐልማሶች ሆይ! ከእናንተ በዕድሜ
ከፍ ያሉትን አዛውንት በሚገባ ታዘዙ።
ትንሹ ለትልቁ ትልቁም ለትንሹ ትሕትናን
ያሳይ። ይህንንም ለማለት የበቃሁት እግዚአ
ብሔር ለትሑታን ልዩ በረከትን የሚያድላ
ቸው፥ ትዕቢተኞችን ግን የሚያዋርዳቸው
በመሆኑ ነው። 6 ራሳችሁን ከኃያሉ የእግዚ
አብሔር ክንድ ሥር በትሕትና ዝቅ ዝቅ
ብታደርጉ፥እርሱ በወሰነው ጊዜ ከፍ ከፍ
ያደርጋችኋል።

7እግዚአብሔር ስለሚያስብላችሁና የሚ
ያስፈልጋችሁም ነገር እንዳይጓደል ስለሚጠ
ነቀቅላችሁ፥የሚያስጨንቃችሁንና የሚያሳስ
ባችሁን ማናቸውንም ነገር ሁሉ ሙሉ
ለሙሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።
8ዋናው ጠላታችሁ ዲያብሎስ ተርቦ
እያገሳ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያ
ደባ አንበሳ በዙሪያችሁ እያንጃበበ ነውና
እንዳይነጥቃችሁ ተጠንቀቁ።
9ዲያብሎስ በሚዋጋችሁ ጊዜ በእምነት
ጸንታችሁ ተቋቋሙት እንጂ አትሸነፉለት።
ይህም ፈተና በእናንተ ላይ ብቻ የሚደርስ
እንዳይመስላችሁ። በዓለም ላይ ባሉ ክርስቲ
ያኖች ሁሉ ላይ የሚደርስባቸው መሆኑን
ተረድታችሁ፥ ጌታ ድሉን እንዲሰጣችሁ
በመታመን ዲያብሎስን ተቃወሙት።
10በክርስቶስ ኢየሱስ ለዘላለም ክብር
የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ እግዚአብ
ሔር፥ ለጥቂት ጊዜ መከራ ከተቀበላችሁ
በኋላ፥እርሱ ራሱ ይጐበኛችኋል፥ያጠነክራ
ችኋል፥ጸንታችሁ እንድትቆሙም ያደርጋች
ኋል። 11ኃይልና ሥልጣን ከዘላለም እስከ
ዘላለም ድረስ ለእርሱ ይሁን። አሜን!
12በጣም ታማኝ ነው ብዬ በማምነው
በወንድም ስልዋኖስ እጅ ይህንን መልእክት
ልኬላችኋለሁ። የእግዚአብሔር በረከት የሚ
ገኝበትን መንገድ በመዘርዘር በዚህ ደብዳ
ቤዬ እንዳበረታታኋችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።
የሰጠኋችሁ ምክር ሁሉ በእውነተኛው የእ
ግዚአብሔር ጸጋ ላይ ጸንታችሁ እንድት
ቆሙ ይጠቅማችኋል።
13እንደእናንተው በእግዚአብሔር የተመ
ረጡት፥ በጌታ ወገኖቻችሁ የሆኑት በባቢ
ሎን (ሮም) ያሉት ክርስቲያኖች ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል። ልጄ ማርቆስም ሰላምታ
ያቀርብላችኋል። 14በክርስቲያናዊ ፍቅር
እርስ በእርሳችሁ በመሳሳም ሰላምታ ተሰ
ጣጡ።
በጌታ ውስጥ ላላችሁ ሁሉ ሰላም ይብዛ
ላችሁ።

ወንድማችሁ
ጴጥሮስ

# የሐዋርያው ጴጥሮስ ሁለተኛው መልእክት

## መግቢያ

ሐዋርያው ጴጥሮስ ይህንን መልእክት የጻፈው በ64 ዓ.ም. በሰማዕትነት ከማረፉ ቀደም ሲል ነው። መልእክቱ አይሁድንና አሕዛብን ያጠቃልላል። የወንጌል ቃል ስሕተትና ግድፈት የማይገኝበት የእውነት ቃል መሆኑን ሐዋርያው በመልእክቱ አማካይነት በሚገባ ያስረዳል። እንደዚሁም ምዕመናን ከሐሰተኞች መምህራን እንዲርቁ ያስጠነቅቃቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በመቃኘት፥ስለ መጨረሻው ዘመን ትንቢት አዘል ቃላትን በመልእክቱ ውስጥ አስፍሯል። ምዕመናን በጥበብና በጸጋ እንዲጐለምሱም አበክሮ ያሳስባል።

---

## ምዕራፍ 1

1የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና ሐዋርያ
ከሆነው ከስምዖን ጴጥሮስ በክበረው እምነት
ከእኛ ጋር አንድ ለሆናችሁት ሁሉ የተላከ።
ይህንንም እምነት ያገኛችሁት አምላካችንና
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው
የጽድቅ ሥራ ነው።
2የእግዚአብሔር ርኅራኄና ሰላም እንዲ
በዛላችሁ እርሱንና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶ
ስን በበለጠ እንድታውቁ የሚያበቃችሁን
እውቀት መገብየት ይኖርባችኋል። 3በክብ
ሩና በቸርነቱ የጠራንን እርሱን በማወቃ
ችን፥ ለመንፈሳዊ ሕይወትና ኑሮ የሚያስፈ
ልገንን ማናቸውንም ነገር ሁሉ በመለኮታዊ
ኃይሉ ሰጥቶናል። 4የመለኮታዊ ባሕርይ
ተካፋዮች እንድንሆንም የተትረፈረፈ ስጦ
ታውንና ድንቅ በረከቱን ሊያድለን ታላላ
ቅና ውድ ተስፋዎችን ሰጥቶናል። ይህም
መለኮታዊ ኃይል ከፈቃደ ሥጋ ምኞትና
በአካባቢያችሁ ካለው የዓለም ብልሹ ሕይ
ወት እንድትጠበቁ የሚያስችላችሁ ነው።
5እነዚህን ስጦታዎች ለመቀበልም፥በቅ
ድሚያ በእምነት ላይ ጨምራችሁ ደግነትን

ገንዘብ አድርጉ። ይህ ብቻም አይበቃም።
እግዚአብሔርን በበለጠ ለማወቅ ትጉ።
6 ይህንንም እያደረጋችሁ ራሳችሁን የምትቆ
ጣጠሩና ታጋሾች ሁኑ። በትዕግሥትም ላይ
ጨምሮ እግዚአብሔርን የመምሰል ሕይወት
ይብዛላችሁ። 7 እርስ በርስ ለመተሳሰብ በሚ
ያበቃችሁ በዚህ እግዚአብሔርን በመምሰል
ሕይወታችሁ ላይ ፍቅርን ጨምሩ። 8 እነ
ዚህ ነገሮች በየጊዜው ቢበዙላችሁና በሙ
ላት ቢኖሩባችሁ፥ ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ
ማወቅ ትደርሳላችሁ፤ ፍሬ ታፈራላችሁ፤
ጠቃሚዎችም ትሆናላችሁ። 9 እነዚህን ነገ
ሮች መከታተል የተሣነው ሰው ግን መንፈ
ሳዊ ዓይኖቹ የታወሩ፤ አርቆ ማየት የማይ
ችል፥ ጌታ ከቀድሞ ኃጢአቱ እንዳነጻውም
የዘነጋ ሰው ነው።
10 ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ፤እግዚአብሔር
ከጠራችሁና ከመረጣችሁ ወገን መሆናች
ሁን ለማረጋገጥ ከምን ጊዜውም ይልቅ የበ
ለጠ ትጋት አሳዩ። እነዚህን ነገሮች ሁሉ
ካደረጋችሁ ልትሰናከሉ አትችሉም። 11 በዚ
ህም ዓይነት ዘላለማዊት ወደ ሆነችው ወደ
ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
መንግሥት ለመግባት እንድትችሉ በሩ
ወለል ብሎ ተከፍቶ ይጠብቃችኋል።
12 ምንም እንኳ እነዚህን ነገሮች የምታ
ውቋቸው ቢሆንና ባወቃችሁትም እውነት
ያላችሁ መሠረት የጸና ቢሆን፥ ደግሜ ደጋ
ግሜ ከማሳሰብ ችል የምል ሰው አይደለ
ሁም። 13-15 በዚች ምድር ላይ በሕይወተ
ሥጋ የምቆየው ለአጭር ጊዜ ነው። በቅርቡ
ከዚህ ዓለም በሞት እንደምለይ ጌታ ኢየ
ሱስ ክርስቶስ ራሱ ገልጾልኛል። በየጊዜው
የምልክላችሁ ማሳሰቢያ ልባችሁ ውስጥ
ሥር ሰዶ፥እኔ ከሞትኩ በኋላም እንኳ ስታ
ስታውሱት እንድትኖሩ፥ ካሁኑ እናንተን
ከመጐትጐት ወደ ኋላ አልልም።
16 ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ኃይልና
ስለ መምጣቱ የነገርናችሁ፥ እውነተኛ
ታሪክ እንጂ «ተረት ተረት» ወይም የልብ
ወለድ ፈጠራ እንዳይመስላችሁ። 17-18 በተ
ቀደሰው ተራራ ላይ በክብሩ ብርሃን በተገ
ለጠ ጊዜ በሥፍራው ተገኝተን መለኮታዊ
ግርማ የተሞላውን ድምፅ እግዚአብሔር
ከሰማይ ሲያስተጋባ ሰምተናል። «በእርሱ
ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው»
በማለት ከገናናው ክብር ምስክርነት በመጣ
ለት ጊዜ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር
አብ ክብርና ምስጋናን ተቀብሏል።
19 ስለዚህም ነቢያት የተናገሩለት ትን
ቢት ትክክል መሆኑን አረጋግጠናል። እናን
ተም እነዚህኑ እነርሱ የጻፏቸውን ነገሮች
ሁሉ በጨለማ ውስጥ እንደሚያበሩ ፋና
ዎች በጥንቃቄ ልትጠብቋቸው ይገባል።
ምክንያቱም ቃሎቻቸው በጨለማ ውስጥ
እንደሚያበሩ ፋናዎች ብርሃን ካልሰጡን፥
ነገሮችን ለመረዳት የምናደርገው ሙከራ
ሁሉ በጨለማ እንደ መደነባበር ይቆጠራ
ልና። አስደናቂ የሆነውን የነቢያትን ቃል
እውነተኝነት በጥንቃቄ በምታስተውሉበት
ጊዜ ጨለማው ሥፍራውን ለብርሃን ይለ
ቃል፥ አጥቢያ ኮከብ የሆነው ኢየሱስ ክርስ
ቶስም ዓይን ልቦናችሁን ያበራላችኋል።
20-21 በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገ
ኘው ትንቢት ማንም በራሱ ፈቃድ ተነሣ
ስቶ ከአሳቡ ያፈለቀው የፈጠራ ድርሰት
አይደለም። በሰዎች አድሮ እውነተኛውን
የእግዚአብሔርን ቃል እንዲናገሩ ያደረጋ
ቸው ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው።

## ምዕራፍ 2

1 በቀድሞ ዘመን ሐሰተኞች ነቢያት እን
ደነበሩ ሁሉ ዛሬም ሐሰተኞች መምህራን
በመካከላችሁ ይነሣሉ። ሐሰቱን እውነት
እያስመሰሉ በማቅረብ ስለ እግዚአብሔር
የተሳሳተ ትምህርት ያስተምራሉ። በደሙ
የገዛቸውንም ጌታ ይቃወሙታል። ይሁን
እንጂ መጨረሻቸው አያምርም፤ድንገተኛና
አሠቃቂ መከራ ይመጣባቸዋል። 2 ‘ኃጢ
አት መሥራት የሚያስፈርደው እምኑ ላይ
ነው?’ ብለው በማስተማር ነውረኛ ሥራቸ
ውን ብዙዎች እንዲከተሉ አድርገዋል።
ይህን በማድረጋቸውም ክርስቶስንና ያስተማ
ረውን የእውነት ትምህርት ጭምር አዋርደ
ዋል።
3 እንደ እነዚህ ያሉ አስተማሪዎች ገንዘባ
ችሁን ለመዝረፍ ሲሉ የማይቀባጥሩት
ታሪክ የለም። ነገር ግን የሚገባቸውን
ፍርድ ከብዙ ጊዜ በፊት እግዚአብሔር
ራሱ የወሰነ በመሆኑ፥ ጥፋታቸው እየተቃ
ረበ በመምጣት ላይ ይገኛል። 4 እግዚአብ
ሔር ኃጢአት ለሠሩት መላእክት እንኳ
አልራራላቸውም። ጥፋተኞች ሆነው ስለተ
ገኙም የመጨረሻውን ፍርዳቸውን እስኪቀ
በሉ ድረስ ታሥረው በገሃነም ጨለማ እንዲ
ቆዩ አድርጎቸዋል። 5 በጥንት ዘመን የጥፋት
ውኃ በምድር ላይ ከመድረሱ በፊት ‘አስ
ረሽ ምቺው’ ይሉ የነበሩትን አመፀኞች
ሰዎች ራርቶ አልተዋቸውም። ኃጢአት
ሠርተው ያሳዘኑትን ሁሉ ጻር እስከ ጻር

በጥፋት ውኃ አጥለቅልቆ አጥፍቶአቸዋል።
በዚያን ጊዜ ከዚህ መዓት ሊተርፍ የቻለው
የጽድቅን መልእክት ይሰብክ የነበረው
ኖኅና ሰባት ቤተሰቡ ብቻ ነበሩ። 6የሰዶ
ምና የገሞራ ሕዝቦች እንደዚሁ ኃጢአት
ሠርተው ጌታን ባሳዘኑት ጊዜ ከነከተሞቻ
ቸው በእሳት አጋይቶ ከምድር ገጽ አጥፍቶ
አቸዋል። በተከታታይ የሚነሣውም ትው
ልድ ይህን አይቶ በእነርሱ የደረሰው ጥፋት
እንዳይደርስበት በመፍራት፥በኃጢአት እን
ዳይወድቅ ከክፉ ሥራ እንዲርቅ፥ያን ጊዜ
የተቃጠሉት የእነዚህ ከተሞች የአመድ
ቁልል ሲያሳስበው እንዲኖር አድርጓል።

7-8በዚያን ዘመን በሰዶም ላይ ከወረደው
ከዚያ መዓት ውስጥ እግዚአብሔር አንድ
ሰው አውጥቷል። ያም ሰው ሎጥ ይባላል።
ሎጥ በአካባቢው በየዕለቱ የሚፈጸመውን
ክፉ ሥራ በማየት ሲያዝን፥ሲተክዝ የኖረ
ጻድቅ ሰው ነበር። 9ጌታ ዛሬም በእርሱ
የሚያምኑትን ከመከራና ከፈተና ሁሉ ልክ
እንደዚሁ ያወጣቸዋል። ኃጢአተኞች ግን
የመጨረሻይቱ የፍርድ ቀን እስክትደርስ
ድረስ በዚች ዓለም ላይ ቅጣታቸውን ሲቀ
በሉ ይኖራሉ። 10በተለይም፥ለፈቃደ ሥጋ
ቸው በመገዛት የፍትወተ ሥጋ ፍላጎታ
ቸው የሚረካበትን መንገድ የሚያውጠነጥኑ
ትንና መንፈሳውያን ሥልጣናትን የሚንቁ
ትዕቢት የወጠራቸውን ደፋሮች፥በቀላሉ
የሚያልፋቸው አይደለም። 11መቼም በእግ
ዚአብሔር ፊት የሚቆሙ መላእክት በኃይ
ልም ሆነ በሥልጣን ከሐሰተኞቹ መምህ
ራን እንደሚበልጡ ጥርጥር የለውም።
ሆኖም እነዚህ መላእክት እንኳ በሥልጣ
ናቱ ላይ የዘለፋ ቃል ደፍረው የሚናገሩ
አይደሉም።

12ሐሰተኞቹ መምህራን ግን በወጥመድ
ተይዘው ለመገደል እንደሚወሰዱ አእምሮ
እንደሌላቸው የዱር እንስሳት ናቸው። በተ
ፈጥሮ ስሜት ብቻ የሚመሩ ስለሆነ፥አጥር
ተው በማያውቁት ነገር ላይ አፋቸውን ለስ
ድብ ያሾሉታል። በዚህም ምክንያት እነዚህ
ሐሰተኞች መምህራን እንደዱር እንስሳት
በክፉ ሥራቸው ወጥመድ ተይዘው ይጠ
ፋሉ።

13እንዲህ ያለውን የረከሰ ሕይወት እንደ
ልማድ አድርገው በየዕለቱ ሲፈጽሙት በመ
ኖራቸውም ለዚሁ ተገቢ የሆነውን ቅጣት
ይቀበላሉ። ባንድ በኩል አልታወቀብንም
በማለት ይህን የመሰለ የረከሰ ሕይወት በመ
ኖራቸው እናንተን ሲያታልሏችሁ፥በሌላ
በኩል ደግሞ ጨዋ መስለው በፍቅር ማዕዳ
ችሁ ላይ በመገኘታቸው አስነዋሪ ተግባር
ፈጽመዋል፥ማሕበራችሁንም በክለውታል።
14ቅንዝረኛ ዓይናቸው በሴት ላይ አንድ
ጊዜ ከተተከለ ስለማይነቀል ዘወትር ያለማቋ
ረጥ ኃጢአት ይሠራሉ። ባጭሩ የዝሙት
ፍቅር ያሳበዳቸውና የዋህ ሴቶችን በቀላሉ
ለማታለል የሚችሉ ናቸው። ሰውነታቸው
ሥራዬ ብሎ ስስታምነትን እንዲለማመድ
ያደርጉታል። ፍርድ የሚጠብቃቸው የተረ
ገሙ ሰዎች ናቸው። 15የገንዘብ ፍቅር
ዓይነ ሕሊናውን አሳውሮ ክፉ ሥራ እንዲ
ሠራ እንደ ገፋፋው እንደ በለዓም—የባሶር
ልጅ—ቀጥተኛውን መንገድ ስተው፤በእርሱ
ክፉ ጐዳና ሄደዋል። 16ነቢዩን በለዓምን
ግን፥ ስለተሳሳተ አድራጎቱ የማትናገረው
አህያ በሰው ቋንቋ ወቅሳው፥በዕውርነት
ከመነዳት አግዳዋለች።

17እነዚህ ሰዎች ግን ውኃ እንደሌለባ
ቸው ምንጮች ጥቅም የማይሰጡ ናቸው።
በሌላም አነጋገር ኃይለኛ ነፋስ ሳያቋርጥ
ከቦታ ወደቦታ እንደሚነዳው ደመና ናቸው
ማለት ነው። ጥቅም የማይሰጡ፥ለጥፋት
የተመደቡ ስለሆኑ ድቅድቅ ጨለማ ይጠብ
ቃቸዋል። 18ደግሞ እንደ ትልቅ ሙያ ቆጥ
ረው፥በኃጢአታቸውና በነውር ሥራቸው
ይመኩበታል። ከዚህ ብልሹ ሕይወት ያመ
ለጡትንም እንደገና ወደዚያው አግባብቶ
ለመመለስ የማያደርጉት ነገር የለም።

19እነርሱ ራሳቸው የኃጢአት ተገዢ
ዎች ሆነው ሳሉ፥ሌሎችን፥ 'ነፃ ትወጣላ
ችሁ' እያሉ የማይጠቅም ተስፋ ይሰጣሉ።
'ከሕግና ከሥርዓት ነፃ ትወጣላችሁ' እያሉ
ሌሎችን የሚመክሩት እነዚህ መምህራን፥
ራሳቸው የኃጢአትና የጥፋት ተገዢዎች
ናቸው። 20ስለጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ
መድኃኒትነት አውቀው ከዓለም ርኩሰት
ከወጡ በኋላ እንደ ገና ተሰነካክለው ቢወድ
ቁና ለኃጢአት ተገዢዎች ቢሆኑ፥ከቀድ
ሞው ያለማመን ሕይወታቸው ይልቅ የኋለ
ኛው የክህደት ሕይወታቸው የከፋ ይሆ
ናል። 21በሌላ አነጋገር፥ጌታን ካወቁ በኋላ
የተቀደሰ ትእዛዙን ንቀውና አቃልለው እን
ደገና ለኃጢአት ተገዢዎች ከሚሆኑ
ይልቅ፥ ቀድሞውኑ ክርስቶስን ሳያውቁት
ቢቀሩ ይሻል ነበር ማለት ነው። 22በእነር
ሱም የተፈጸመው፥ «ውሻ ወደ ትፋቱ
ይመለሳል፤ አሳማም ታጥቦ እንደገና ማጥ
ውስጥ ይዘፈቃል» የሚለው የጥንት ምሳሌ
ነው።

## ምዕራፍ 3

1-2 ወዳጆቼ ሆይ፤ይህ ሁለተኛ ጊዜ የጻ
ፍኩላችሁ ደብዳቤዬ መሆኑ ነው። በሁለ
ቱም መልእክቶቼ፣ከዚህ በፊት ቅዱሳን ነቢ
ያት የተናገሩትን ቃልና በሐዋርያቶቻችሁ
አማካይነት የተማራችሁትን የጌታችን የመ
ድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ፣
እያስታወሳችሁ እንድትነቃቁ ጽፌላችኋ
ለሁ።
3 በእውነት ላይ የሚያሾፉ፣የሚያፌዙ፣
የራሳቸውን ክፉ ምኞት የሚከተሉ ዋዘ
ኞች፣በመጨረሻው ዘመን እንደሚነሡ አስ
ቀድሜ ላስጠነቅቃችሁ እፈልጋለሁ።
4 «'ኢየሱስ ዳግም እመጣለሁ' ብሎ ተስፋ
ገብቶልናል ትላላችሁ። ታዲያ የታል የመ
ጣው? እንዲያው እናንተ 'ይመጣል' ትላላ
ችሁ እንጂ እርሱ እንደሆን አይመጣም፤
ዘበት ነው! ማንም እንደሚያውቀው ዓለም
ከተፈጠረበት ጊዜ አንሥቶ ምንም ነገር ከቦ
ታው ንቅንቅ አላለም!» እያሉ የተወላገደ
ክርክር ያቀርባሉ።
5-6 ይህን የተሳሳተ አሳብ ሲሰነዝሩ ግን፣
እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማያትን በቃሉ
ብቻ ከፈጠረና ምድርንም በውቅያኖሶች
እንድትከበብ ካደረጋት በኋላ የጥፋት ውኃ
አምጥቶ የዓለምን ሕዝብ ያጠፋ መሆኑን
የተረዱት አይመስልም። 7 ከዚህም ሌላ፣
ጌታ በኃጢአተኞች ላይ በሚፈርድበት በዚ
ያች ዕለት ሰማይና ምድር በእሳት እንዲጋዩ
እግዚአብሔር በቃሉ የወሰነባቸው መሆኑን
ዘንግተውታል።
8 ወዳጆቼ ሆይ፤በእግዚአብሔር ዘንድ
አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፣ ሺውም
ዓመት እንደ አንድ ቀን መሆኑን ይህን
አንድ ነገር አትርሱ። 9 የጌታ ዳግም ምፅ
አት የዘገየ መስሎ ቢታይም፣አንዳንዶች እን
ደሚሉት ይቀራል ማለት አይደለም። ምክን
ያቱም፣ጌታ የተናገረውን የተስፋ ቃል ከመ
ፈጸም አይዘገይም! የዳግም ምፅአቱ የዘገ
የው ግን ማናችሁም እንድትጠፉ እግዚአብ
ሔር ስለማይፈልግ በቂ የንስሐ ጊዜ እንዲኖ
ራችሁ ትዕግሥቱን ሲያሳያችሁ ነው።
10 ሌባ በምን ሰዓት እንደሚመጣ እንደማይ
ታወቅ ሁሉ፣የጌታም ዳግም ምፅአት እንደ
ዚያው ሳይታሰብ በድንገት ይሆናል። በዚ
ያን ጊዜ ሰማያት በታላቅ ድምፅ ተነዋው
ጠው ያልፋሉ። የሰማይ አካላት እንደ ሰም
ይቀልጣሉ። ምድርና በላይዋ ላይ ያለ ነገር
ሁሉ በእሳት ይጋያል።
11 እንግዲህ መላው ዓለም እንደዚህ
ቀልጦ የሚጠፋ ከሆነ ይህን የጌታን ቀን
በናፍቆት እየተጠባበቃችሁ የተቀደሰ ሕይ
ወት መኖር ይገባችኋል። 12 በዚያም ቀን፣
ሰማያት በእሳት ተቃጥለው፣የሰማይ አካላ
ትም እንደ ሰም ቀልጠው ይጠፋሉ።
13 እኛ ግን እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋ
መሠረት ጽድቅ የሰፈነባትን አዲስ ሰማይና
አዲስ ምድር ለመውረስ በናፍቆት እንጠባበ
ቃለን።
14 ወዳጆቼ ሆይ፤የእነዚህን ነገሮች መፈ
ጸምና የጌታን ዳግም መምጣት በምንጠባበ
ቅበት ወቅት፣ከማናቸውም ኃጢአት ርቀን
እንኑር። ከሌሎች ጋር ያለን ግንኙነት በሰ
ላም ላይ የተመሠረተ ይሁን። ይህን ያደረ
ግን እንደሆነ በዳግም ምፅአቱ ጊዜ ጌታን
ደስ የምናሰኝ ሆነን እንገኛለን።
15-16 የጌታ ዳግም ምፅአት ለምን እንደዘ
ገየ ታውቃላችሁ? የዘገየበት አንዱ ምክን
ያት የወንጌልን ቃል ሰምተው ላልዳኑት
የምሥራቹን ቃል የምናደርስበት በቂ ጊዜ
እንዲኖረን ነው። ይህንንም ነገር አስተዋይና
ተወዳጅ የሆነው ወንድማችን ጳውሎስ በጻ
ፈላችሁ መልእክቶች በአብዛኛዎቹ ላይ
ጠቅሶታል። ጳውሎስ በጻፋቸው መልእክ
ቶች ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ አሳቦች
ለመረዳት ከባድ ነው። ታዲያ አላዋቂ የሆኑ
ሰዎች አልገባ ሲላቸው፣ለሌሎቹ የቅዱሳት
መጻሕፍት ቃሎች የተሳሳተ ትርጉም እንደ
ሰጡ ሁሉ፣ለእርሱም መልእክቶች የተሳሳተ
ትርጉም ሲሰጧቸው ይታያሉ። የዚህም
ውጤቱ ጥፋትን በራሳቸው ላይ ማምጣት
ነው።
17 ወንድሞቼ ሆይ፤እናንተ ግን ይህን
አስቀድማችሁ ስለምታውቁ እንደዚህ ካሉ
ራሳቸው ስተው ከሚያስቱና እምነታች
ሁን ከሚያናውጡ ሰዎች ጠማማ ትምህ
ርት ተጠንቀቁ። 18 ነገር ግን መንፈሳዊ
ሕይወታችሁ በጸጋው ያድግ ዘንድ፣ጌታች
ንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በበ
ለጠ ለማወቅ ተጣጣሩ። ምስጋናና ክብር
ዛሬም ዘወትርም እስከ ዘላለም ድረስ ለእ
ርሱ ይገባዋል። አሜን!

ወንድማችሁ
ጴጥሮስ

# የሐዋርያው ዮሐንስ የመጀመሪያው መልእክት

## መግቢያ

ዮሐንስ ከመጀመሪያዎቹ የጌታ ደቀ መዛሙርት አንዱ ነው። በስሙ የሚጠራውን ወንጌልና እነዚህን ሦስት መልእክቶች መቼ እንደ ጻፋቸው በውል ተለይቶ የሚታወቅ ነገር የለም። በ85 እና በ95 ዓ.ም. መካከል ባሉት ዓመታት ጽፏቸዋል ተብሎ ይገመታል። መልእክቶቹ እግዚአብሔር ፍቅር እንደሆነ፥ የእግዚአብሔር ልጆችም እርስ በርሳቸው መፋቀር እንዳለባቸውና ስለ እግዚአብሔር የተነገረውንም የእውነት ቃል ማፍቀር እንደሚገባቸው ደግመው ደጋግመው ያሳስባሉ።

---

## ምዕራፍ 1

1 ገና ዓለም ሳይፈጠር ሕያው ሆኖ
ይኖር የነበረው ክርስቶስ፥የተናገረውን ሰም
ተናል፤በዓይናችን አይተነዋል፤ተመልክተነ
ዋል፤በእጃችንም ዳስሰነዋል። 2 ይህ የዘላለም
ሕይወት የሆነውና በአብ ዘንድ የነበረው
ክርስቶስ፥ወደዚች ምድር በእርግጥ መጥቶ
እኛም በዓይናችን ያየነው መሆኑን እናረጋ
ግጥላችኋለን። 3 ከእግዚአብሔር አብና
ከልጁ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ኅብረት እን
ዳለን ሁሉ፥እናንተም ከእኛ ጋር ኅብረት
ይኖራችሁ ዘንድ፥ያየነውንና የሰማነውን እን
ነግራችኋለን። 4 ይህንን የምንጽፍላችሁ ደስ
ታችን ፍጹም ይሆን ዘንድ ነው።

5 ለእናንተ እንድንነግራችሁ ከክርስቶስ
የተቀበልነው መልእክት፥ «እግዚአብሔር
ብርሃን ነው፥በእርሱ ዘንድ ምንም ጨለማ
የለም» የሚል ነው። 6 ስለዚህ፥የእግዚአብ
ሔር ወዳጆች ነን እያልን በኃጢአትና
በጨለማ ውስጥ የምንኖር ከሆንን ሐሰተ
ኞች ነን፤እውነትም በሕይወታችን በተግ
ባር አልታየም። 7 ነገር ግን እግዚአብሔር
በብርሃን እንደሚኖር እኛም በመንፈሳዊ
ብርሃን ውስጥ ብንኖር፥ከእርሱ ጋር ትክክ
ለኛ ግንኙነት አለን ማለት ነው። የልጁም
የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ
ያነጻናል።

8 ኃጢአት የለብንም ብንል፥ራሳችንን
እናታልላለን፤እውነተኞችም አይደለንም።
9 ኃጢአታችንን ብንናዘዝ ግን፥እርሱ የታመ
ነና ጻድቅ በመሆኑ፥ኃጢአታችንን ይቅር
ይለናል፤ከክፋትም ሁሉ ያነጻናል። 10 ኃጢ
አት አልሠራንም ብንል የእግዚአብሔርን
ቃል ማስተባበልና እግዚአብሔርንም ሐሰ
ተኛ ማድረግ ይሆንብናል።

## ምዕራፍ 2

1 ልጆቼ ሆይ፥ይህንን ሁሉ የምጽፍላ
ችሁ ኃጢአት እንዳትሠሩ በማለት ነው።
ኃጢአት ብትሠሩ ግን፥በአብ ዘንድ የሚከራ
ከርላችሁ ጠበቃ እንዳላችሁ ልታውቁ ይገ
ባል። ጠበቃችሁም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ
ክርስቶስ ነው። 2 እርሱ ኃጢአታችንን ለማ
ስወገድ መሥዋዕት ሆኖልናል። መሥዋዕት
የሆነውም ለእኛ ኃጢአት ብቻ ሳይሆን
ለመላው ዓለም ኃጢአት ሁሉ ነው። 3 የእግ
ዚአብሔር ወገኖች መሆናችንን ማረጋገጥ
የምንችለውም ትእዛዛቱን በመፈጸም ነው።
4 «እኔ አውቀዋለሁ» እያለ፥ትእዛዛቱን የማ
ይፈጽም ቢኖር ግን፥እርሱ ሐሰተኛ ነው፤
እውነትንም መቀበል አይፈቅድም። 5 የእግ
ዚአብሔርን ትእዛዝ የሚፈጽም በእርግጥ
እግዚአብሔርን ይወዳል። 6 «የእርሱ ነኝ»
የሚል ሰው፥ክርስቶስ እንደኖረ በመኖር የእ
ርሱን አርአያ መከተል አለበት። የእርሱ
መሆናችንንም የምናረጋግጠው በአኗኗራችን
ነው።

7 ወንድሞቼ ሆይ፥የምጽፍላችሁ ከዚህ
በፊት ስለማታውቁት አዲስ ትእዛዝ አይደ
ለም። እኔ የምጽፍላችሁ ከመጀመሪያው
አንሥቶ ስለሰማችሁትና ስለምታውቁት
ነባር ትእዛዝ ነው። 8 ይህም ትእዛዝ ምን
ጊዜም አዲስ ነው። ትእዛዙ በመጀመሪያ
በክርስቶስ ሕይወት ውስጥ የተፈጸመ
ሲሆን፥አሁን ደግሞ ፍሬው በሕይወታችሁ
ውስጥ እየታየ ነው። ይህም የሆነበት ምክን
ያት ጨለማው ተወግዶ እውነተኛው መንፈ
ሳዊ ብርሃን በሕይወታችሁ ውስጥ መብራት
በመጀመሩ ነው።

9 በክርስቶስ ብርሃን እመላለሳለሁ እያለ
ወንድሙን የሚጠላ ገና ከጨለማ አልወ

ጣም። 10 ነገር ግን ወንድሙን የሚወድ
በብርሃን ይመላለሳል። በመንገዱም ላይ አደ
ናቅፎ የሚጥለው መሰናክል አይኖርም።
11 ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ ውስጥ
ይደናበራል። ጨለማውም አጥርቶ እንዳያይ
ዓይኑን ስለሚጋርደው የሚሄድበትን አያው
ቅም።

12 በዕድሜ አነስተኛ የሆናችሁ ልጆቼ
ሆይ፥ ኃጢአታችሁ በመድኃኒታችን በኢየ
ሱስ ክርስቶስ ስም ይቅር ስለተባለላችሁ
ይህንን እጽፍላችኋለሁ። 13 እናንተም አባ
ቶቼ ሆይ፥ከመጀመሪያው አንሥቶ ሕያው
ሆኖ የሚኖረውን ክርስቶስን ስላወቃችሁት
ይህንን እጽፍላችኋለሁ። እናንተም ጐልማ
ሶች ሆይ፥ ሰይጣንን ድል ስላደረጋችሁት
ይህንን እጽፍላችኋለሁ። 14 እናንተ ወጣት
ወንዶችና ልጃገረዶች ሆይ፤አባታችን እግዚ
አብሔርን ስለአወቃችሁት ይህንን እጽፍላ
ችኋለሁ። አባቶች ሆይ፥ዘላለማዊ የሆነውን
አምላክ ስላወቃችሁት ይህንን ጽፌላችኋ
ለሁ። ወጣቶች ወንዶችና ልጃገረዶች ሆይ፥
የእግዚአብሔር ቃል በልባችሁ በመኖሩ
ብርቱ ስለሆናችሁና ሰይጣንን ስለአሸነፋ
ችሁ ይህንን ጽፌላችኋለሁ። 15 ዓለምንና
በውስጥዋ ያሉትን ነገሮች አትውደዱ። ዓለ
ምንና በውስጥዋ ያሉትን ነገሮች የሚወዱ
የእግዚአብሔር ፍቅር የለባቸውም። 16 የዓ
ለም ነገሮች የምላቸውም፤ ክፉ ምኞት፥
የሥጋ ፍትወት፥ያዩትን ሁሉ «ምነው የእኔ
በሆነ» ማለት፥ ከሀብትና ከተደላደለ ኑሮ
የሚመጣ አጉል ትምክህት ናቸው። የእነ
ዚህ ሁሉ ምንጫቸው እግዚአብሔር አብ
ሳይሆን ክፉው ዓለም ነው። 17 ዓለምና በው
ስጥዋ ለሚገኙ ነገሮች ያለ ጉጉት ሁሉ
ይጠፋሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደ
ርግ ሰው ግን ለዘላለም ይኖራል።

18 የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ፥ ይህች
ዓለም የምታልፍበት ጊዜ ሩቅ እንዳይመስላ
ችሁ። በመጨረሻው ጊዜ ሐሰተኛ ክርስቶስ
እንደሚመጣ ሰምታችኋል። አሁንም እንኳ
ሐሰተኞች ክርስቶሶች ተነሥተዋል። ስለዚህ
ይህንን ሁሉ ስናይ ይህች ዓለም የምታልፍ
በት ሰዓት እየተቃረበ መምጣቱን እንረዳ
ለን። 19 እነዚህም ሐሰተኞች ክርስቶሶች
ቀድሞ በመንፈሳዊ ኅብረታችን መካከል የነ
በሩ ናቸው። ሆኖም በዚያን ጊዜም ቢሆን
አፋቸው እንጂ ልባቸው ከእኛ ጋር አልነበ
ረም። ቢሆንማ ኖሮ ከእኛ ጋር ጸንተው
በቆዩ ነበር። ከእኛ ተለይተው መውጣ
ታቸው ቀድሞውንም ቢሆን ከእኛ ጋር
እንዳልነበሩ ያሳያል።

20 እናንተ ግን መንፈስ ቅዱስ አድሮባ
ችሁ ስለሚኖር እውነትን በማወቃችሁ ከእ
ነርሱ ጋር አንድ አይደላችሁም። 21 ይህን
የምጽፍላችሁ እውነትን ስለማታውቁ አይደ
ለም። እውነትንና ሐሰትን መለየት ስለምት
ችሉ እንድትጠነቀቁ ብቻ ላሳስባችሁ ነው።

22 ለመሆኑ ኢየሱስ መሲሕ መሆኑን
ከሚክድ ሰው በቀር ሐሰተኛ ማነው? እን
ዲህ ያለው ሰው በአብና በወልድ ስለማያ
ምን የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው። 23 የእግዚአ
ብሔር ልጅ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን
የማያምን አብንም አያምንም። በወልድ
የሚያምን ግን አብንም ያምናል።

24 ስለዚህ ከመጀመሪያው አንሥቶ በተ
ማራችሁት ቃል ልባችሁ ጸንቶ ይኑር። ይህ
ንን ብታደርጉ ከእግዚአብሔር አብና ከል
ጁም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድነት ይኖ
ራችኋል። 25 ክርስቶስ ራሱ የዘላለምን ሕይ
ወት ተስፋ ሰጥቶአችኋል።

26 ከስሕተት አዘቅት ሊጨምሯችሁ ወዲ
ያና ወዲህ ስለሚሯሯጡት ሰዎች እንድታ
ውቁ ይህን እጽፍላችኋለሁ። 27 እናንተ
መንፈስ ቅዱስን ስለተቀበላችሁና የእርሱም
ቅባት በእናንተ ስለሚኖር ሌላ አስተማሪ
አያስፈልጋችሁም። መንፈስ ቅዱስ እውነ
ትን እንጂ ሐሰትን ስለማይናገር እርሱ ራሱ
ሁሉንም ያስተምራችኋል። ስለዚህ መንፈስ
ቅዱስ በገለጸላችሁ መሠረት ምን ጊዜም
በክርስቶስ ኑሩ።

28 አሁንም ልጆቼ ሆይ፥ ጌታ በሚመጣ
በት ጊዜ እንዳናፍር፥ ነገር ግን ተማምነን
ፊቱ መቅረብ እንድንችል ካሁኑ ጀምሮ ከእ
ርሱ ጋር ደስ የሚያሰኝ አንድነት ይኑራ
ችሁ። 29 ጌታ ጻድቅ መሆኑንና የሚያደርገ
ውም ሁሉ መልካም መሆኑን ካወቃችሁ፥
መልካም የሚያደርጉ ሁሉ የእርሱ ልጆች
እንደሆኑ ትረዳላችሁ።

## ምዕራፍ 3

1 የሰማዩ አባታችን የቱን ያህል እንደወ
ደደን ተመልከቱ! ስለ ወደደንም «የእግዚ
አብሔር ልጆች» ተብለን ለመጠራት አብቅ
ቶናል። በእርግጥም ደግሞ የእግዚአብሔር
ልጆች ነን። ዓለም ግን እኛን እንደ እግዚአ
ብሔር ልጆች አያውቀንም፤ ምክንያቱም
ዓለም እግዚአብሔርን ራሱን ስላላወቀው
ነው። 2 ወዳጆቼ ሆይ፥አሁን የእግዚአብሔር
ልጆች መሆናችንን የሚያጠያይቅ ነገር አይደ
ለም። እርግጥም የእግዚአብሔር ልጆች

ነን። ወደፊት ግን ከትንሣኤ በኋላ ምን እን
ደምንሆን አስቀድሞ መገመቱ ያዳግት ይሆ
ናል። ግን አንድ ነገር እናውቃለን። ይህም
ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ማንነቱን ፊት
ለፊት ስለምናይ እርሱን መስለን እንደምን
ገኝ እናውቃለን። 3 ይህ ተስፋ በልቡ ያለ
አማኝ፥ክርስቶስ ንጹሕ እንደሆነ ሁሉ እር
ሱም ራሱን በንጽሕና ይጠብቃል።

4 ኃጢአት የሚሠራ ሁሉ የእግዚአብሔ
ርን ትእዛዝ ያፈርሳል፤ምክንያቱም ኃጢአት
ማለት እግዚአብሔርን አለመታዘዝ ነውና።
5 ክርስቶስ ግን በሥጋ የተገለጠው ኃጢአታ
ችንን ለማስወገድ እንደሆነ ታውቃላችሁ፤
እርሱ ራሱማ ምን ኃጢአት አለበት? 6 ስለ
ዚህ በክርስቶስ ጸንቶ የሚኖር ኃጢአትን
አይለማመድም ፤ ኃጢአትን የሚለማመድ
ግን፥እርሱን ፈጽሞ አላየውም፤አላወቀው
ምም።

7 ውድ ልጆቼ ሆይ፥በዚህስ ማንም እንዳ
ያሳስታችሁ ተጠንቀቁ። ክርስቶስ ጻድቅ እን
ደሆነ የጽድቅን ሥራ የሚሠራ ሁሉ ጻድቅ
ነው። 8 ነገር ግን ኃጢአት መሥራትን
እንደ ልማድ አድርጎ የሚኖር እርሱ የዲያ
ብሎስ ወገን ነው። ምክንያቱም ዲያብሎስ
ከመጀመሪያው አንሥቶ በኃጢአት ሥራ
ጸንቶ ይኖራልና። የእግዚአብሔር ልጅ የተ
ገለጠውም ይህንኑ የዲያብሎስን ሥራ ለመ
ሻር ነው። 9 የእግዚአብሔር የቅድስና ባሕ
ርይ በእርሱ ውስጥ ይኖራልና፥ከእግዚአብ
ሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን በመለማ
መድ አይኖርም። ከእግዚአብሔር ተወልዶ
አዲስ ሕይወት አግኝቷልና ኃጢአት መሥ
ራት አይችልም።

10 ከዚህ የተነሣም እነማን የእግዚአብ
ሔር ልጆች፥እነማን ደግሞ የዲያብሎስ
ልጆች መሆናቸውን፥ለይቶ ማወቅ ይቻ
ላል። ትክክል የሆነውን ነገር ሁሉ የማያደ
ርግና ወንድሙን የሚጠላ የእግዚአብሔር
ልጅ አይደለም። 11 ከጥንት ከመሠረቱ የሰ
ማችሁት መልእክት እርስ በእርሳችን እንድ
ንፋቀር የሚያዝዝ ነው።

12 የክፉው የሰይጣን ወገን እንደሆነውና
ወንድሙን እንደገደለው እንደ ቃየል
መሆን የለብንም። ለመሆኑ ቃየል ወንድ
ሙን ለምን ገደለው? የእርሱ ሥራ ክፉ
የወንድሙ የአቤል ሥራ ግን ትክክል መሆ
ኑን ያውቅ ስለነበረ አይደለምን? 13 ወዳ
ጆቼ ሆይ፥ስለዚህ ዓለም ቢጠላችሁ አትደ
ነቁ።

14 ወንድሞቻችንን የምንወድ ከሆነ የዘላ
ለም ሕይወት አለን፤ከሞት ወደ ሕይወትም
ተሻግረናል። 15 ወንድሙን የሚጠላ በእርግ
ጥም ነፍሰ ገዳይ ነው። ነፍሰ ገዳይ ደግሞ
የዘላለም ሕይወት እንደሌለው ታውቃላ
ችሁ። 16 የእውነተኛ ፍቅርን ምንነት ለመ
ረዳትም ክርስቶስ ለእኛ ሲል መሞቱን ማስ
ታወስ ይጠቅማል። እኛም ለወንድሞቻችን
ስንል ሕይወታችንን አሳልፈን መስጠት ይገ
ባናል።

17 አንድ ክርስቲያን በቂ ሀብት ኖሮት
ወንድሙ በችግር ላይ መሆኑን እያየ ሳይረ
ዳው ቢቀር፥ያ ሰው የእግዚአብሔር ፍቅር
አለው ለማለት እንዴት ይቻላል? 18 ልጆቼ
ሆይ፥ሰዎችን «እናፈቅራችኋለን» እያልን
በአፍ ብቻ መደለሉን ወዲያ ትተን ፍቅራ
ችን እውነተኛና በበጎ ሥራ የሚገለጥ
ይሁን። 19 ይህን በማድረጋችንም ከእውነት
ወገን መሆናችንን እናረጋግጣለን። ሕሊናች
ንም በሚወቅሰን ጊዜ ልባችንን በጌታ ፊት
የምናሳርፈው በዚሁ ነው። 20 ምክንያቱም
ጌታ ከሕሊናችን ስለሚበልጥ ከእርሱ
ምንም የተሰወረ ነገር የለምና።

21 ውድ ወዳጆቼ ሆይ፥ነገር ግን ከሕሊና
ወቀሳ ነጻ ከሆንን ፍጹም በሆነ መታመን
ወደ ጌታ ልንቀርብ እንችላለን። 22 ትእዛዛ
ቱን ስለምንፈጽም ደስ የሚያሰኘውንም ስለ
ምናደርግ ከእርሱ የለመንነውን ሁሉ እናገ
ኛለን። 23 የእግዚአብሔር ትእዛዝም፥በልጁ
በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ማመንና እንደታዘዝ
ነው እርስ በእርሳችን መፋቀር ነው። 24 የእ
ግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚፈጽሙ ከእግዚ
አብሔር ጋር ይኖራሉ፤እግዚአብሔርም በእ
ነርሱ ውስጥ ይኖራል። እግዚአብሔር በእኛ
ውስጥ መኖሩንም በሰጠን በመንፈስ ቅዱስ
እናውቃለን።

## ምዕራፍ 4

1 የተወደዳችሁ ወዳጆቼ ሆይ፥መንፈስን
ሁሉ አትመኑ። ብዙዎች ሐሰተኞች መምህ
ራን በዓለም አካባቢ ስለተነሡ፥ከእግዚአብ
ሔር መሆን አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ
መንፈስን ሁሉ መርምሩ። 2 የእግዚአብሔር
ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ለብሶ ወደዚች
ምድር መምጣቱን የሚያምን መንፈስ ከእግ
ዚአብሔር የተገኘ ለመሆኑ እርግጠኞች
መሆን ትችላላችሁ። ነገር ግን ኢየሱስ ሥጋ
ለብሶ መምጣቱን የማያምን መንፈስ እርሱ
ከእግዚአብሔር አይደለም። 3 የዚህ ዓይነቱ
መንፈስ፥ይመጣል ሲባል የሰማችሁት የሐሰ
ተኛው ክርስቶስ መንፈስ መሆኑን እወቁ።

ይህ መንፈስ ዛሬም እንኳ በዓለም ላይ ይገ
ኛል።
4 የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ፥እናንተ የእ
ግዚአብሔር ምርጦች ናችሁ። በመሆናች
ሁም ሐሰተኞችን መምህራን አሸንፋችኋቸ
ዋል። ለማሸነፍ የበቃችሁትም በእናንተ
አድሮ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ በዚች
ክፉ ዓለም ካለው ከማንኛውም የክፋት
ኃይል ይልቅ የሚበረታ በመሆኑ ነው።
5 እነርሱ ግን፥ዓለማውያን ስለሆኑ የሚያስቡ
ትም የሚናገሩትም ስለዚች ዓለም ነገር
ብቻ ነው። ይህ በመሆኑም በዓለም ሰዎች
ዘንድ ተደማጭነት አላቸው። 6 እኛስ?
እኛማ የእግዚአብሔር ልጆች ነን። እግዚአ
ብሔርን የሚያውቁ ይሰሙናል። የእግዚአብ
ሔር ወገኖች ያልሆኑ ደግሞ አይሰሙንም።
በዚህም የእውነትን መንፈስ ከሐሰት መን
ፈስ ለይተን ለማወቅ እንችላለን። 7 ወዳጆቼ
ሆይ፥ፍቅር ከእግዚአብሔር የሚገኝ ስለሆነ
እርስ በእርሳችን እንዋደድ። ሌላውን የሚ
ወድ በእርግጥ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ
ነው፤እግዚአብሔርንም ያውቃል። 8 ወንድ
ሙን የማይወድ እግዚአብሔርን አያውቀ
ውም፤እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።
9 በልጁ ሞት እኛ የዘላለምን ሕይወት
እንድናገኝ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ
ዚች ዓለም በመላክ የቱን ያህል የሚያፈቅ
ረን መሆኑን ገልጾልናል። 10 እኛ ስለ ወደ
ድነው ሳይሆን እርሱ ስለ ወደደንና ኃጢአ
ታችንን እንዲያስወግድልን ልጁን ስለ ላከ
ልን የእውነተኛ ፍቅርን ምንነት በተግባር
አሳይቶናል።
11 ወዳጆቼ ሆይ፥እግዚአብሔር እኛን
ይህን ያህል ካፈቀረን እኛም እርስ በርስ
መዋደድ ይገባናል። 12 እግዚአብሔርን ከቶ
ያየው የለም፤እርስ በእርሳችን ከተፋቀርን
ግን፥የእግዚአብሔር ማደሪያዎች እንሆና
ለን። ፍቅሩም በውስጣችን እያደገና እየላቀ
ይሄዳል። 13 እርሱ በእኛ እኛም በእርሱ
የምንኖር ለመሆናችን ማረጋገጫ ይሆነን
ዘንድ፥መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ እን
ዲያድር አድርጓል። 14 እንዲሁም አብ የዓ
ለም መድኃኒት አድርጎ ልጁን እንደላከው
በዓይናችን ያየን ስለሆነ ይህንኑ እንመሰክራ
ለን። 15 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆ
ኑን አምኖ የሚመሰክር ሁሉ፥እግዚአብሔር
በእርሱ እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።
16 እርሱ እንደሚያፈቅረን የተናገረውን
ቃል አምነን ስለተቀበልንና ፍቅሩንም ስለ
ቀመስን እግዚአብሔር የሚወደን የቱን
ያህል መሆኑን ተረድተናል። እግዚአብሔር
ፍቅር ነው። በፍቅርም የሚኖር ሁሉ በእግ
ዚአብሔር ይኖራል፥እግዚአብሔርም በእ
ርሱ ይኖራል። 17 በዚህ ዓለም ከክርስቶስ
ጋር ጸንተን የኖርን ከሆነ ፍቅራችን እያደ
ገና እየላቀ ስለሚሄድ፥በዚያች በፍርድ ቀን
ያለ አንዳች ፍርሃትና ጭንቀት በፊቱ ለመ
ቅረብ ድፍረት ይኖረናል።
18 ከልብ የሚወደንን ሰው እንደማንፈ
ራው ሁሉ፥እግዚአብሔርም የሚወደን
ፍጹም በሆነ ፍቅር በመሆኑ፥እንደሚቀጣን
በማሰብ ብቻ አንፈራውም። እግዚአብሔር
ይቀጣኛል በሚል ሥጋት የሚፈራው ሰው፥
እግዚአብሔር ፍጹም በሆነ ፍቅር እንደሚ
ወደው ገና ያላረጋገጠ መሆኑ ይታወቃል።
19 እርሱ አስቀድሞ ስለወደደን እኛም
መውደድን ከእርሱ ተማርን።
20 «እግዚአብሔርን እወደዋለሁ» እያለ
ወንድሙን የሚጠላ ሐሰተኛ ነው። በዓይነ
ሥጋ የሚያየውን ወንድሙን ያልወደደ፥ያላ
የውን እግዚአብሔርን እንዴት ሊወደው
ይችላል? 21 እግዚአብሔር ያዘዘን ትእዛዝ
ይህ ነው፤«እግዚአብሔርን የሚወድ ወንድ
ሙን ደግሞ ይውደድ።»

## ምዕራፍ 5

1 ኢየሱስ ክርስቶስ፥እርሱ ሲጠበቅ የነበ
ረው መሲሕ መሆኑን የሚያምን ሁሉ፥
እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። አባትን
የሚወድ ሁሉ ከእርሱ የተወለደውን ልጁ
ንም ይወደዋል። 2 የእግዚአብሔርን ልጆች
የምንወዳቸው መሆኑ የሚታወቀው እግዚአ
ብሔርን ስንወድና ትእዛዛቱንም ስንፈጽም
ነው። 3 እግዚአበሔርን መውደድ ማለትም
ትእዛዛቱን መፈጸም ነው። ትእዛዛቱም
እንደ ከባድ ሸክም የሚቆጠሩ አይደሉም።
4 የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ፥በክርስ
ቶስ ኃይል ኃጢአትንና ዓለማዊ ፈቃድን
በማሸነፍ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይፈጽ
ማል። ዓለምንም ማሸነፊያ መሣሪያችን
እምነት ነው።
5 ዓለምን ማሸነፍ የሚችለውም ኢየሱስ
የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን የሚያምን
ሰው ብቻ ነው። 6-8 ኢየሱስ የእግዚአብሔር
ልጅ መሆኑን እናውቃለን። እግዚአብሔር
ራሱ ይህንኑ በቃሉ አረጋግጦልናል። መጀ
መሪያ፥በተጠመቀበት ጊዜ ከሰማይ የተሰ
ማው ድምፅ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን
አብሥሯል። ቀጥሎም ከሕማማቱ በፊት
ይኸው እውነት በድጋሚ ከላይ በተሰማ

ድምፅ ተረጋግጦአል። በመጨረሻም፣የእው
ነት ምንጭ የሆነው መንፈስ ቅዱስ ለኢየ
ሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆን፣የዘወትር
ምስክር ነው። ስለዚህ ያሉን ምስክሮች
ሦስት መሆናቸው ነው። እነዚህም፣በልቦና
ችን ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ የም
ስክርነት ቃል፤ክርስቶስ በተጠመቀበት ጊዜ
ከላይ ከሰማይ የተሰማው ድምፅ፤እንዲሁም
ከሕማማቱ በፊት የተሰማው ድምፅ ናቸው።
ሦስቱም ምስክሮች የሚያረጋግጡልን ኢየ
ሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን
ነው። 9 ሰዎች የሚሰጡትን የምስክርነት
ቃል አምነን የምንቀበል ከሆነ፣የአምላክ
ምስክርነት ነውና እግዚአብሔር ስለ ልጁ
የተናገረውን ቃል በበለጠ አምነን መቀበል
ይኖርብናል። 10 በእግዚአብሔር ልጅ የሚያ
ምን ሁሉ የሚሰማው የምስክርነት ቃል
እውነት መሆኑን ልቦናው ያውቀዋል። ነገር
ግን እግዚአብሔርን የማያምን እርሱ ራሱ
ስለ ልጁ የሰጠውን ምስክርነት ባለመቀበሉ
እግዚአብሔርን ሐሰተኛ ያደርገዋል።
11 እግዚአብሔር አብ ስለ ልጁ የተናገ
ረው ቃል እርሱ ራሱ የዘላለምን ሕይወት
እንደሰጠንና ይህም ሕይወት በልጁ በኢየ
ሱስ ክርስቶስ የሚገኝ መሆኑን የሚመሰክር
ነው። 12 ስለዚህ የእግዚአብሔር ልጅ
ያለው የዘላለም ሕይወት አለው። የእግዚአ
ብሔር ልጅ የሌለው ግን የዘላለም ሕይወት
የለውም።
13 በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስ
ቶስ ለምታምኑ ሁሉ የዘላለም ሕይወት እን
ዳላችሁ እንድታውቁ ይህንን ጽፌላችኋ
ለሁ። 14 በእግዚአብሔር ላይ ያለን መተማ
መን ይህ ነው። ከእርሱ ፈቃድ ውጪ ያል
ሆነ ማናቸውንም ነገር ብንለምነው እርሱ
ይሰማናል። 15 የምንነግረውን እንደሚሰማን
ካወቅን፣የለመንነውን ሁሉ እንዳገኘን እና
ውቃለን።
16 ማንም ሰው ወንድሙ ለሞት የማያደ
ርሰውን ኃጢአት ሲሠራ ካየው፣እግዚአብ
ሔር ይቅር እንዲለው ይጸልይለት። ኃጢ
አቱ ለሞት የማያደርሰው ከሆነ እግዚአብሔ
ርም ይቅር ይለዋል። በሌላ በኩል ደግሞ፣
ለሞት የሚያደርሰውን ኃጢአት ለሠራ ሰው
መጸለዩ ዋጋ የለውም። 17 ማናቸውም ክፉ
ሥራ ሁሉ ኃጢአት ነው። እኔ የምናገረው
ግን፣ሰውን ለዘላለም ሞት ስለማያበቃ ኃጢ
አት ነው።
18 የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ኃጢአትን
እንደ ልማድ አድርጎ አይሠራም። ምክንያ
ቱም የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ
ስለሚጠብቀው ሰይጣን እጁን ሊያሳርፍበት
አይችልም። 19 እኛ የእግዚአብሔር ልጆች
ነን፤የቀረው ዓለም ግን ከሰይጣን ኃይል
ሥር መሆኑን እናውቃለን። 20 የእግዚአብ
ሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ወደዚች
ምድር መምጣቱንና እውነተኛውን አምላክ
እንድናውቀው የሚረዳንን ማስተዋል የሰ
ጠን መሆኑን እናውቃለን። በልጁ በኢየሱስ
ክርስቶስ ጸንተን የምንኖር ከሆነ፣በእግዚአ
ብሔር ጸንተን እንኖራለን ማለት ነው።
እውነተኛው አምላክና የዘላለምም ሕይወት
እርሱ ነው።
21 የተወደዳችሁ ልጆቼ ሆይ፣ከማንኛ
ውም የጣዖት አምልኮ ራቁ።

የእናንተው
ዮሐንስ

# የሐዋርያው ዮሐንስ ሁለተኛው መልእክት

1 የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ከሆንኩት
ከእኔ ከአረጋዊው ከዮሐንስ የተላከ። ለተ
መረጠችውና የእግዚአብሔር ወዳጅ ለሆነ
ችው እመቤት። በእኔ ብቻ ሳይሆን በምዕ
መናን ዘንድ ሁሉ በእውነት ተወዳጅ
ለሆኑትም ልጆቿ። 2 ምን ጊዜም ቢሆን
እውነት በልባችን ውስጥ ጸንታ ስለምት
ኖር፣ 3 በእውነትና በፍቅር በምንኖረው
ሕይወታችን የተነሣ፣ጸጋ፣ምሕረትና ሰላም
ከእግዚአብሔር አብና ከልጁ ከኢየሱስ
ክርስቶስ እናገኛለን።
4 ልጆችሽ በእውነት ጸንተውና የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ ፈጽመው የሚኖሩ መሆና
ቸውን በማየቴ እጅግ ደስ ብሎኛል።
5 ውድ እመቤት ሆይ፣ይህን መልእክት
የምጽፍልሽ አዲስ ትእዛዝ ልሰጥሽ ሳይ
ሆን፣ከሥር ከመሠረቱ፣«እርስ በርሳችሁ
ተዋደዱ» ተብሎ የተሰጠንን ትእዛዝ ላሳስ
ብሽ ነው። 6 ፍቅር ማለት ደግሞ የእግዚአ
ብሔርን ትእዛዝ መፈጸምና ከጥንት በተሰ

ጠው ትእዛዝ መሠረት በፍቅር ተሳስሮ
መኖር ነው።
[7-8]ኢየሱስ ክርስቶስ በዚች ምድር ላይ
ሰው ሆኖ በሥጋ መገለጡን የማያምኑ ብዙ
ሐሰተኞች መምህራን ተነሥተዋል። እነዚህ
በስሕተት ጐዳና ሊመሯችሁ የሚፈልጉ
አታላዮችና ፀረ ክርስቶሶች ናቸው። ትምህ
ርታቸውም ጸንተን ከምንኖርበት እውነት
የሚያናጋን በምሆኑ ፥ ልፋታችሁን ከንቱ
እንዳያስቀረው ተጠንቀቁ። እኔ በማስተማር
እናንተም በመማር የደከምንበትና ልናገ
ኘው የምንመኘው ዋጋ፥ከንቱ ሆኖ እንዳይ
ቀር አደራ። [9]በክርስቶስ ትምህርት የማይ
ጸና እግዚአብሔርን ያጣል። በክርስቶስ
ትምህርት ጸንቶ የሚኖር ግን አብም
ወልድም አይለዩትም።
[10]የክርስቶስን ትምህርት የሚቃወም
ሰው ላስተምራችሁ ብሎ ቢመጣ፥ቤታችሁ
አታስገቡት፤ፈጽሞ አታስጠጉት፤ [11]እንዲህ
ዓይነቱን ሰው ማቅረብ የክፉ ሥራው ደጋፊ
ሆኖ መገኘት ነውና።
[12]ልጽፍላችሁ የሚገባኝ ብዙ ነገር ነበ
ረኝ። ግን ሁሉንም በዚች ደብዳቤ ልገል
ጸው አልፈልግም። በቅርቡ መጥቼ ላያችሁ
አስባለሁ። ያን ጊዜ ስለ ሁሉም ነገር አንሥ
ተን በሰፊው እንነጋገርበታለን፤ ደስታችንም
የተሟላ ይሆናል።
[13]የተመረጠችው የእህትሽ ልጆች ሰላ
ምታ ያቀርቡልሻል።

ዮሐንስ

# የሐዋርያው ዮሐንስ ሦስተኛው መልእክት

[1]ከእኔ ከሽማግሌው ዮሐንስ እጅግ ለም
ወደው ወዳጄ ለጋይዮስ የተላከ፤
[2]የተወደድክ ወዳጄ ሆይ ፥ ነፍስህ
ፍጹም የሆነ ሰላም ያገኘችውን ያህል ጤን
ነትህ የተሟላ እንዲሆን፥ነገር ሁሉ እንዲሳ
ካልህም እጸልያለሁ። [3]አንዳንድ ወንድሞች
በዚህ ሲያልፉ ጐራ ብለው ጠይቀውኝ
ነበረ። ስለ አንተ አንሥተው፥በወንጌል ቃል
መሠረት በእውነት ጸንተህ የምትኖር መሆ
ንክን በነገሩኝ ጊዜ ፥ እጅግ ደስ አለኝ።
[4]የመንፈስ ልጆቼ በእውነት እየተመሩ
መኖራቸውን የሚያረጋግጥ የምስክርነት
ቃል ከሌሎቹ ከመስማት የበለጠ የሚያስደ
ስተኝ ነገር የለም።
[5]ውድ ወዳጄ ሆይ፥የወንጌልን ቃል በየ
ቦታው ለማዳረስ በዚያ የሚያልፉትን መም
ህራን ተቀብለህ በማስተናገድ ረገድ የፈጸም
ከው ተግባር ደስ የሚያሰኘኝ ነው። [6]ስላደረ
ግህላቸው አቀባበልና ስላሳየሃቸውም ፍቅር
እዚህ በሚገኙት ምዕመናን ፊት አመስግ
ነው ተናግረውልሃል። ወደፊትም ቢሆን
እንዳይቸገሩ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ሰጥ
ተህ እንድትሸኛቸው አደራ እልሃለሁ።
[7]እነዚህ መምህራን ከአገር አገር የሚንከራ
ተቱት ስለ ጌታ ስም ብለው ነው እንጂ፥
በሌላ ምክንያት አይደሉም። ወንጌልን የሚ
ያስተምሩት ገና ላላመኑ ወገኖች በመሆኑ፥
ምግባቸውንና ልብሳቸውን ቻሉን ፥ ማረፊያ
ሁኑን፥ወይም ደመወዝ ክፈሉን ብለው የሚ
ጠይቁ አይደሉም። [8]ስለዚህ እኛም የዚህ
የተቀደሰ አገልግሎት ተካፋዮች በመሆን፥
እንደነዚህ ያሉትን የእውነት መልእክተ
ኞች ልንረዳቸው ይገባል።
[9]ከዚህ ቀደም ለቤተ ክርስቲያኒቱ አንድ
ደብዳቤ መጻፌ ይታወሳል። ነገር ግን የቤተ
ክርስቲያኒቱ መሪ ነኝ ባዩ ዲዮጥራጢስ፥
ቃሌን ከቁም ነገር መቁጠር አልፈለገም።
[10]የዚህን ሰው ክፉ ሥራ፥ምን ብሎ እንደ
ሰደበንና ስሜንም እንዴት አድርጎ እንዳ
ጠፋ ስመጣ እነግራችኋለሁ። ይህ ብቻ
አይደለም። መምህራን ወንጌል ለማስተ
ማር በሚመጡበት ጊዜ ተቀብሎ አያስተ
ናግዳቸውም። ሌሎቹ ምዕመናንም እንዳያ
ስተናግዷቸው ይከለክላል። አልፎ ተር
ፎም እነዚህን መምህራን ሲያስተናግዱ
ያገኛቸውን ከቤተ ክርስቲያን ሕብረት
ያስወጣቸዋል።
[11]ውድ ወዳጄ ሆይ፥የእንደዚህ ዓይነቱን
ሰው ክፉ ምሳሌ እንዳትከተል ተጠንቀቅ።
ምን ጊዜም ቢሆን በጎ ሥራ ከመሥራት
ቸል አትበል። በጎ ሥራ መሥራት የእግዚ
አብሔር ልጅነት የሚገለጥበት፥በክፉ ሥራ
ጸንቶ መገኘት ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚ
ያርቅ መሆኑን አትርሳ። [12]ወደዚህ የመጣ
ሁሉ ድሜጥሮስን ደግ ሰው ነው እያለ ያመ
ሰግነዋል። ስለ ደግነቱ እውነት ራስዋም
ትመሰክርለታለች። እኔም አንዱ ምስክር
ነኝ። ምስክርነቱም እውነት ነው።

[13] ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበ
ረኝ። ነገር ግን ሁሉንም በዚች ደብዳቤ
ልገልጸው አልፈልግም። [14] የእግዚአብሔር
ፈቃዱ ቢሆን በቅርቡ ስለምመጣ ማናቸው
ንም ነገር በጥሞና አጫውትሃለሁ።
[15] እስከዚያው ድረስ ግን በሰላም ቆየኝ።
ከእኔ ጋር ያሉ ወዳጆችህ ሰላምታቸውን
ያቀርቡልሃል። አብረውህ ላሉት ወዳጆቼ
ደግሞ፣ ለእያንዳንዳቸው ሰላምታዬን በስም
አቅርብልኝ።

ያንተው
ዮሐንስ

# የይሁዳ መልእክት

## መግቢያ

ይህን መልእክት የጻፈው ይሁዳ፣እንደ ያዕቆብ እርሱም የጌታ ወንድም ተብሎ ይጠራል። መልእክቱን። በ68 እና በ80 ዓ.ም. መካከል ባሉት ዓመታት በአንዱ ሳይጽፈው እንዳል ቀረ ይገመታል። የእግዚአብሔር ቃል የማይሻርና የማይለወጥ መሆኑን፣እንደ ቃሉ የማይ ኖሩትንና የሐሰት ትምህርት ፈጥረው የሚያስተምሩትን ፣ የሚያስፈራና የሚያስደነግጥ ፍርድ የሚጠብቃቸው መሆኑን የይሁዳ መልእክት በማያወላውል ሁኔታ ያስረዳል።

---

[1] የኢየሱስ ክርስቶስ አገልጋይና የያዕቆ
ብም ወንድም ከሆነው ከይሁዳ የተላከ፤እግ
ዚአብሔር አብ ለጠራቸውና ለወደዳቸው፣
ኢየሱስ ክርስቶስም በእምነት ውስጥ ላዳና
ቸው ሁሉ።
[2] እግዚአብሔር፤ምሕረት፣ሰላምና ፍቅር
በብዛት ያድላችሁ።
[3] ወዳጆቼ ሆይ ፣ እግዚአብሔር ለሁላች
ንም ስለሰጠን ደኅንነት ልጽፍላችሁ ጥረት
በማድረግ ላይ ነበርኩ። ሆኖም ግን ፣እምነ
ታችሁን የሚያናጋ አሳሳቢ ነገር መኖሩን
ስለተረዳሁ ፣ አሳቤን በመቀየር ከእግዚአብ
ሔር ዘንድ ስለተቀበልነው እምነት እንድት
ጋደሉ በማሳሰብ ልጽፍላችሁ ተገደድኩ።
[4] ጌታችንና ገዢያችን የሆነውን ኢየሱስ ክር
ስቶስን የሚክዱና ፣ ‘ሰው አንድ ጊዜ ክርስ
ቲያን ከሆነ የፈለገውን ኃጢአት ቢሠራ እግ
ዚአብሔር አይቀጣውም’ እያሉ የሚያስተ
ምሩ ፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች
እናንተ መካከል ሠርገው ገብተዋል። እነዚ
ህን የመሳሰሉ ሰዎች ፍርድ እንደሚጠብቃ
ቸው ቀደም ብሎ የተጻፈ ስለሆነ ፣ ነገሩ
ዱብ ዕዳ አይሆንባችሁም።
[5] እንደምታውቁት ሁሉ እግዚአብሔር
የእሥራኤልን ሕዝብ ከግብጽ አገር ካወጣ
ቸው በኋላ ፣ ያላመኑትንና መታዘዝ ያልፈለ
ጉትን ከመካከላቸው ለይቶ በሞት ቀጥቶአ
ቸዋል። [6] እንደዚሁም ሥልጣናቸውንና
ክብራቸውን ስላልጠበቁ መኖሪያቸውን የለ
ቀቁትን መላእክት ፣ እግዚአብሔር በጨለማ
ቦታ ለዘላለም አሥሮ ፣ እስከ ታላቁ የፍርድ
ቀን ድረስ ያቆያቸው መሆኑን ላስታውሳ
ችሁ እወዳለሁ። [7] በተመሳሳይ ሁኔታም፣በሰ
ዶምና ገሞራ በአካባቢያቸውም በነበሩት
ከተሞች፣የደረሰውን ፍርድ መርሳት የለባች
ሁም። የእነዚህ ከተሞች ነዋሪዎች ፣ ወንድ
ከወንድ ጋር ግብረ ሥጋ ግንኙነት እስኪያ
ደርጉ ድረስ ከተፈጥሮ ሥርዓት ውጪ
የሆነ የዝሙት ተግባር ፈጽመው በመገኘታ
ቸው፣ከተሞቹና በውስጣቸው የነበሩት ነዋ
ሪዎች በእሳት ተቃጥለው ጠፍተዋል
ይህም ፣ ኃጢአተኞች በገሃነም እሳት እንደ
ሚቀጡ የሚያሳስብና የሚያስጠነቅቅ ትም
ህርት ነው።
[8] እነዚህ ነውረኞች ሰዎችም ፣ ይህንን
ሁሉ ዘንግተው አስጸያፊ ተግባራቸውን
በመቀጠል አካላቸውን ያረክሳሉ፤ባለሥልጣ
ኖችን ይንቃሉ፣በሰማይ በሚኖሩት ቅዱሳን
መላእክት ላይም የፌዝና የስድብ ቃል ይሰ
ነዝራሉ። [9] የመላእክት አለቃ የሆነው ሚካ
ኤል እንኳን ፣ ከሰይጣን ጋራ ስለ ሙሴ
አካል በተከራከረ ጊዜ፣ «እግዚአብሔር ይገ
ሥጽህ!» አለው እንጂ እንደ እነዚህ ሰዎች
ከአፉ የስድብ ቃል አልወጣም። [10] እነዚህ
ሰዎች ግን፣በማያውቁት ጉዳይ ጥልቅ ብሎ
መግባትና በሰውም ላይ ማሾፍ ልማዳቸው

ነው። አእምሮ እንደሌላቸው እንስሳት የተ
ፈጥሮ ስሜታቸው የሚፈልገውን ማድረግ
ስለሚወዱ ነፍሳቸውን ወደ ጥፋት ይመ
ራሉ።

11 ለእነዚህ ሰዎች ወዮላቸው! ምክንያ
ቱም ወንድሙን የገደለውን የቃየልን መን
ገድ ተከትለዋል፤ እንደ በለዓም ለገንዘብ
በመስገብገብ ስተዋል፤እንደ ቆሬም በዓመፅ
ድርጊታቸው ከጥፋት ላይ ወድቀዋል።

12 እነዚህ ሰዎች፥ በቤተ ክርስቲያን
ውስጥ በምታቀርቡት የፍቅር ማዕድ ላይ
ሲገኙ የለመደባቸውን አስጸያፊና ነውረኛ
ተግባር ከመፈጸም ወደኋላ አይሉም። ከስግ
ብግብነታቸው የተነሳም ያለቅጥ እየተሻሙ
ይበላሉ። ልክ በነፋስ እንደሚገፋ ዝናብ
እንደሌለው ደመና ናቸው። በመከር ወራት
ፍሬ እንደማይገኝባቸውና ከሥራቸው ተነቅ
ለው ሁለት ጊዜ እንደሞቱ፥ከማገዶነት በስ
ተቀር ሌላ ጥቅም እንደሌላቸው ዛፎች
ናቸው።

13 የተቆጣ የባሕር ማዕበል በሚደፍ
ቀው በአረፋው እንደሚታወቅ፥ እነርሱም
በአሳፋሪና በአስነዋሪ ተግባራቸው ይታወ
ቃሉ። እግዚአብሔር ካበጀላቸው ሥርዓት
ተፈናቅለው እንደሚንከራተቱት ከዋክብት፥
እነርሱንም ድቅድቅ ጨለማ የሞላበት የእ
ግዚአብሔር ፍርድ ለዘላለም ይጠብቃቸ
ዋል።


14 ከአዳም ሰባተኛው ትውልድ የሆነው
ሄኖክ ስለእነዚህ ሰዎች እንዲህ ሲል ትን
ቢት ተናግሯል፤ «እነሆ ጌታ ከብዙ ሺህ
ቅዱሳን ጋር ወደ ምድር ይመጣል። 15 ከዚ
ያም የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ ለፍርድ ከፊቱ
ይሰበስባል። በእግዚአብሔር ላይ ስለተናገ
ሩት የስድብ ቃልና ከከፉ መንገዳቸው የተ
ነሳ ስላደረጉት ዓመፅ፥ለኃጢአተኞች የሚገ
ባቸውን ቅጣት ይሰጣቸዋል።» 16 እነዚህም
ሰዎች ዘወትር የሚያጉረመርሙ፥እንደበታ
ቸው ያልተገራ፥ ክፋትን ሠርተው በቃን
የማይሉ፥በትዕቢት የተወጠሩና፥ጥቅም ለማ
ግኘት በማለት ሌሎችን በከንቱ ውዳሴ የሚ
ክቡ ናቸው።

17 ወዳጆቼ ሆይ፥የጌታችን የኢየሱስ ክር
ስቶስ ሐዋርያት አስቀድመው የተናገሩትን
ቃል አስታውሱ። 18 «በመጨረሻው ዘመን
ቅዱስ የሆነውን ነገር ሁሉ የሚያቃልሉና
የሚንቁ፥ርኩስ የሆነውን ምኞታቸውን የሚ
ፈጽሙ ሰዎች ይነሣሉ።» ሲሉ ተናግረ
ዋል። 19 በመካከላችሁ መለያየትን የሚፈ
ጥሩ እነዚህ ሰዎች ናቸው። እነርሱ ግን
ራሳቸውን ለሥጋዊ ምኞታቸው ያስገዙ
እንጂ መንፈስ ቅዱስ በእነርሱ ውስጥ አላደ
ረም።

20 እናንተ ግን፥ወዳጆቼ ሆይ፥ሕይወታች
ሁን በተቀደሰው እምነታችሁ ላይ መሥ
ርቱ፤ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል መጸለይን
አታቋርጡ።

21 ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፍቅር
ውስጥ በመኖር፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ
በምሕረቱ ያዘጋጀላችሁን የዘላለም ሕይወት
ለመውረስ በትዕግሥት ተጠባበቁ። 22 ለሚ
ጠራጠሩትም ርኅራኄንና ምሕረትን አሳዩዋ
ቸው። 23 አንዳንዶቹንም ከእሳት ላንቃ
ነጥቆ እንደማውጣት ያህል፥ ወደ ደኅንነት
ጉዳና መልሷቸው። ሌሎችም ደግሞ ደግነ
ታችሁን አይተው ልባቸውን ወደ ክርስቶስ
እንዲመልሱ ቸርነትን አድርጉላቸው።
ሆኖም እናንተ ራሳችሁ በእነርሱ ኃጢአት
እንዳትሳቡና እንዳትበከሉ በርኩሰት ካደ
ፈው ልብሳቸው እንኳን ራቁ። 24-25 እንዳ
ትወድቁ አቅፎና ደግፎ ሊያቆማችሁ፥ ከኃ
ጢአት አንጽቶና ቀድሶ በፍጹምነት ዘላለ
ማዊ ደስታ ወዳለበት ፊቱ ሊያቀርባችሁ
ለሚችል፥ እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው
አምላክ፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ፥
ክብር፥ግርማ፥ኃይልና ሥልጣን ጥንትም፥
አሁንም፥ ለወደፊትም እስከዘላለም ድረስ
ይሁን። አሜን!

ወንድማችሁ
ይሁዳ



# ስለ ዓለም ፍጻሜ

በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ገደማ ክርስቲያኖች በሃይማኖታቸው ምክንያት እንደ አውሬ እየታደኑ ይገደሉ ነበር። በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በተለይ ከሚያቀርባቸው ሦስት ደቀመዛሙርት መካከል አንዱ የሆነው ዮሐንስ፣ሽምግሎና እርጅና በጣም ተጭኖት ነበር። እርሱም በዚያ ዕድሜው በሜድትራኒያን ባሕር፣ፍጥሞ በተባለች ደሴት በግዞት ላይ ሳለ፣ እግዚአብሔር የሚያስደንቅ ራእይ ገለጠለት። ራእዩ በየዘመናቱ የሚገኙትን፣በተለይም በዓለም ፍጻሜ ላይ ሕያዋን የሚሆኑትን ክርስቲያኖች የሚመለከት ነው።

በመጨረሻዎቹ ዘመናት ከሰዎች ክፋት የተነሣ አሰቃቂ መከራ የሚመጣበት ጊዜ መኖሩንና ይህም፣ብሩሕ የንጋት ጮራ በሚፈነጥቅበት አዲስ ዓለም የሚተካ መሆኑን፣እግዚአብሔር በራእይ ለዮሐንስ ገልጦለታል።

በእርግጥ! በሰው ልጆች ክፋትና እብሪት ምክንያት፣ከፍ ያለ ሁከትና ብጥብጥ የሚከሰትበት የመጨረሻው ዘመን አልፎ፣ሰላምና ፍቅር የሠፈነበት አዲስ ሰማያዊ ዓለም ይመጣል። አዎ፣ሕመምና ሞት የሌለበት፣የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥበት፣ዘላለማዊ ደስታ የሞላበት፣አዲስ ዓለም!

# የዮሐንስ ራእይ

## መግቢያ

ጸሐፊው ሐዋርያው ዮሐንስ ነው። የተጻፈበትም ዘመን በ96 ዓ.ም. አካባቢ መሆኑ ይታመናል። መጽሐፉ ወደ ፊት በዓለም ላይ ስለሚደርሱትና ስለሚፈጸሙት ድርጊቶች ይናገራል። ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣትና ከዚሁ ጋር ስለ ተያያዙት ነገሮች ይገልጣል። ዮሐንስ የተገለጠለትን ራእይ በዚህ መጽሐፉ ያሰፈረው በልዩ ልዩ ምልክቶችና የሰው አእምሮ በቀላሉ ተመራምሮ ሊረዳቸው በማይችል ምሥጢራዊ ቃላት ነው። ይህም ሆኖ አጠቃላይ መሠረተ አሳቡ እስከዚህ የተሰወረ አይደለም። ስለሆነም፣ በዓለም ፍጻሜ ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ ከባድ መከራና ሥቃይ፣ እንዲሁም ልዩ ልዩ ዓይነት ጥፋቶች በዚች ምድር ላይ እንደሚደርሱ ከዚሁ መጽሐፍ መረዳት አያዳግትም። እነዚህ ሁሉ ነገሮች ከተፈጸሙ በኋላ፣ ክርስቶስ የጌቶች ጌታና የነገሥታት ንጉሥ ሆኖ በኃይል ይገለጣል። ለኃይሉና ለሥልጣኑም ወሰን አይኖረውም።

---

## ምዕራፍ 1

1 ይህ ቶሎ ብለው ስለሚፈጸሙ ነገሮች
የሚናገር መጽሐፍ ነው። ወደ ፊት የሚሆ
ኑትንም ነገሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ለአገልጋ
ዮቹ እንዲገልጽላቸው እግዚአብሔር ሥል
ጣን ሰጠው። ኢየሱስ ክርስቶስም መልአ
ኩን ልኮ እነዚህ ነገሮች ለአገልጋዩ ለዮሐ
ንስ በራእይ እንዲገለጡለት አደረገ። 2 ዮሐ
ንስ ከኢየሱስ የተቀበለውን የእግዚአብሔር
ቃል፣ በራእይ ያየውንና የሰማውን ሁሉ፣
በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጻፈው።
3 ስለዚህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻ
ፈው ነገር በቅርቡ ስለሚፈጸም፣ ይህንን የት
ንቢት ቃል የሚያነቡና ሲነበብ የሚሰሙ፣
ሰምተውም የሚፈጽሙት ሁሉ የተባረኩ
ናቸው።
4 በታናሹ እስያ ለሚገኙት ለሰባቱ አብ
ያተ ክርስቲያን ከዮሐንስ የተላከ።
ወዳጆቼ ሆይ፣ ካለውና ከነበረው፣ ወደ
ፊትም ከሚመጣው፣ በዙፋኑም ፊት ካሉት
ከሰባቱ መናፍስት፣ 5 እውነትን ከሚገልጥ
ልን ከታማኙ ምስክር ከኢየሱስ ክርስቶስ
ዘንድ፣ ጸጋና ሰላም ይሁንላችሁ። ከሙታ
ንም መካከል መጀመሪያ የተነሣ እርሱ
ነው። እርሱም የምድር ነገሥታት ሁሉ
ገዢ ነው። እኛን ስለሚወደን፣ በደሙ ከኃ
ጢአታችን ሁሉ አንጽቶ 6 አባቱና አምላኩ
ለሆነው ለእግዚአብሔር ካህናት ሆነን እን
ድናገለግል፣ ወደ መንግሥቱ አግብቶናል።
ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብ
ርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።
7 እነሆ እርሱ በደመና ታጅቦ ይመጣል።
የወጉት እንኳን ሳይቀሩ ሰዎች ሁሉ ያዩ
ታል። በምድር የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ መም
ጣቱን ሲያዩ፣ ከኀዘንና ከፍርሃት የተነሣ ስቅ
ስቅ ብለው ያለቅሳሉ። አዎን፣ ይህ ሁሉ
ይፈጸም፤ አሜን።
8 ያለውና የነበረው፣ ወደ ፊትም የሚመ
ጣው፣ ኃያሉ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣
«'አልፋና ኦሜጋ' የሆንኩ፣ ማለትም የሁሉ
ነገር መጀመሪያና መጨረሻ እኔ ነኝ።»
9 እኔም ዮሐንስ፣ በኢየሱስ ባገኘነው አን
ድነት፣ ሥቃያችሁን፣ የምትወርሱትን መንግ
ሥትና ጽኑ ትዕግሥታችሁን፣ የምጋራ ወን
ድማችሁ ነኝ።
የእግዚአብሔርን ቃል ስላስተማርኩና
ስለ ክርስቶስ የማውቀውን ሁሉ ስለ መሰከ
ርኩ ተይዤ፣ ፍጥሞ በምትባል ደሴት ላይ
ታሥሬ ነበር። 10 አንድ ጊዜ፣ 'በጌታ ቀን'
በመንፈስ ቅዱስ ተመስጬ ሳለሁ፣ ከኋላዬ
ኃይለኛ የሆነ የመለከት ድምፅ እንዲህ
ሲለኝ ሰማሁ፣ 11 «የምታየውን ነገር ሁሉ
በመጽሐፍ ጽፈህ በኤፌሶን፣ በሰምርኔስ፣ በጴ
ርጋሞን፣ በትያጥሮን፣ በሰርዴስ፣ በፊልድልፍ
ያና በሎዶቅያ ወደሚገኙት ሰባት አብያተ
ክርስቲያን ላክ።»
12 የሚያናግረኝ ማን ይሆን በማለት ወደ
ኋላዬ ዞር ስል፣ ሰባት የወርቅ መቅረዞችን
አየሁ። 13 በመቅረዞቹ መካከል እስከ እግሩ
ድረስ የሚደርስ ረጅም ልብስ የለበሰ፣ ወገ
ቡን በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ 'የሰው

ልጅ የሚመስል' ሰው አየሁ። 14 የራሱ
ጠጉር እንደ በረዶ የነጣ ነበር። ዓይኖቹም
ልክ እንደ እሳት ነበልባል ይጋረፉ ነበር።
15 እግሮቹ እንደ ተወለወለ ናስ ያበሩ
ነበር። ድምፁም እንደ ባሕር ማዕበል
ድምፅ ያስተጋባ ነበር። 16 በቀኝ እጁ ሰባት
ከዋክብት ይዞ ነበር። ከአፉም ፥ በሁለት
ወገን የተሳለና የሰላ ሰይፍ ይወጣ ነበር።
ፊቱም ደመና እንዳልጋረዳት ፀሐይ በኃይል
ያበራ ነበር።

17 ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ
ከእግሩ ሥር ወደቅሁ። እርሱ ግን ቀኝ
እጁን በላዩ ላይ ጭኖ፥ «አይዞህ አትፍራ፤
የሁሉ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ እኔ
ነኝ። 18 እኔ ሕያው ነኝ። ከዚህ በፊት ሞቼ
ነበር፤ ነገር ግን አሁን ለዘላለም ሕያው ሆኜ
እኖራለሁ። በሞትና በሲኦልም ላይ ሥል
ጣን አለኝ። 19 ስለዚህ አሁን ያየኸውንና
ወደ ፊትም የሚሆነውን ነገር ሁሉ ጻፍ።
20 በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና
የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ትርጉም የሚከተ
ለው ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ
ክርስቲያን መላእክት ናቸው። ሰባቱ መቅረ
ዞች ደግሞ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያን
ናቸው» አለኝ።

## ምዕራፍ 2

1 «በኤፌሶን ከተማ ላለው ቤተ ክርስቲ
ያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

«ሰባቱን ከዋክብት በቀኝ እጁ የያዘውና
በሰባቱ የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚመላ
ለሰው እንዲህ ይላል፥

2 «የፈጸምከውን ሥራ አውቃለሁ። በት
ጋት የምትሰጠውን አገልግሎትና ትዕግሥት
ህንም ተረድቻለሁ። ሰዎች ሲያጠፉ አይ
ተህ ዝም አለማለትህንና ሐዋርያ ሳይሆኑ፥
'ሐዋርያ ነን' የሚሉትን መርምረህ ውሸተ
ኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው፥ አውቃለሁ።
3 ለእኔ ስትል መከራን ሁሉ ያለመታከት
በትዕግሥት ተቀብለሃል።

4 «ነገር ግን፥ አንድ ጉድለት አግኝቼብሃ
ለሁ። እርሱም የዛሬ ፍቅርህ እንደ ድሮ
አይደለም። ድሮ ለእኔ የነበረህ ፍቅር አሁን
ቀንሶአል። ስለዚህ የድሮ ፍቅርህ ምን
ያህል እንደ ነበረ አስብ። 5 ከዚህ ቀደም
እንዴት ትወደኝ እንደ ነበርና፥ አሁን ግን
እንዴት እንደ ተለወጥክ ልብ በል። ስለዚህ
ንስሐ ግባ፤ መጀመሪያ ከልብ ታፈቅረኝ በነ
በረ ጊዜ ትፈጽመው የነበረውን ተግባር አከ
ናውን። ንስሐ ባትገባ ግን መጥቼ መቅረ
ዝህን ከሥፍራው አነሣዋለሁ።

6 «ነገር ግን አንድ ጥሩ ጠባይ አለህ፤እኔ
የምጠላውን የኒቆላውያንን ሐሰተኛ ትምህ
ርት አትወድም። 7 የሚሰማ የልቦና ጆሮ
ያለው፥መንፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን
የሚናገረውን ይስማ። ድል ለሚነሣ ሁሉ፥
በእግዚአብሔር ገነት ውስጥ ካለው ከሕይ
ወት ዛፍ ፍሬ እንዲበላ እፈቅድለታለሁ።

8 «በሰምርኔስ ከተማ ላለው ቤተ ክርስቲ
ያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

«የሁሉ ነገር መጀመሪያና መጨረሻ
የሆነው፥ ሞቶ የነበረውና ከሞት ተነሥቶ
በሕይወት የሚኖረው፥እንዲህ ይልሃል፤

9 «ስለ እኔ የምትቀበለውን መከራ፥በዚህ
ዓለም ላይ ድሀ መሆንህንና በሰማያዊ ሀብት
ግን ባለጸጋ መሆንህን አውቃለሁ። አይሁዳ
ውያን ሳይሆኑ፥ 'አይሁዳውያን ነን' የሚሉ
ትንና የሚቃወሙህን የሰይጣን መናኸሪያ
የሆኑትን ሰዎች ሁኔታ አውቃለሁ። 10 በእኔ
ምክንያት ሊደርስብህ ያለውን መከራ አት
ፍራ። ሰይጣን ሊፈትናችሁ ከእናንተ መካ
ከል አንዳንዶቹን በቅርቡ እንድትያዙና
ወደ ወህኒ ገብታችሁ መከራ እንድትቀበሉ
ያደርጋል። ለአሥር ቀኖች ትሠቃያላችሁ።
ነገር ግን እስከ ሞት የሚያደርስ መከራ
ቢያጋጥምህም እንኳ፥እስከ መጨረሻው የጸ
ናህ ሁን። እኔም የሕይወት አክሊል እሰጥሃ
ለሁ።

11 «የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፥ መን
ፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረ
ውን ይስማ። ድል የሚነሣ ሁሉ በሁለተ
ኛው ሞት አይጐዳም።

12 «በጴርጋሞን ከተማ ላለው ቤተ ክርስ
ቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፥

«በሁለት በኩል የተሳለና የሰላ ሰይፍ
ያለው እንዲህ ይልሃል፤ 13 «የሰይጣን ዙፋን
በተዘረጋበትና የአጋንንት አምልኮ እምብ
ርት በሆነችው ከተማ እንደምትኖር፥ለእ
ኔም ታማኝ እንደ ሆንክ አውቃለሁ።
ታማኝ ምስክሬ አንቲጳስ፥በዚች ከተማ ሰይ
ጣናዊ ተግባር በሚፈጽሙ ሰዎች በተገደለ
በት ጊዜ እንኳን፥አልካድከኝም።

14 «ነገር ግን እነዚህን ጥቂት ነገሮች
እጠላብሃለሁ። በእናንተ መካከል ያሉትን
የበለዓምን ትምህርት የሚከተሉትን አንዳ
ንድ ሰዎች ፥ አልተቃወምካቸውም። በለ
ዓም፥የእሥራኤል ልጆች ለጣዖት የታረደ
ውን እንዲበሉና የዝሙት ኃጢአት ፈጽ
መው እንዲሰናከሉ ለማድረግ፥ባላቅን መከ
ሮታል። 15 አዎን፥የኒቆላውያንን ትምህርት

የሚከተሉ ሰዎች በእናንተ መካከል እስካሁ
ንም አሉ።
16«ስለዚህ ንስሐ ግባ፤ ከስሕተትህም
ተመለስ፤ያለበለዚያ ግን በድንገት እመጣብ
ሃለሁ። እነዚህንም ሰዎች ከአፌ በሚወ
ጣው ሰይፍ አጠቃቸዋለሁ።
17«የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፥መን
ፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረ
ውን ይስማ። ድል ለሚነሣ፥ስውር ከሆነው
ሰማያዊ የሕይወት መና እመግበዋለሁ። እን
ዲሁም፥እኔ ከምሰጠው ሰው በቀር ማንም
ሊያነበው የማይችል፥አዲስ ስም የተጻፈበ
ትን ነጭ ድንጋይ እሰጠዋለሁ።
18«በትያጥሮን ከተማ ላለው ቤተ ክርስ
ቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
«እንደ እሳት ነበልባል የሚጋረፉ ዓይ
ኖች፥እንደ ተወለወለ ናስ የሚንቦገቦጉ እግ
ሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ፥እንዲህ
ይልሃል፤
19«የምታደርገውን መልካም ሥራ ያለ
ህን ፍቅርና፥ታማኝነት እንደዚሁም አገልግ
ሎትህንና ትዕግሥትህን አውቃለሁ። እንዲ
ሁም በፊት ከምታደርገው መልካም ሥራ
ይልቅ፥አሁን የምታደርጋቸው መልካም
ሥራዎች እንደሚበልጡ አውቃለሁ።
20«ይሁን እንጂ ይህን አንድ ነገር እጠ
ላብሃለሁ። ያቺን አገልጋዮቼን ዝሙት እን
ዲፈጽሙ፥ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ
የምትገፋፋውን፥'ነቢይ ነኝ' የምትለዋን
ኤልዛቤልን፥ዝም ብለሃታል። 21ንስሐ እን
ድትገባና ከዚህ ክፉ ሥራዋ እንድትመለስ
ጊዜ ሰጥቻት ነበር። ነገር ግን ንስሐ ለመግ
ባት ፈቃደኛ አልሆነችም። 22ስለዚህ እርሷ
ንና ከእርስዋ ጋር በመተባበር የሚያመነዝሩ
ትን ተከታዮቿን፥ክፉ ሥቃይ ላይ እጥላቸዋ
ለሁ። እርስዋም ሆነች ግብረ አበሮችዋ ስለ
ኃጢአታቸው ንስሐ ካልገቡ በቀር፥ቅጣቴን
ውሎ ሳያድር እፈጽምባቸዋለሁ። 23የኤልዛ
ቤልን ልጆች ሁሉ እገድላለሁ። አብያተ
ክርስቲያንም የሰውን ልብና ኩላሊት የም
መረምር መሆኔን ያውቃሉ። ለእያንዳንዳች
ሁም እንደ ሥራችሁ እከፍላችኋለሁ።
24-25«ነገር ግን ይህንን የሰይጣን ምሥ
ጢራት የተባለውን የሐሰት ትምህርት ያል
ተከተላችሁ በትያጥሮን የምትኖሩ፥ከዚህ
በላይ የምፈልግባችሁ ነገር የለም። እኔ እስ
ከመጣ ድረስ እምነታችሁን አጥብቃችሁ
ያዙ።
26«ድል ለሚነሣና እስከ መጨረሻ
ድረስ ፈቃዴን እየፈጸመ ለሚጠብቀኝ፥ሕዝ
ቦችን እንዲያስተዳድር ሥልጣን እሰጠዋ
ለሁ። 27አባቴ ለእኔ እንደሰጠኝ የግዛት
ሥልጣን እርሱም በብረት በትር ይገዛቸ
ዋል፤እንደ ሸክላም ይሰባብራቸዋል። 28የን
ጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ።
29«የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፥መን
ፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረ
ውን ይስማ።

## ምዕራፍ 3

1«በሰርዴስ ከተማ ላለው ቤተ ክርስቲ
ያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
«ሰባቱን የእግዚአብሔር መናፍስትና፥
ሰባቱን ከዋክብት የያዘው እንዲህ ይልሃል፥
«ሥራህን አውቃለሁ፤በስም ብቻ፥'መን
ፈሳዊ ነህ' ይሉሃል። እንደ እውነቱ ከሆነ
ግን፥በመንፈሳዊ ሕይወትህ የሞትህ ነህ።
2በእግዚአብሔር ፊት ሥራህን ፍጹም ሆኖ
አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን። ከሕይወትህ
ውስጥ ጨርሶ ሊጠፋ የተቃረበውን መል
ካም ነገር ነፍስ እንዲዘራ አድርግ። 3ስለ
ዚህ በመጀመሪያ የተማርከውንና የተቀበልከ
ውን ትምህርት አስብ፤አጥብቀህም ታዘዘው፤
ንስሐም ግባ። ይህንን ለማድረግ ባትሻ ግን፥
እንደ ሌባ ባላሰብከበትና ባልተዘጋጀህበት
ጊዜ መጥቼ፥ተገቢውን ቅጣት እንድትቀበል
አደርጋለሁ።
4«ሆኖም በዚያ በሰርዴስ፥በዓለም ርኩ
ሰት ሕይወታቸውን ያልበከሉ ጥቂት ሰዎች
አሉኝ። እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰው
ከእኔ ጋር ለመሄድ ብቁ ይሆናሉ። 5ድል
የሚነሣም ሁሉ፥እንደነርሱ ነጭ ልብስ ይለ
ብሳል። ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አል
ሰርዘውም። በአባቴና በቅዱሳን መላእክት
ፊትም የእኔ መሆኑን በግልጽ እመሰክርለታ
ለሁ።
6«የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፥መንፈስ
ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረውን
ይስማ።
7«በፊልድልፍያ ከተማ ላለው ቤተ ክር
ስቲያን፥መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤
«የዳዊት መክፈቻ ቁልፍ ያለው፥ቅዱ
ስና እውነተኛ የሆነው፥እርሱ የከፈተውን
ማንም የማይዘጋው፥እርሱ የዘጋውን ማንም
የማይከፍተው፥እንዲህ ይልሃል፥
8«ደህና አድርጌ ሥራህን አውቃለሁ፤
ብዙ ብርታት ባይኖርህም እንኳን፥ትእዛዜን
ፈጽመሃል፤ስሜንም አልካድከም። ስለዚህ
ማንም ሊዘጋው የማይችለውን በር ከፍቼል
ሃለሁ። 9ይህንን ነገር ልብ በል። አይሁዳው

ያን ሳይሆኑ፣ 'አይሁዳውያን ነን' እያሉ
የሚዋሹትን የሰይጣን ተከታዮች፣ ከእግርህ
ሥር እንዲወድቁና እንደምወድህም እንዲያ
ውቁ አደርጋለሁ። 10 ትዕግሥተኛ እንድት
ሆን የነገርኩህን የምክር ቃል ጠብቀሃል።
ስለዚህ እኔ ደግሞ በዚህ ምድር ላይ በሕይ
ወት የሚኖሩትን ሁሉ ሊፈትን ከሚመ
ጣው፣ የመከራ ቀን አድንሃለሁ። 11 እነሆ
በቶሎ እመጣለሁ። የተዘጋጀልህን አክሊል
ማንም እንዳይወስድብህ፣ ያለህን ብርታት
አጥብቀህ ያዝ። 12 ድል የሚነሣውን፣ አም
ላኬ መቅደስ ውስጥ ምሰሶ አድርጌ አቆመ
ዋለሁ። ከመቅደሱም ውስጥ ማንም ሊያወ
ጣው አይችልም። የአምላኬን ስም፣ ከሰማይ
የምትወርደውን የአምላኬን ከተማ የአዲሲ
ቷን ኢየሩሳሌምን ስም፣ እንዲሁም የእኔን
አዲስ ስም እጽፍበታለሁ።

13 «የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፣ መን
ፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረ
ውን ይስማ።

14 «በሎዶቅያ ላለው ቤተ ክርስቲያን
መልአክ፣ እንዲህ ብለህ ጻፍ፤

«ስሙ አሜን የሆነው፣ እግዚአብሔር
በመጀመሪያ የመፍጠር ሥራውን ሲጀምር
የነበረው፣ የማይናወጠውና ታማኝ የሆነው
እውነተኛው ምስክር እንዲህ ይልሃል፣

15 «ቀዝቃዛ ወይም ሙቅ እንዳልሆንክ
አውቃለሁ። ከሁለት አንዱን ብትሆን በተ
ሻለ ነበር። 16 ነገር ግን ቀዝቃዛ ወይም
ሙቅ ሳትሆን ለብ ያልክ በመሆንህ ልተ
ፋህ ነው። 17 'ሁሉ ነገር አለኝ፤ ሀብታም
ነኝ፤ የሚያስፈልገኝ ምንም ነገር የለም'
ትላለህ። ነገር ግን በመንፈስ የተራቆትህ
ጉስቋላ፣ ድሀና ዕውር መሆንህን አላስተዋል
ክም።

18 «ሀብታም መሆን ከፈለግህ በእሳት የነ
ጠረውን ንጹሕ ወርቅ፣ ራቁትነትህንና ሐፍ
ረትህንም ለመሸፈን ነጭ ልብስ፣ ለታወረ
ውም ዓይንህ ፍቱን የሆነ የዓይን መድኃ
ኒት፣ ከእኔ ግዛ። 19 የምወዳቸውን ሁሉ የም
ገሥጽና የምቀጣ እኔ ነኝ። አንተም ከፍ
ጹም ልብህ ንስሐ ግባ።

20 «እነሆ በደጅ ቆሜ በር አንኳኳለሁ።
ማንም ስጠራው ሰምቶ በሩን ቢከፍትልኝ
ወደ ቤቱ እገባለሁ፤ ከእርሱም ጋር እበላ
ለሁ፤ ሕብረትም ይኖረናል። 21 ድል ነሥቼ
በአባቴ ዙፋን ላይ እንደ ተቀመጥሁ፣ ድል
የሚነሣውንም ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ እንዲ
ቀመጥ እፈቅድለታለሁ።

22 «የሚሰማ የልቦና ጆሮ ያለው፣ መን
ፈስ ቅዱስ ለአብያተ ክርስቲያን የሚናገረ
ውን ይስማ።»

## ምዕራፍ 4

1 ከዚህ በኋላ በሰማይ የተከፈተ በር
አየሁ። ከዚህ ቀደም የሰማሁት እንደ ታላቅ
መለከት ድምፅ የሚያስተጋባው ድምፅም፣
«ወደዚህ ና! ከአሁን በኋላ የሚሆኑትን ነገ
ሮች አሳይሃለሁ» አለኝ።

2 ወዲያውኑ በመንፈስ ሆኜ ስመለከት
በሰማይ ተዘርግቶ የነበረውን ዙፋንና በዙፋ
ኑም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። 3 መልኩም
እንደ ኢያስጲድንና ሰርዲኖን ዕንቁ ያንጸባ
ርቅ ነበር። በዙፋኑ ዙሪያ፣ የሚንበለበል
'መረግድ' የተባለውን የከበረ ድንጋይ የመ
ሰለ፣ ቀስተ ደመና ነበር። 4 ዙፋኑንም የከ
በቡ ሌሎች ሃያ አራት ዙፋኖች ነበሩ። በእ
ነዚህ ዙፋኖች ላይ ነጭ ልብስ የለበሱና
በራሳቸው ላይ የወርቅ ዘውድ የደፉ፣ ሃያ
አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።
5 ከዙፋኑ የመብረቅና የነጐድጓድ ድምፅ
ይወጣ ነበር። ከዙፋኑ ፊት ለፊት ሰባት
የሚበሩ መብራቶች ነበሩ። እነርሱም ሰባቱ
የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው። 6 እንዲ
ሁም በዙፋኑ ፊት መስተዋት የሚመስል
የጠራ ባሕር ነበር። በመካከሉ ላይ በዙፋኑ
ዙሪያ፣ ከፊትም ከኋላም ብዙ ዓይኖች ያሏ
ቸው አራት እንስሶች ነበሩ። 7 የመጀመሪ
ያው እንስሳ አንበሳ፣ ሁለተኛው እንስሳ
በሬ፣ ሦስተኛውም እንስሳ የሰው ፊት፣ አራ
ተኛው እንስሳ ክንፉን ዘርግቶ የሚበር ንስር
ይመስል ነበር። 8 እያንዳንዱም እንስሳ በው
ስጥና በውጭ ብዙ ዓይኖች ያሏቸው ስድ
ስት ክንፎች ነበሩት። እነዚህም እንስሶች
ቀንና ሌሊት ባለማቋረጥ፣ «ቅዱስ፣ ቅዱስ፣
ቅዱስ ሁሉን የሚችል ጌታ አምላክ፣ አስቀ
ድሞ የነበረ፣ አሁንም ያለ፣ ወደ ፊትም የሚ
ኖር» ይሉ ነበር።

9 እንስሶቹ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና
ከዘላለም እስከ ዘላለም ለሚኖረው፣ ምስጋ
ናና ክብር በሚሰጡበት ጊዜ ሁሉ፣
10-11 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው
ተደፍተው በፊቱ እየሰገዱ፣ ከዘላለም እስከ
ዘላለም የሚኖረውን እርሱን ያመልኩት
ነበር። ዘውዳቸውን ከራሳቸው ላይ አንሥ
ተው በዙፋኑ ፊት በማስቀመጥ፣ «ጌታች
ንና አምላካችን ሆይ፣ ሁሉ ነገር የተፈጠ
ረው በአንተ ነው ሕይወትም ያገኘው በአ
ንተ ፈቃድ ነው። ስለዚህ ክብር፣ ኃይል፣
ምስጋና ይገባሃል» ይሉ ነበር።

## ምዕራፍ 5

[1] በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው በቀኝ እጁ፣
በውስጥና በውጭ የተጻፈበትና በሰባት ማኅ
ተም የታሸገ ብራና ይዞ ነበር። [2] አንድ
ብርቱ መልአክ በታላቅ ድምጽ፣ «ይህንን
እሽግ ሊከፍትና ብራናውን ሊገልጥ የሚገ
ባው ማን ነው?» ብሎ ሲጠይቅ ሰማሁ።
[3] ነገር ግን በሰማይም ሆነ በምድር እንዲ
ሁም ከምድር በታች፣ የማኅተሙን እሽግ
ለመክፈትና ብራናውን ገልጦ ለማየት የቻለ
ማንም አልተገኘም።
[4] እኔም ብራናውን ለመክፈትና ለማየት
ብቁ የሆነ ማንም ስላልተገኘ ተስፋ ቆርጬ
አለቀስኩ። [5] በዚህ ጊዜ ከሃያ አራቱ ሽማግ
ሌዎች አንዱ፣ «አይዞህ አታልቅስ፤ከይሁዳ
ነገድ ከዳዊት ዘር፣የተወለደውና ድልን የተ
ቀዳጀው አንበሳ ብራናውን ሊገልጥ፣የሰባቱ
ንም ማኅተሞች እሽግ ሊከፍት ይችላል»
አለኝ።
[6] ከዚህ በኋላ በዙፋኑ መካከል፣በአራቱ
እንስሶችና በሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ተከቦ፣
እንደታረደ የሚመስል በግ ቆሞ አየሁ።
ሰባት ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት።
ሰባቱ ቀንዶችና ሰባቱ ዓይኖች ወደ ምድር
ሁሉ የተላኩት ሰባቱ የእግዚአብሔር መና
ፍስት ነበሩ። [7] በጉም በዙፋኑ ላይ ወደ
ተቀመጠው ቀርቦ ከቀኝ እጁ ብራናውን
ወሰደ። [8] በዚህ ጊዜ አራቱ እንስሶችና ሃያ
አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወድቀው
ሰገዱ። እያንዳንዳቸውም በእጃቸው በገና
ይዘው ነበር። የቅዱሳን ጸሎት የሆነውን
ዕጣን የሞላ የወርቅ ሳህን ይዘው ነበር።
[9] እነርሱም ይህንን አዲስ መዝሙር
ዘመሩ፣ «ብራናውን ለመውሰድ የማኅተሞ
ቹንም እሽግ ከፍተህ ብራናውን ለመግለጥ
ብቁ ነህ፤ምክንያቱም ታርደህ ስለ ነበር ባፈ
ሰስከው ደም፣ ከየነገዱ፣ ከየቋንቋው፣ ከየሕ
ዝቡ ሰዎችን የእግዚአብሔር ወገን እንዲ
ሆኑ ዋጅተሃል። [10] የአምላካችንም ካህናት
እንዲሆኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
ሰብስበሃቸዋል፤በምድርም ላይ ይነግሣሉ።»
[11] ከዚህ በኋላ በሚሊዮን የሚቆጠሩ
መላእክት በዙፋኑና በአራቱ እንስሶች፣በሃያ
አራቱም ሽማግሌዎች ዙሪያ ቆመው
አየሁ። [12] እነርሱም ድምፃቸውን ከፍ አድ
ርገው፣ «የታረደው በግ ኃይልና ብልጽ
ግና፣ጥበብና ብርታት፣ክብር፣ውዳሴና ምስ
ጋና ይገባዋል» እያሉ ይዘምሩ ነበር።
[13] ከዚህ በኋላ በሰማይና በምድር፣ከም
ድር በታችና በባሕር ውስጥ ያሉ ፍጥረታት
ሁሉ፣ «በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠውና ለበጉ፤
ኃይል፣ ምስጋና፣ ክብር፣ ውዳሴ ከዘላለም
እስከ ዘላለም ድረስ ይሁን» እያሉ ሲዘምሩ
ሰማሁ። [14] አራቱ እንስሶች እየደጋገሙ
«አሜን» አሉ። ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችም
በግምባራቸው ተደፍተው ሰገዱ።

## ምዕራፍ 6

[1] በጉ ከሰባቱ ማኅተሞች እሽግ አንዱን
ሲከፍት አየሁ። ወዲያው ከአራቱ እንስሶች
አንዱ ነጐድጓድ በሚመስል ድምፅ፣ «ና!»
ሲል ሰማሁ።
[2] እኔም ልብ ብዬ ስመለከት አንድ ነጭ
ፈረስ አየሁ። በፈረሱም ላይ የተቀመጠው
ቀስት ይዞ፣ ዘውድም በራሱ ላይ ደፍቶ
ነበር። በደረሰበት ሁሉ ድልን ለመቀዳጀት
እንደ ድል አድራጊ ወጣ።
[3] በጉ የሁለተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፣ ሁለተኛው እንስሳ፣ «ና!» ሲል
ሰማሁ። [4] እኔም ልብ ብዬ ስመለከት አንድ
ቀይ ፈረስ አየሁ። በላዩ ላይ ለተቀመጠው
ትልቅ ሰይፍ ተሰጠው። እንደዚሁም፣ ሰላ
ምን ከምድር ላይ እንዲያጠፋና ሰዎች
እርስ በእርሳቸው እንዲጋደሉ እንዲያደ
ርግ፣ሥልጣን ተሰጠው።
[5] በጉ የሦስተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፣ ሦስተኛው እንስሳ፣ «ና!» ሲል
ሰማሁ። እኔም አንድ ጥቁር ፈረስ አየሁ።
በፈረሱ ላይ ተቀምጦ የነበረው በእጁ ሚዛን
ይዞ ነበር። [6] ከአራቱ እንስሳት መካከል፣
«አንድ እርቦ ስንዴ በአንድ ቀን ደመወዝ፣
ሦስት እርቦ ገብስ በአንድ ቀን ደመወዝ፤
ዘይትና ወይኑ ግን አይነካ» የሚል ድምፅ
ሲያስተጋባ ሰማሁ።
[7] የአራተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፣ አራተኛው እንስሳ፣ «ና!» ሲል
ሰማሁ። [8] እኔም አንድ ግራጫ ፈረስ አየሁ።
በላዩ ላይ ተቀምጦ የነበረው ስሙ ሞት
ይባል ነበር። ሲኦልም ተከተለው። የዓለምን
ሕዝብ አንድ አራተኛውን በሰይፍ፣በራብ፣
በበሽታ፣በክፉ አራዊት ወረራ፣እንዲገድሉና
እንዲያጠፉ ሥልጣን ተሰጣቸው።
[9] የአምስተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፣ መሠዊያ አየሁ። ከመሠዊያው በታች
የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማራቸውና
ታማኝ ምስክር በመሆናቸው የተገደሉ ሰማ
ዕታት ነፍሶች ነበሩ። [10] እነርሱም፣ «ሁሉን
የምትገዛ ቅዱስና እውነተኛ የሆንክ ጌታ
ሆይ፣ ደማችንን ያፈሰሱትን በምድር ላይ

የሚኖሩትን ደመኞቻችንን ሳትበቀላቸው
እስከ መቼ ትታገሣቸዋለህ?» እያሉ
ይጮኹ ነበር። 11 ለእያንዳንዳቸው ነጭ
ልብስ ተሰጣቸውና፥ «በምድር የሚኖሩት
ሌሎቹ ወንድሞቻችሁ እንደ እናንተ በሰማ
ዕትነት ተገድለው እናንተ ወዳላችሁበት
እስኪመጡ ድረስ ጥቂት ታገሡ» ተባሉ።
12 የስድስተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፥ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ። ፀሐ
ይም ጠቈረች፤ጨረቃም እንደ ደም ቀላች።
13 ነፋስ የበለስን ዛፍ ሲያወዛውዛት ፍሬዋ
እንደሚረግፍ፥ የሰማይ ከዋክብትም ወደ
ምድር ረገፉ። 14 ሰማይም እንደሚጠቀለል
ብራና ተጠቅልሎ ጠፋ። ተራራዎችና ደሴ
ቶችም ከነበሩበት ሥፍራ ተወገዱ። 15 የዓ
ለም ነገሥታትና መሳፍንት፥የጦር አዛዦች፥
ሀብታሞችና ኃይለኞች፥ አገልጋዮች፥ ጌቶ
ችም ሁሉ በየቋጥኙና በየተራራው ሥር
በሚገኙ ዋሻዎች ውስጥ ተሸሸጉ። 16 በፍር
ሃት ከመርበድበዳቸውም የተነሣ፥ ተራራዎ
ችንና ትልልቅ ቋጥኞችን፥ «በላያችን ላይ
ውደቁ። በዙፋኑ ላይ ከተቀመጠውና ከበ
ጉም ቁጣ ሰውሩን። 17 ታላቁ የቁጣ ቀን
መጥቶአል፤ማንስ ይህንን ቁጣቸውን ሊቋቋ
መው ይችላል?» አሉ።

## ምዕራፍ 7

1 ከዚህ በኋላ አራት መላእክት በአራቱ
የምድር ማዕዘኖች ዙሪያ ቆመው፥ከአራቱም
አቅጣጫ የሚነፍሱትን ነፋሶች ሲቈጣጠሩ
አየሁ። ከዚህም የተነሣ በምድር ላይ፥በባ
ሕር ላይና በዛፎች ላይ ጸጥታ ሰፍኖ ነበር።
2 እንደዚሁም ሌላ መልአክ ታላቁን የሕ
ያው እግዚአብሔር ማኅተም ይዞ ከምሥ
ራቅ ሲመጣ አየሁ። እርሱም መሬትንና
ባሕርን ለመጉዳት ሥልጣን የተሰጣቸውን
አራት መላእክት ጮኽ ብሎ፥ 3 «በአምላካ
ችን አገልጋዮች ግምባር ላይ የማኅተሙን
ምልክት ከማተማችን በፊት፥በምድር፥በባ
ሕር፥ወይም በዛፎች ላይ ምንም ጉዳት አታ
ድርሱ» አላቸው።
4 ከአሥራ ሁለቱ የእሥራኤል ነገዶች
ምልክቱ የታተመባቸው ሰዎች ቁጥር አንድ
መቶ አርባ አራት ሺህ ነበር። ዝርዝሩም
እንደሚከተለው ነው፥
5 ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ከሮ
ቤል ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ከጋድ ነገድ
አሥራ ሁለት ሺህ፥ 6 ከአሴር ነገድ አሥራ
ሁለት ሺህ፥ ከንፍታሌም ነገድ አሥራ
ሁለት ሺህ፥ ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት
ሺህ፥ 7 ከስምዖን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥
ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከይሳኮር
ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ 8 ከዛብሎን ነገድ
አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከዮሴፍ ነገድ አሥራ
ሁለት ሺህ፥ ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት
ሺህ፥
9 ከዚህ በኋላ ከየአገሩ፥ከየነገዱና ከየቋን
ቋው ሁሉ የተውጣጡ ቁጥራቸው ይኽ
ነው የማይባል ብዙ ሕዝቦች አየሁ። እነር
ሱም፥ነጭ ልብስ ለብሰው የዘንባባ ዝንጣፊ
በእጃቸው ይዘው፥ በዙፋኑና በበጉ ፊት
ቆመው ነበር። 10 ድምፃቸውንም ከፍ አድ
ርገው፥ «ደኅንነት የሚገኘው በዙፋኑ ላይ
ከተቀመጠው ከአምላካችንና ከበጉ ነው»
እያሉ ይጮኹ ነበር።
11 በዚህ ጊዜ በዙፋኑ፥በሃያ አራቱ ሽማ
ግሌዎችና በአራቱ እንስሶች ዙሪያ ቆመው
የነበሩት መላእክት፥በዙፋኑ ፊት በግምባራ
ቸው ተደፍተው እንዲህ እያሉ ለእግዚአብ
ሔር ይሰግዱ ነበር። 12 «አሜን! ውዳሴ፥
ታላቅነት፥ጥበብ፥ምስጋና፥ክብር፥ኃይልም፥
ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ
ለአምላካችን ይሁን! አሜን።»
13 ከሃያ አራቱ ሽማግሌዎች አንዱ፥
«ለመሆኑ እነዚህ ነጭ ልብስ የለበሱት እነ
ማን እንደሆኑና ከየት እንደ መጡ ታውቃ
ለህ?» ሲል ጠየቀኝ።
14 እኔም፥ «አላውቅም፥እባክህን ንገረኝ»
አልኩት። እርሱም፥
«እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው።
ልብሳቸውን በበጉ ደም አጥበው አጽድተ
ዋል። 15 እዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት
የተገኙትም በዚህ ምክንያት ነው። እንደም
ታየው እርሱን ሌሊትና ቀን በመቅደሱ
ውስጥ ያመልኩታል። በዙፋኑም ላይ የተቀ
መጠው መጠለያቸው ይሆናል። 16 ስለዚህ
ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፤ አይጠሙም።
ፀሐይም ሆነ ሙቀት አያጠቃቸውም።
17 በዙፋኑ መካከል ቆሞ የምታየው በግ
እረኛቸው ይሆናል፤ይመግባቸዋልም። ወደ
ሕይወት ውኃ ምንጭ ይመራቸዋል። እግዚ
አብሔርም ከዓይኖቻቸው ላይ እንባቸውን
ያብሳል» በማለት አስረዳኝ።

## ምዕራፍ 8

1 በጉ የሰባተኛውን ማኅተም እሽግ ሲከ
ፍት፥ ለግማሽ ሰዓት ያህል በሰማይ ታላቅ
ጸጥታ ሰፈነ። 2 እኔም በእግዚአብሔር ፊት

ቆመው የነበሩትን ሰባቱን መላእክት
አየሁ። ለእያንዳንዳቸውም አንድ አንድ
መለከት ተሰጣቸው።
3 አንድ ሌላ መልአክ ከወርቅ የተሠራ
ማዕጠንት ይዞ መጣና ከመሠዊያው አጠገብ
ቆመ። ከዙፋኑ ፊት ለፊት በቆመው የወ
ርቅ መሠዊያ ላይ እንዲቀርብ የቅዱሳን
ጸሎት የተቀላቀለበት ብዙ ዕጣን ተሰጠው።
4 መልአኩም ዕጣኑን በሠዋ ጊዜ ጢሱ ከቅ
ዱሳን ጸሎት ጋር ተቀላቅሎ ከእጁ ወደ
እግዚአብሔር ፊት ወጣ። 5 መልአኩም
በመሠዊያው ላይ ከተቀጣጠለው እሳት ላይ
የወርቅ ማዕጠንቱን ሞላበትና ወደ ምድር
ወረወረው። በዚህ ጊዜ ነጐድጓድ፣ መብረ
ቅና የምድር መናወጥ ሆነ።
6 ከዚያም ሰባቱ መላእክት የያዙትን
ሰባት መለከቶች ለመንፋት ተዘጋጁ።
7 የመጀመሪያው መልአክ መለከቱን
ነፋ። ወዲያው ደም የተቀላቀለበት በረዶና
እሳት ምድር ላይ ወረደ። የምድርና የዛፎች
አንድ ሦስተኛው፣እንዲሁም ለምለም አትክ
ልት ሁሉ ተቃጠሉ።
8 ሁለተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፣
አንድ ትልቅ የሚቃጠል ተራራ የሚመስል
ነገር በባሕር ላይ ወደቀ። የባሕርም አንድ
ሦስተኛው ደም ሆነ። 9 በባሕር ውስጥ ከሚ
ኖሩ ፍጥረቶች አንድ ሦስተኛው ሞቱ። በባ
ሕር ላይ ከሚገኙ መርከቦችም አንድ ሦስተ
ኛው ተደመሰሱ።
10 ሦስተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፣
እንደ ችቦ የሚቃጠል ትልቅ ኮከብ ከሰማይ
በወንዞችና በምንጮች አንድ ሦስተኛ ላይ
ወደቀ። 11 የኮከቡ ስም፣ «እሬቶ» ነበር።
በዚህ ኮከብ መውደቅ ምክንያት የውኃ
ሁሉ አንድ ሦስተኛው መራራ ሆነ። ብዙ
ሰዎችም ይህንን መራራ ውኃ ጠጥተው
ሞቱ።
12 አራተኛው መልአክ መለከቱን ሲነፋ፣
ከፀሐይ፣ከጨረቃና ከከዋክብት አንድ ሦስተ
ኛው ክፍል ከሰመ። ይሰጡት የነበረውም
ብርሃን ከበፊቱ በአንድ ሦስተኛ ቀነሰ። ስለ
ዚህ በቀንም በማታም ከነበረው ብርሃን
አንድ ሦስተኛው ተቀነሰ።
13 ከዚህ በኋላ አንድ ንስር በሰማይ ላይ
እየበረረ፣ ከፍ ባለ ድምፅ፣ «የቀሩት ሦስቱ
መላእክት መለከቶቻቸውን በሚነፉበት ጊዜ
በምድር ላይ አሰቃቂ ነገሮች ይፈጸማሉ።
ስለዚህ በምድር ላይ ለሚኖሩ ሁሉ ወዮላ
ቸው ፣ ወዮላቸው ፣ ወዮላቸው!» ሲል
ሰማሁ።

## ምዕራፍ 9

1 አምስተኛው መልአክ መለከቱን
ሲነፋ፣ ከሰማይ ወደ ምድር የወደቀ ኮከብ
አየሁ። የጥልቁ ጉድጓድ መክፈቻም ለኮ
ከቡ ተሰጠው። 2 በተሰጠው መክፈቻም
ጥልቁን ጉድጓድ ሲከፍት ከውስጡ በጣም
ብዙ ጢስ ወጥቶ አየሩን ሁሉ በከለው።
ፀሐይም በጢሱ ተሸፈነች።
3 ከጢሱም ውስጥ ብዙ አንበጣዎች
ወጥተው ምድርን አለበሱት። እንደ ጊንጦች
እንዲናደፉ ኃይል ተሰጣቸው። 4-5 በምድር
ላይ የበቀለውን ሣር ወይም ማናቸውንም
የለመለመ አትክልት እንዳይነኩ፣ ነገር ግን
የእግዚአብሔር ማኅተም በግምባራቸው ላይ
ያልታተመባቸውን ሰዎች ብቻ እንዲናደፉ
ተፈቀደላቸው። በእነርሱ የተነደፈ ማንኛ
ውም ሰው ሳይሞት ከፍተኛ የሆነ ሥቃይ
ለአምስት ወር ጊዜ እንዲሰማው እንዲያደ
ርጉ ታዘዙ። የሥቃዩም ዓይነት ሰው በጊ
ንጥ መርዝ ሲነደፍ እንደሚሰማው ዓይነት
ሕመም ነበር። 6 በእነዚህ አምስት የሥቃይ
ወራት ውስጥ ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ፤
ነገር ግን አያገኙትም። ለመሞት ይመኛሉ፤
ሞት ግን ይሸሻቸዋል።
7 አንበጣዎቹ ለጦርነት የተዘጋጁ ፈረሶች
ይመስሉ ነበር። በራሶቻቸው ላይ የወርቅ
ዘውድ የሚመስል ነገር ደፍተዋል። ፊታቸ
ውም የሰው ፊት ይመስላል። 8 ጠጉራቸው
እንደ ሴት ጠጉር ረጅም፣ ጥርሳቸውም
እንደ አንበሳ ጥርስ ጠንካራ ነበር። 9 ከብ
ረት የተሠራ ጥሩር የመሰለ የጦርነት ልብስ
ለብሰዋል። ከክንፎቻቸውም ውስጥ የሚወ
ጣው ድምፅ ወደ ጦርነት የሚገሠግሡ የፈ
ረሶችና የሠረገሎች ድምፅ ይመስላል።
10 አንበጣዎቹም እንደ ጊንጥ ሰዎችን ለአ
ምስት ወራት የሚያሠቃዩበት መናደፊያ
በጅራታቸው ላይ ነበር። 11 ንጉሥም ነበራ
ቸው፤ እርሱም የጥልቁ ጉድጓድ መልአክ
ነበር። ስሙ በዕብራይስጥ ቋንቋ፣ «አብ
ዶን» በግሪክ ቋንቋ «አጶልዮን» ይባል
ነበር። ትርጓሜውም «አጥፊ» ማለት ነው።
12 ይኸ የመጀመሪያው 'ወዮ' ፍጻሜ
ነው። ከዚህ በኋላ ደግሞ ሁለት 'ወዮ' ይከ
ተላል።
13 ስድስተኛው መልአክ መለከቱን
ሲነፋ፣በእግዚአብሔር ፊት ካለው በወርቅ
ከተሠራው መሠዊያ ቀንዶች ድምፅ ሲወጣ
ሰማሁ። 14 ድምፁም መለከት የያዘውን ስድ
ስተኛውን መልአክ፣ «በታላቁ የኤፍራጥስ

ወንዝ የታሠሩትን አራቱን መላእክት ፍታ
ቸው» አለው። 15 ታሥረው የነበሩት አራ
ቱም መላእክት ተፈቱ። እነዚህ መላእክት
የታሠሩት ይህች ሰዓት፥ቀን፥ወራትና ዓመት
እስክትደርስ ድረስ ነበር። ጊዜው በመድ
ረሱ የሰዎችን አንድ ሦስተኛ እንዲገድሉ
ተለቀቁ። 16 ቁጥራቸውን ሰማሁ። የተሰለፉ
ትም ሁለት መቶ ሚሊዮን የጦር ወታደ
ሮች ነበሩ።
17 በራእዬም፥ ፈረሶቻቸውንና በላያቸው
ተቀምጠው የሚጋልቡትን ደረታቸው ላይ
ያደረጉት ጥሩር እንደ እሳት ቀይ፥ «ያክ
ንት» እንደተባለው የከበረ ድንጋይ፥ሰማያ
ዊና እንደ «ድኝ» ደማቅ ብጫ የሆነ
መልክ ነበረው። የፈረሶቹም ራሶች የአንበሳ
ራስ ይመስሉ ነበር። ከአፋቸው እሳትና
ጢስ፥ዲንም ይወጣ ነበር። 18 በዚህ በሦስቱ
መቅሰፍቶች፥ ማለትም በእሳቱ፥ በጢሱና
በዲኑ ከሰው ልጆች መካከል አንድ ሦስተ
ኛው ተገደለ። 19 እነዚህ ፈረሶች መግደል
የሚችሉት ከአፋቸው በሚወጣው ኃይል
ብቻ ሳይሆን እንደ እባብ መንደፍና ማቁ
ሰል በሚችለው ጅራታቸውም ጭምር
ነበር።
20 በእነዚህ መቅሰፍቶች ከመሞት የተረ
ፉት ሰዎች ግን ንስሐ አልገቡም። እንዲ
ሁም አጋንንትንና መስማት፥ወይም ማየት፥
ወይም መሄድ የማይችሉትን ከወርቅ፥
ከብር፥ከናስ፥ከድንጋይና ከእንጨት የተሠሩ
ጣዖታትን ማምለካቸውን አልተዉም።
21 እንዲሁም የሰውን ነፍስ በማጥፋታቸው፥
ወይም በስርቆታቸው ወይም በአስማታቸ
ውና በዝሙት ሥራቸው ተጸጽተው ንስሐ
አልገቡም።

## ምዕራፍ 10

1 ከዚህ በኋላ አንድ ብርቱ መልአክ በደ
መና ተከቦ፥በራሱ ዙሪያ ቀስተ ደመና ተተ
ክሎ፥ ፊቱ እንደ ፀሐይ፥ እግሮቹም እንደ
እሳት ላንቃ እያበሩ ሲመጣ አየሁ። 2 በእጁ
አንዲት የተከፈተች ትንሽ ብራና ይዞአል።
መልአኩም ቀኝ እግሩን በባሕር ላይ፥ግራ
እግሩን በምድር ላይ ተክሎ 3 እንደሚያገሣ
አንበሳ ጮኸ፤በጮኸም ጊዜ ሰባቱ ነጐድጓ
ዶች በማስተጋባት መልስ ሰጡ።
4 እኔም ሰባቱ ነጐድጓዶች የተናገሩትን
ቃል በጽሑፍ ለማስፈር ሳስብ፥ ከሰማይ፥
«ሰባቱ ነጐድጓዶች የተናገሩት ቃል መገ
ለጽ ስለሌለበት እንዳትጽፍ!» የሚል
ድምፅ ሰማሁ።
5 እግሮቹን በባሕርና በምድር ላይ አሳ
ርፎ የነበረው መልአክ ቀኝ እጁን ወደ
ሰማይ ዘርግቶ፥ 6 ሰማይን፥ምድርን፥ባሕርንና
በእነርሱ ውስጥ የሚኖሩትን ሁሉ በፈጠ
ረው በዘላለማዊው አምላክ ስም ምሎ በመገ
ዘት እንዲህ አለ፥ 7 «ሰባተኛው መልአክ
መለከቱን በሚነፋበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር
በአገልጋዮቹ በነቢያት አንደበት የተናገረው
ምሥጢር ሁሉ ሳይዘገይ ይፈጸማል።»
8 ቀጥሎም ከሰማይ የሰማሁት ድምፅ፥
አሁንም እንደገና፥ «ሂድና እግሮቹን በባሕ
ርና በምድር ካሳረፈው መልአክ እጅ የተከ
ፈተችውን ብራና ተቀበል» አለኝ።
9 እኔም ወደ መልአኩ ቀርቤ፥ «ብራና
ዋን ስጠኝ» አልኩት። መልአኩም «እንካ
ውሰድና ብላት፥ስትበላት በአፍህ ላይ እንደ
ማር ትጣፍጥሃለች፤ከዋጥካት በኋላ ግን በሆ
ድህ ውስጥ እንደመራራ ትሆናለች» አለኝ።
10 እኔም ከመልአኩ እጅ ትንሿን ብራና
ወስጄ በላሁ። ስበላት፥በአፌ ውስጥ እንደ
ማር ጣፈጠችኝ። ከዋጥኳት በኋላ ግን
በሆዴ ውስጥ መረረችኝ።
11 ከዚህ በኋላ፥ «ስለብዙ ወገኖች፥ሕዝ
ቦች፥ ቋንቋዎችና ነገሥታት ትንቢት መና
ገር አለብህ» አለኝ።

## ምዕራፍ 11

1 የእግዚአብሔርን መቅደስና መሠዊ
ያው ያለበትን ውስጣዊ አደባባይ እንድለካ
በትር የመሰለ መለኪያ ተሰጠኝ። በመቅ
ደሱ ውስጥ የሚሰግዱትንም ሰዎች ብዛት
እንድቆጥር ተነገረኝ። 2 «ከቤተ መቅደሱ
ውጭ ያለው አደባባይ ግን ለአሕዛብ ስለ
ተሰጠ አትለካው። አሕዛብ ለአርባ ሁለት
ወራት ቅድስቲቱን ከተማ ይረግጡአ
ታል። 3 በዚያን ጊዜ ከማቅ የተሠራ ልብስ
የለበሱትን ሁለቱን ምስክሮቼን እልካለሁ።
እነርሱም ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ ስድሳ
ቀናት ትንቢት ይናገራሉ» የሚል ቃል
ተነገረኝ።
4 እነዚህ ሁለት ምስክሮች በምድር ገዢ
በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙት ሁለቱ የወ
ይራ ዛፎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።
5 እነርሱን ሊጐዱ የሚፈልጉትን ሁሉ ከአ
ፋቸው በሚወጣው እሳት ያጠፏቸዋል።
ሊጐዷቸው የሚሹ ሁሉ የሚሞቱት በዚህ
ዓይነት አሟሟት ነው። 6 ትንቢት በሚተነ
ብዩበት ሦስት ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ
ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ለመዝጋት ሥል
ጣን ተሰጥቶአቸዋል። እንዲሁም በፈለጉ

በት ጊዜ ውኃን ወደ ደም ለመለወጥና ልዩ
ልዩ መቅሰፍቶችን በምድር ላይ ለማውረድ
ይችላሉ።

7 ምስክርነታቸውን አሰምተው ከጨረሱ
በኋላ ከጥልቁ ጉድጓድ የሚወጣው አውሬ
ይዋጋቸውና ያሸንፋቸዋል ፤ ይገድላቸዋ
ልም። 8 ሬሳቸውም «ግብጽ» ወይም
«ሰዶም» እየተባለች በምሳሌያዊ አነጋገር
በምትጠራውና፣ጌታ ራሱ በተሰቀለባት በታ
ላቂቱ ከተማ አደባባይ ላይ ይጣላል። 9 የዓ
ለም ሕዝብ ሁሉ ለሦስት ቀን ተኩል ሬሳቸ
ውን ያያል፤ሬሳቸውም እንዳይቀበር ይቃወ
ማል። 10 በሕይወት በነበሩበት ጊዜ ባደረሱ
ባቸው ሥቃይ ምክንያት በሁለቱ ምስክሮች
መገደል በምድር የሚኖሩ ሰዎች ደስ ይላቸ
ዋል። ደስታውና ፈንጠዝያው ይቀልጣል፤
ሰዎችም እርስ በእርሳቸው ስጦታ ይለዋወ
ጣሉ።

11 ነገር ግን ከሦስት ቀን ተኩል በኋላ፣
የእግዚአብሔር የሕይወት እስትንፋስ የሁለ
ቱን ምስክሮች ሬሳ፣ነፍስ ዘርቶ እንዲነሣ
ያደርጋል። በዚህ ጊዜ ያዩዋቸው ሰዎች
በታላቅ ፍርሃት ይያዛሉ። 12 ከዚህም በኋላ
ሁለቱ ምስክሮች፣ «ወደዚህ ኑ» የሚል
ታላቅ ድምፅ ከሰማይ ይሰማሉ። ከዚያም
ጠላቶቻቸው እያዩአቸው በደመና ተከብ
በው ወደ ሰማይ ይወጣሉ።

13 በዚያኑ ሰዓት ታላቅ የምድር መና
ወጥ ይሆናል። ከከተማይቱ ሕንፃዎች መካ
ከል አንድ አሥረኛው ይፈራርሳል። ሰባት
ሺህ ሰዎችም በምድሩ መናወጥ ይሞታሉ።
ከሞት የተረፉትም በፍርሃትና በመንቀጥ
ቀጥ ለሰማዩ አምላክ ለእግዚአብሔር ክብር
ይሰጣሉ።

14 በዚህም ሁለተኛው ‘ወዮ’ ያልፍና
ወዲያውኑ ሦስተኛው ‘ወዮ’ ይተካል።

15 ሰባተኛው መልአክ፣መለከቱን ሲነፋ፣
ከሰማይ፣ «ከእንግዲህ ወዲህ፦የዓለምን መን
ግሥት የመግዛቱ ሥልጣን፣የጌታችን የእግ
ዚአብሔርና እርሱ የቀባው የክርስቶስ ይሆ
ናል። እርሱም ከዘላለም እስከ ዘላለም ይነግ
ሣል» የሚል ከፍተኛ ድምፅ ተሰማ።

16 በእግዚአብሔር ፊት በየዙፋኖቻቸው
የተቀመጡት ሃያ አራት ሽማግሌዎችም በግ
ምባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር በመ
ስገድ 17 እንዲህ አሉ፣ «ያለህና የነበርክ፣
ሁሉን የምትችል ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፣
በታላቁ ኃይልህና ሥልጣንህ ስለነገሥህ እና
መሰግንሃለን። 18 ሕዝቦች በአንተ ላይ
አመፁ። እነሆ ቁጣህ ወረደባቸው። በሙ
ታን ላይ የምትፈርድበትና ለአገልጋዮችህ፣
ለነቢያትና የአንተ ለሆነው ሕዝብህ፣ለሚፈ
ሩህ ለትልቁም ለትንሹም፣ዋጋቸውን የምት
ከፍልበት ጊዜ ደረሰ። በምድር ላይ ጥፋት
ያስከተሉትን የምታጠፋበት ዘመን መጣ።»

19 ከዚህ በኋላ በሰማይ ያለው የእግዚአብ
ሔር መቅደስ ተከፈተ። በመቅደሱም
ውስጥ የቃል ኪዳኑ ታቦት ታየ። ወዲያው
መብረቅና ነጐድጓድ ተሰማ። ታላቅ በረ
ዶም ጣለ። ኃይለኛ የሆነ የምድር መናወጥ
ዓለምን ከሥር ከመሠረቱ አናጋው።

## ምዕራፍ 12

1 ከዚህ በኋላ ታላቅና አስደናቂ ምልክት
በሰማይ ታየ። ፀሐይን የለበሰች፣ ጨረቃን
በእግሮችዋ የረገጠችና በራስዋ ላይ አሥራ
ሁለት ከዋክብት ያሉበት ዘውድ የደፋች
አንዲት ሴት አየሁ። 2 እርስዋም እርጉዝ
ስለነበረች ምጥ ይዟት ለመውለድ ታጣጥር
ነበር።

3 አንድ ሌላ ምልክት ደግሞ በሰማይ
ታየ። ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት፣
በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች የደፋ አንድ
ግዙፍ ቀይ ዘንዶ ታየ። 4 ዘንዶው የከዋክብ
ትን አንድ ሦስተኛ በጅራቱ ስቦ ከሰማይ
ወደ ምድር ጣላቸው። ቀጥሎም፣ ሴቲቱ
በምትወልድበት ጊዜ የሚወለደውን ልጅ
ለመዋጥ ፈልጎ ከሴትዮዋ ፊት ሄዶ ቆመ።
5 ሴቲቱም የዓለምን ሕዝቦች በብረት በትር
የሚገዛውን ወንድ ልጅ ወለደች። ልጁም
ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ፊት ተወ
ሰደ። 6 ሴቲቱም ለአንድ ሺህ ሁለት መቶ
ስድሳ ቀን እንድትሸሸግበት በበረሃ ውስጥ
እግዚአብሔር ወደ አዘጋጀላት ሥፍራ
ሸሸች።

7 ከዚህ በኋላ ሚካኤልና መላእክቱ በሰ
ማይ ላይ ዘንዶውን ጦርነት ገጠሙ። ዘንዶ
ውም ርኩሳን መናፍስትን አስከትሎ ከሚካ
ኤልና ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ። 8 ነገር ግን
ሊቋቋማቸው አልቻለም። በጦርነቱ ድል
ስለተመታ ከሰማይ ተባረረ። 9 ይህ ዘንዶ፣
«ዲያብሎስ» ወይም «ሰይጣን» በመባል
የታወቀውና ዓለምን ሁሉ የሚያሳስተው
የቀድሞው እባብ ነው። ዘንዶው ጭፍሮቹ
ከሆኑት መላእክት ጋር ወደ ምድር ተጣለ።

10 ከዚህ በኋላ አንድ ታላቅ ድምፅ ከሰ
ማይ እንዲህ ሲል አስተጋባ፤ «አሁን ማዳ
ንና ኃይል፣መንግሥትም የአምላካችን ሆኖ
አል። ሥልጣንም ለክርስቶስ ተሰጥቷል።
ምክንያቱም ወንድሞቻችንን ቀንና ሌሊት

በእግዚአብሔር ፊት የሚያሳጣቸው ከሳሽ
ወድቋል። 11 በበጉ ደም ኃይልና በሚመሰክ
ሩት ቃል ከሳሻቸውን ድል አድርገውታል።
በእምነታቸው ምክንያት ሞት ሳይበግራ
ቸው ሕይወታቸውን መሥዋዕት አድርገ
ዋል። 12 ስለዚህ ሰማይና በውስጥዋ የምት
ኖሩ ሁሉ ደስ ይበላችሁ። በምድርና በባ
ሕር የምትኖሩ ግን ወዮላችሁ። ዲያብሎስ
ጥቂት ጊዜ ብቻ እንደቀረው ስለሚያውቅ
በቁጣ ወደ እናንተ ወርዶአል።

13 ዘንዶው ወደ ምድር ከተጣለ በኋላ፥
ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት ማሳደድ
ጀመረ። 14 ሴቲቱ ከዘንዶው አምልጣ ለሦ
ስት ዓመት ተኩል ወደምትኖርበት በረሃ
እንድትበር የትልቁ ንስር ክንፎች ተሰ
ጧት።

15 ዘንዶው ሴትዮዋን ለመያዝ አሳደዳት፤
እንደ ወንዝ የሚጕርፍ ውኃ ከአፉ በመት
ፋት ጠልፎ ሊያጠፋት ሞከረ። 16 ይሁን
እንጂ ምድር ሴትዮዋን በመርዳት አፍዋን
ከፍታ ከዘንዶው የሚወጣውን ጅረት
ዋጠች። 17 ዘንዶው ሴቲቱን ለመያዝ ባለመ
ቻሉ ተናዶ፥የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚ
ጠብቁትንና ስለ ኢየሱስ የሚመሰክሩትን፥
የቀሩትን የሴትዮዋን ልጆች ለማጥቃት
ቆርጦ ተነሣ። በባሕር ዳር በሚገኝ በአሸ
ዋማ ሥፍራ ላይ ቆሞ አድብቶ ይጠብቅ
ጀመር።

## ምዕራፍ 13

1 ከዚያም አሥር ቀንዶችና ሰባት
ራሶች፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውድ
የጫነ አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ። በሰ
ባቱ ራሶች በእያንዳንዳቸው ላይ እግዚአብ
ሔርን የሚሳደቡ ጽሑፎች ተጽፈው ነበር።
2 ይህ አውሬ ቀርጹ ነብር ሲመስል፥እግሮቹ
የድብ፥አፉም የአንበሳ ይመስል ነበር። ዘን
ዶውም ለዚህ አውሬ ኃይሉን፥ ዙፋኑንና
ሥልጣኑን ሰጠው።

3 አውሬው፥ ከሰባቱ ራሶቹ በአንዱ ላይ
ለሞት የሚያደርስ ቁስል ነበረበት። ቁስ
ሉም ወዲያው ዳነለት። የዚህ ዓለም ሕዝበ
ችም በቁስሉ መዳን በመደነቅ አውሬውን
መከተል ጀመሩ። 4 ለአውሬው ሥልጣን
ለሰጠው ዘንዶም ሰገዱለት። «አውሬውን
ሊስተካከል የሚችል ማን ነው? ማንስ ሊቋ
ቋመው ይችላል?» እያሉ አውሬውን ማም
ለክ ያዙ።

5 አውሬው እግዚአብሔርን እንዲሳደብና
ለአርባ ሁለት ወራት የፈለገውን ነገር ሁሉ
እንዲያደርግ የሚያስችለውን ሥልጣን ከዘን
ዶው ተቀበለ። 6 ስለዚህ እግዚአብሔርን፥
የእግዚአብሔርን ስምና መቅደሱን፥በሰማይ
የሚኖሩትንም ሁሉ በስድብ አዋረደ። 7 እን
ዲሁም የእግዚአብሔርን ሰዎች እንዲወጋና
እንዲያሸንፋቸው፥ የምድርንም ነዋሪዎች
ሁሉ እንዲገዛ ሥልጣን ተሰጠው። 8 ዓለም
ሲፈጠር ጀምሮ፥በታረደው በግ የሕይወት
መጽሐፍ ውስጥ ስሞቻቸው ያልተጻፉ
ሰዎች ሁሉ ለአውሬው ይሰግዱለታል።

9 መስማት የሚችል የልቦና ጆሮ ያለው
ይስማ። 10 ለእሥር የተወሰኑት የእግዚአብ
ሔር ሰዎች ይታሠራሉ። ለሞት የተወሰኑ
ትም ይገደላሉ። የቅዱሳን ትዕግሥትና ታማ
ኝነት የሚፈተነው በዚያን የመከራና የጭን
ቀት ጊዜ ነው።

11 ቀጥሎም የበግ ቀንዶች የሚመስሉ
ሁለት ቀንዶች ያሉትና እንደ ዘንዶ የሚና
ገር ሌላ አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ።
12 ይህ አውሬ ከመጀመሪያው አውሬ በሚያ
ገኘው ሥልጣን ተግባሩን ያከናውናል።
ለሞት ከሚያደርስ ቁስል የዳነውን የመጀ
መሪያውን አውሬ፥ሰዎች ሁሉ እንዲያመል
ኩት ያደርጋል። 13 ሰዎች እያዩት ከሰማይ
እሳት እስኪያወርድ ድረስ አስደናቂ ተአም
ራትን ይሠራል። 14 ከመጀመሪያው አውሬ
ከተቀበለው ሥልጣን የተነሣ በሚያደርጋ
ቸው ምልክቶች፥በምድር የሚኖሩትን ሁሉ
ያሳስታል። በሰይፍ ቆስሎ ሳለ በሕይወት
ሊኖር ለቻለው ለመጀመሪያው አውሬ
ክብር፥ ሐውልት እንዲሠራለት ያደርጋል።
15 ይህ የኋለኛው አውሬ ለሐውልቱ የሕይ
ወት እስትንፋስ እንዲሰጠውም ሥልጣን
ይቀበላል። ይኸውም ሐውልቱ መናገር እን
ዲችልና ለእርሱም የማይሰግዱለት ሁሉ እን
ዲገደሉ ትእዛዝ ለመስጠት ነው።

16 ከዚህም ሌላ የኋለኛው አውሬ ታናና
ሾችንና ታላላቆችን፥ ሀብታሞችንና ድሆ
ችን፥ ጌታዎችንና አገልጋዮችን፥በቀኝ እጃ
ቸው ወይም በግምባራቸው ላይ የመጀመሪ
ያውን አውሬ ምልክት እንዲያደርጉ፥ያስገ
ድዳል። 17 የአውሬው ስም ወይም የስሙ
መለያ ቁጥር የሌለው ሰው፥ ምንም ነገር
መግዛትም ሆነ መሸጥ አይፈቀድለትም።
18 ይህንን የአውሬውን ምልክት እንቆቅልሽ
ለመፍታት ጥበብና እውቀት ይጠይቃል።
ጥበብና እውቀት ያለው ትርጉሙን መር
ምሮ ይድረስበት። የአውሬውን ስም የያዘው
መለያ ቁጥር ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት
(666) ነው።

## ምዕራፍ 14

1 ከዚህ በኋላ በጉን በጽዮን ተራራ ላይ
ቆሞ አየሁ። ከእርሱ ጋር የራሱና የአባቱ
ስም በግምባራቸው ላይ የተጻፈባቸው
አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች ነበሩ።
2 ከሰማይ እንደ ታላቅ ፏፏቴና እንደ ነጐ
ድጓድ የሚያስተጋባ ድምፅ ሰማሁ። የሰማ
ሁት ድምፅ፣ መዘምራን በበገና ታጅበው
እንደሚያሰሙት ዜማ ይመስል ነበር።
3 አንድ መቶ አርባ አራት ሺህ አባላት
ያሉት ይህ ታላቅ ሠራዊት በዙፋኑ፣በአራቱ
እንስሳትና በሃያ አራቱ ሽማግሌዎች ፊት
ቆሞ፣ ከዚህ ቀደም ተሰምቶ የማያውቅ
አዲስ ዜማ አሰማ። ይህንንም ዜማ ከእነዚህ
ከምድር ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት
ሺው በቀር ማንም ሊዘምረው አይችልም።
4 እነዚህ ከሴቶች ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙ
ነት ያልፈጸሙ ድንግሎች፣በጉንም ወደሚ
ሄድበት ሁሉ የሚከተሉና ከሰዎች መካከል
ተዋጅተው የእግዚአብሔርና የበጉ እንዲ
ሆኑ የተመረጡ የመጀመሪያ ፍሬዎች
ናቸው። 5 እነርሱም ምንም ዓይነት ቅጥፈት
ያልፈጸሙና ነቀፋ የሌለባቸው ናቸው።
6 አንድ ሌላ መልአክ በምድር ላይ ለሚ
ኖር ሕዝብ ሁሉ የሚነገር የዘላለም ወንጌል
ይዞ በሰማይ ሲበር አየሁ። 7 ድምፁንም ከፍ
አድርጎ፣ «እግዚአብሔርን ፍሩ፤ ክብርም
ስጡት። ሰማይን፣ምድርን፣ባሕርንና የውኃ
ምንጮችን ለፈጠረው አምላክ ስገዱለት።
ምክንያቱም እርሱ ፍርድ የሚሰጥበት ጊዜ
ደርሷልና» ይል ነበር።
8 ቀጥሎም ሌላ ሁለተኛ መልአክ፣ «የዓ
ለምን ሕዝቦች ሁሉ ከረከሰው ከዝሙትዋ
የወይን ጠጅ ያጠጣች፣ ታላቂቱ ባቢሎን
ወደቀች! ወደቀች!» እያለ የመጀመሪያ
ውን መልአክ ይከተለው ነበር።
9 ሌላም ሦስተኛ መልአክ ደግሞ እንዲህ
እያለ ተከተላቸው፤ «ለአውሬውና ለሐው
ልቱ የሚሰግድ፣ምልክቱ በግምባሩ ወይም
በእጁ ላይ እንዲታተም የሚፈቅድ፣ 10 የእ
ግዚአብሔርን የቁጣ ወይን ይጠጣል።
ይህም ወይን ምንም ነገር ሳይቀላቀልበት
በእግዚአብሔር የቁጣ ጽዋ ተሞልቶ ተቀ
ምጦአል። ይህን የሚያደርግ ሁሉ በቅዱ
ሳን መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን
ይቃጠላል። 11 ለአውሬውና ለሐውልቱ የሰ
ገዱ፣ የስሙም ምልክት የታተመባቸው
ሁሉ ቀንና ሌሊት ያለ ዕረፍት ይሠቃ
ያሉ። የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም
ሲጨስ ይኖራል።»
12 ይህም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚ
ጠብቁትንና ለኢየሱስም ታማኝ የሆኑትን
የእግዚአብሔር ሰዎች የበለጠ ጽናትና ትዕ
ግሥት እንዲኖራቸው ይገፋፋቸዋል።
13 ከሰማይ፣ «ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ
ያላቸውን እምነት እንደ ያዙ የሚሞቱ የተ
ባረኩ ናቸው ብለህ ጻፍ» የሚል ድምፅ
ሰማሁ። የእግዚአብሔርም መንፈስ፣
«አዎን፣የተባረኩ ናቸው፤ምክንያቱም ከድ
ካማቸው ሁሉ ያርፋሉ። የሠሩትም መል
ካም ምግባር ይከተላቸዋል» አለ።
14 ከዚህ በኋላ የሰውን ልጅ የሚመስል
በነጭ ደመና ላይ ተቀምጦ አየሁ። እርሱም
በራሱ ላይ የወርቅ ዘውድ ደፍቶ፣በእጁ ስለ
ታም ማጭድ ይዞ ነበር።
15 ሌላ መልአክ ከመቅደስ ወጥቶ ድም
ፁን ከፍ በማድረግ በነጭ ደመና ላይ የተቀ
መጠውን፣ «በምድር ያለው መከር ለአጨዳ
ደርሷል። ስለዚህ በማጭድህ እጨደው»
አለው። 16 በደመና ላይ የተቀመጠውም
ማጭዱን ወደ ምድር ሰነዘረ፤ መከሩንም
አጨደ።
17 ከዚህ በኋላ አንድ ስለታም ማጭድ
የያዘ መልአክ በሰማይ ካለው መቅደስ
ወጣ።
18 ቀጥሎም ዓለምን በእሳት ለማጥፋት
ሥልጣን የተሰጠው ሌላ መልአክ፣ከመሠዊ
ያው ወጣና ድምፁን ከፍ አድርጎ ስለታም
ማጭድ የያዘውን መልአክ እንዲህ አለው፣
«የወይኑ ፍሬ ለመቆረጥ ደርሷልና ማጭድ
ህን ወደ ምድር ሰንዝረህ የወይኑን ፍሬ
ቁረጥ» አለው። 19 መልአኩም ማጭዱን
ሰንዝሮ በምድር ላይ በቅሎ ያሸተውን የወ
ይን ፍሬ እየቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ቁጣ
መጭመቂያ ውስጥ ጣለው። 20 ወይኑም ከከ
ተማው ውጭ በሚገኘው የወይን መጭመ
ቂያ ውስጥ ገብቶ ተጨመቀ። ከፍታው
እስከ ፈረስ ልጓም የሚደርስ፣ርቀቱ ሦስት
መቶ ኪሎሜትር የሚሆን ደም ከመጭመቂ
ያው ውስጥ ወጥቶ ይጐርፍ ጀመር።

## ምዕራፍ 15

1 ሌላ ታላቅ አስደናቂ ምልክት በሰማይ
ታየኝ። የእግዚአብሔር የመጨረሻ የቁጣ
መቅሰፍት ያለበት ሰባት ጽዋ የያዙ ሰባት
መላእክት አየሁ። ይህም ትርእይት «የመ
ጨረሻ መቅሰፍት» የተባለበት ምክንያት፣
የእግዚአብሔር ቁጣ ማከተሚያ በመሆኑ
ነው።

2ከዚያም እንደ እሳት የሚንቀለቀል
የመስተዋት ባሕር የሚመስል ነገር ተንጣ
ሎ አየሁ። በአጠገቡም ፥ አውሬውንና
ሐውልቱን ድል ያደረጉት ፥ ምልክቱንና
ቁጥሩን አንቀበልም ያሉት ሁሉ ፥ከእግዚአ
ብሔር የተሰጣቸውን በገና ይዘው ቆመው
ነበር።
3-4እነርሱም፥የእግዚአብሔርን አገልጋይ
የሙሴን መዝሙር፥እንዲሁም የበጉን መዝ
ሙር እንዲህ እያሉ ይዘምሩ ነበር፥
«ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ
ሥራህ ታላቅና ድንቅ ነው። መንገድህ ትክ
ክልና እውነት ነው ፥ አንተ የሕዝቦች ሁሉ
ንጉሥ ነህ። ጌታ ሆይ ፥ አንተን የማይፈራ
ማን ነው? ስምህንስ የማያከብር የት ይገ
ኛል? አንተ ብቻ ቅዱስ ነህ ሕዝብ ሁሉ
ወደ አንተ ይመጣል፤ይሰግድልሃልም ምክን
ያቱም ጽድቅ የተሞላበት ሥራህ ተገልጧ
ልና።»
5ከዚህ በኋላ በሰማይ ያለው ቤተ መቅ
ደስ ፥ ይኸውም የምስክሩ ድንኳን ፥ ወለል
ብሎ ሲከፈት አየሁ።
6ሰባቱን መቅሰፍቶች የያዙት ሰባቱ
መላእክት ከተልባ እግር የተሠራ ንጹሕ
ነጭ ልብስ ለብሰው ፥ ወገባቸውን በወርቅ
መታጠቂያ ታጥቀው ከመቅደስ ወጡ።
7ከአራቱ እንስሳት አንዱ ለእነዚህ ሰባት
መላእክት ለዘላለም የሚኖረውን የሕያው
እግዚአብሔርን ቁጣ የተሞሉ ሰባት የወርቅ
ጽዋዎች ሰጣቸው። 8መቅደሱንም የእግዚአ
ብሔር ክብርና ኃይል ሞላው። ሰባቱ መላእ
ክት ሰባቱን መቅሰፍቶች አፍስሰው እስኪ
ጨርሱ ማንም ወደ መቅደስ መግባት አል
ቻለም።

## ምዕራፍ 16

1ከመቅደሱ ውስጥ፥ «ሄዳችሁ የእግዚአ
ብሔር ቁጣ የሞላባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች
በምድር ላይ አፍስሱ» የሚል ከፍተኛ
ድምፅ ሰባቱን መላእክት ሲያዛቸው ሰማሁ።
2ወዲያው የመጀመሪያው መልአክ
ከቤተ መቅደሱ ወጥቶ፥በያዘው ጽዋ ውስጥ
የነበረውን መቅሰፍት በምድር ላይ አፈሰሰ።
ለአውሬው ሐውልት የሰገዱትና የስሙን
መለያ ቁጥር የተቀበሉት ሁሉ ክፉኛ በሚነ
ዘንዝ ቁስል ተበከሉ።
3ሁለተኛው መልአክ ፥ በያዘው ጽዋ
ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት በባሕር ላይ
አፈሰሰ። ባሕሩም እንደ ረጋ ደም ሆነ። በባ
ሕር ውስጥ የሚኖሩ ፍጥረቶች ሁሉ ሞቱ።
4ሦስተኛው መልአክ ፥ በያዘው ጽዋ
ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት በወንዞችና
በምንጮች ላይ አፈሰሰ። ወንዞችና ምን
ጮች ወደ ደም ተለወጡ። 5በውኃዎች
ላይ ሥልጣን የተሰጠው መልአክም፥ «ያለ
ህና የነበርክ ቅዱስ ጌታ ሆይ፥ፍርድህ ትክ
ክለኛና እውነተኛ ነው። 6እነዚህ ሰዎች
የቅዱሳንንና የነቢያትን ደም አፍስሰው
ነበር። አንተም በአጸፋው ደም እንዲጠጡ
አድርገህ ተገቢ የሆነ ፍርድ ሰጠሃቸው»
አለ።
7ወዲያውም ከመሠዊያው ውስጥ ፥
«ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥አዎን፥
ፍርድህ ትክክልና እውነተኛ ነው» የሚል
ድምፅ ሰማሁ።
8አራተኛው መልአክ በያዘው ጽዋ
ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት በፀሐይ ላይ
አፈሰሰ። ፀሐይም የነበራትን ግለት ከፊት
ይልቅ በጣም ጨምራ ሰዎችን እንድታቃ
ጥል ኃይል ተሰጣት። 9ሰዎችም በፀሐይ
ትኩሳት ተቃጠሉ። ነገር ግን በመቅሰፍቶቹ
ላይ ሥልጣን የነበረውን የእግዚአብሔርን
ስም ከመርገም በቀር ፥ በንስሐ ተመልሰው
የሚገባውን ክብር አልሰጡትም።
10አምስተኛው መልአክ በያዘው ጽዋ
ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት ፥ ከባሕር በወ
ጣው አውሬ ዙፋን ላይ አፈሰሰ። የአውሬ
ውም ግዛት በጨለማ ተዋጠች። ሰዎችም
ሥቃይ ስለበረታባቸው ጥርሳቸውን ያፋጩ
ጀመር። 11ከክፉ ሥራቸው ንስሐ ሊገቡ
ግን አልፈለጉም። እንዲያውም ስለ ደረሰባ
ቸው ሥቃይና ስለ ወረራቸው ቁስል እግዚ
አብሔርን ይረግሙ ነበር።
12ስድስተኛው መልአክ ፥ በያዘው ጽዋ
ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት ኤፍራጥስ በተ
ባለው ታላቅ ወንዝ ላይ አፈሰሰ። የምሥ
ራቅ ነገሥታት ያለ ምንም ችግር ከነሠራዊ
ቶቻቸው መዝመት ይችሉ ዘንድ ወንዙ
ደረቀ። 13ከዚያም ከዘንዶው አፍ ፥ ከአው
ሬው አፍና ከሐሰተኛው ነቢይ አፍ እንቁራ
ሪት የመሰሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት
ሲወጡ አየሁ። 14እነዚህም ተአምራት
መሥራት የሚችሉ ርኩሳን መናፍስት፥የዓለ
ምን መንግሥታት አከማችተው በኃያሉ በእ
ግዚአብሔር ቀን ጦርነት እንዲያነሡ ያግባ
ቧቸው ጀመር።
15«እነሆ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ።
ነገር ግን ከእንቅልፍ ነቅተው ልብሳቸውን
ለብሰውና ተዘጋጅተው የሚጠብቁኝ የተባ
ረኩ ናቸው። እነርሱ ራቁታቸውን አይሆ

ኑም፥በአደባባይ ላይም አይዋረዱም።»
16 ርኩስ መንፈሶቹም የዓለም መንግሥ
ታትን ጦር፥ ‘ክተት ሠራዊት’ አሰኝተው
በዕብራይስጥ ቋንቋ፥ «አርማጌዶን» በተባ
ለው ሥፍራ አከማቹ።
17 ከዚህ በኋላ ሰባተኛው መልአክ በያ
ዘው ጽዋ ውስጥ የነበረውን መቅሰፍት በአ
የር ላይ አፈሰሰ። በዚህ ጊዜ በቤተ መቅ
ደሱ ውስጥ ካለው ዙፋን፥ «ተፈጸመ!»
የሚል ኃያል ድምፅ ተሰማ። 18 ወዲያውም
የመብረቅና የነጐድጓድ ድምፅ አስተጋባ።
ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ታይቶም ተሰም
ቶም የማይታወቅ ታላቅ የምድር መናወጥ
ሆነ። 19 ታላቂቱም ከተማ ከሦስት ቦታ ተከ
ፈለች። በዓለም የሚገኙ ትልልቅ ከተሞ
ችም በመሬቱ መናወጥ ምክንያት ፈራረሱ።
እግዚአብሔር የታላቂቱን ባቢሎን ኃጢአት
አስታውሶ በቁጣው ወይን የተሞላውን ጽዋ
ሰጣት። 20 ደሴቶች ከዓይን ጠፉ፤ተራራዎ
ችም እንደ ሜዳ ተዘረጉ። 21 ከሰማይም እያ
ንዳንዳቸው አርባ ኪሎ የሚመዝኑ የበረዶ
ኳሶች በሰዎች ላይ ይወርዱ ጀመር።
ሥቃዩ ከባድ ነበርና ሰዎችም በወረደው
ከባድ በረዶ ምክንያት እግዚአብሔርን ተራ
ገሙ።

## ምዕራፍ 17

1 ሰባቱን መቅሰፍቶች በምድር ላይ ካፈ
ሰሱት ሰባት መላእክት አንዱ፥ወደ እኔ ጠጋ
ብሎ እንዲህ አለኝ፤ «ወደዚህ ና፤በብዙ
ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታወቀች
ውን አመንዝራ ሴት የመጨረሻ ፍርድ አሳ
ይሃለሁ። 2 የዓለም መንግሥታት መሪዎች
ሁሉ ከእርስዋ ጋር አመንዝረዋል። ሰዎችም
ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ጠጥተው ሰክረ
ዋል።»
3 ቀጥሎ መልአኩ በመንፈስ ወደ በረሃ
ወሰደኝና በቀይ አውሬ ላይ የተቀመጠች
ውን ሴት አሳየኝ። ይህች ሴት የተቀመጠች
በት አውሬ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች
ነበሩት። በራሶቹም ላይ እግዚአብሔርን
የሚሳደቡ ብዙ ጽሑፎች ይታያሉ።
4 ሴቲቱ ቀይና ሐምራዊ ልብስ ለብሳ፥በወ
ርቅ፥በዕንቁና በከበሩ ድንጋዮችም አጊጣ
ነበር። በአጸያፊ ሥራዎችዋና በዝሙት ርኩ
ሰቶቿ የተሞላ የወርቅ ጽዋ በእጅዋ ይዛ
ነበር። 5 በግምባርዋም ላይ፥ «ታላቂቱ ባቢ
ሎን! በመላው ዓለም የሚኖሩ የአመንዝሮ
ችና የምድር ርኩሰቶች ሁሉ እናት»
የሚል ምሥጢራዊ ጽሑፍ ተጽፎ ነበር።
6 እኔም ይህች ሴት ባስገደለቻቸው በሰማ
ዕታትና በኢየሱስ ምስክሮች ደም ሰክራ
በማየቴ፥በመገረም ትኩር ብዬ ተመለከት
ኋት።
7 መልአኩ ግን የሚከተለውን ተናገረኝ፤
«እንዲህ የሚያስገርምህ ምንድን ነው?
ሴቲቱ ማን እንደሆነች፥የተቀመጠችበትም
ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶች ያሉት አውሬ
ምን እንደሆነ ምሥጢሩን እነግርሃለሁ።
8 ይህ የምታየው አውሬ በሕይወት ይኖር
ነበር። አሁን ግን በሕይወት የለም። ይሁን
እንጂ በቅርቡ ካለበት ከጥልቁ ጉድጓድ
ይወጣል። ወደ ጥፋትም ይወርዳል። ዓለም
ከተፈጠረ ጀምሮ ስማቸው በሕይወት መጽ
ሐፍ ያልተጻፈ ሰዎች፥ይህ አውሬ አስቀ
ድሞ እንደነበረ፥በኋላ እንደሌለ፥አሁን
ደግሞ እንደገና በሕይወት እንደሚኖር
ሲያዩ ይደነቃሉ።
9 «ይህንን ምሥጢር ለመረዳት የምነግር
ህን በጥሞና አድምጥ። የአውሬው ሰባት
ራሶች ሴቲቱ የምትኖርባቸው ሰባት ኮረብ
ቶች ናቸው። 10 በተጨማሪም ሰባቱ ራሶች
ሰባት ነገሥታት ናቸው። ከሰባቱ ነገሥታት
መካከል አምስቱ ከዚህ በፊት አልፈዋል።
አንዱ በሥልጣን ላይ ይገኛል። አንደኛው
ደግሞ ወደ ፊት ይነግሣል። ይሁን እንጂ
በሥልጣን ላይ የሚቆየው ለጥቂት ጊዜ
ብቻ ነው። 11 ሞቶ የነበረው ቀዩ አውሬ
ስምንተኛው ንጉሥ ነው። እርሱ ከሰባቱ
አንዱ ነው፤በኋላም ወደ መጨረሻ ጥፋቱ
ይወርዳል። 12 ያየሃቸው አሥር ቀንዶች ገና
በሥልጣን ላይ ያልተቀመጡት አሥር ነገ
ሥታት ናቸው። ነገር ግን እነርሱ ከአው
ሬው ጋር ለአንድ ሰዓት በሥልጣን ላይ
ይቀመጣሉ። 13 አንድ ዓይነት ዓላማ ስላላ
ቸው ሥልጣናቸውንና ኃይላቸውንም ለአ
ውሬው አሳልፈው ይሰጡታል። 14 እነዚ
ህም ነገሥታት በኅብረት ሆነው በጉን ይወ
ጋሉ። ነገር ግን በጉ የጌቶች ጌታና የነገሥ
ታት ንጉሥ በመሆኑ፥ድል ያደርጋቸዋል።
ከዓለም የተጠሩ፥የተመረጡና የታመኑ
የበጉ ተከታዮችም፥ከበጉ ጎን ይቆማሉ።»
15 ቀጥሎም መልአኩ እንዲህ አለኝ፥
«ሴቲቱ ተቀምጣበት ያየኸው ውኃ ከየሕ
ዝቡ፥ከየቋንቋውና ከየወገኑ የተውጣጡ
ሰዎች ምሳሌ ነው።
16 «ቀዩ አውሬና ያየሃቸው አሥር ቀን
ዶች አመንዝራይቱን ሴት ስለሚጠሉአት
ይወጓታል። ራቁቷንም ያስቀሩአታል፤ሥጋ
ዋንም ይበሉታል፤በእሳትም ያቃጥሏታል።

17 እንዲሁ የሆነበትም ምክንያት፥ እግዚአብ
ሔር የተናገረው ቃል እስኪፈጸም ድረስ
አሳባቸውን አንድ አድርገው የአገዛዝ ሥል
ጣናቸውን ለአውሬው ለመስጠት እንዲስ
ማሙ፥ የእግዚአብሔር እቅድ በመሆኑ
ነው። 18 ያየሃትም ሴት የዓለምን ነገሥታት
አሽቆጥቁጣ የምትገዛዋ የታላቂቱ ከተማ
ምሳሌ ናት።»

## ምዕራፍ 18

1 ከዚህ በኋላ ታላቅ ሥልጣን ያለው ሌላ
መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ። ከክብ
ሩም የተነሣ ምድር በብርሃን ተጥለቀለ
ቀች። 2 መልአኩም ድምፁን ከፍ አድርጎ፥
«ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፤ወደቀች! የአጋ
ንንት መሰብሰቢያ፥ የርኩሳን መናፍስት
ሁሉ መኖሪያና የአጸያፊ አእዋፍ ሁሉ
መጠጊያ ሆነች። 3 የዓለም ሕዝቦች በሙሉ
ከዝሙት ጽዋዋ ጠጥተው ሰክረዋል። የም
ድር ነገሥታት ከእርሷ ጋር አመንዝረዋል።
የምድር ሀብታሞችም በኃይልዋና በምቾ
ትዋ ተንደላቀዋል» ሲል ጮኸ።
4 በዚህ ጊዜ ከሰማይ እንዲህ የሚል ሌላ
ድምፅ ሰማሁ፥ «ሕዝቤ ሆይ፥ከእርሷ ጋር
አብራችሁ እንዳትቀጡ፥የባቢሎን ኃጢአት
ተባባሪዎች አትሁኑ፤ከእርስዋም ሽሽታችሁ
ውጡ። 5 ምክንያቱም ኃጢአትዋ እስከ
ሰማይ ድረስ ተከምሮአል። እግዚአብሔርም
ያደረገችውን ዓመፅ ተመልክቶአል። 6 እንደ
ሥራዋ መጠን መልሱላት፥ ላደረገችውም
እጥፉን ክፈሏት። የቀላቀለችውንም ጽዋ
እጥፍ ኃይለኛ አድርጉባት። 7 በደስታና
በምቾት ትኖር ነበር። አሁን ግን ሥቃይና
ኀዘን ትቀበላለች። በልብዋ፥ 'እኔ ንግሥት
ነኝ፤የማንም መበለት አይደለሁም፤ኀዘንም
አይነካኝም' ብላ ታስባለች። 8 ስለዚህ በአ
ንድ ቀን ሞት፥ኀዘንና ረሃብ ያጠፉአታል።
የሚፈርድባት ጌታ እግዚአብሔር ብርቱ
ስለሆነ በእሳት ትቃጠላለች።»
9 ከባቢሎን ጋር ያመነዘሩ የዓለም መንግ
ሥታት መሪዎች፥ባቢሎን ስትቃጠልና ስት
ጨስ ሲያዩ ስቅስቅ ብለው ያለቅሱላታል።
10 ሥቃይዋን በማየታቸው በሩቅ ቆመው፥
«ከእንግዲህ የባቢሎን ነገር አከተመ። ያቺን
የመሰለች ታላቅ ከተማ እንዲህ በአንድ
ሰዓት ውስጥ ትውደም? ወይ ባቢሎን!»
እያሉ ሙሾ ያወርዱላታል።
11 የዓለም ነጋዴዎችም በባቢሎን መጥ
ፋት የተነሣ ሸቀጣ ሸቀጣቸውን የሚገዛ
ቸው ባለመኖሩ ያዝናሉ፤ ያለቅሳሉም።
12 ወርቅ፥ብር፥የከበረ ድንጋይ፥ዕንቁ፥ከተ
ልባ እግርና ከሐር የተሠራ ጨርቃ ጨርቅ፥
የሚሸተት እንጨት፥ከዝሆን ጥርስ የተሠራ
ዕቃና ከእንጨት፥ከናስ፥ከብረትና ከዕብነ
በረድ የተሠሩ ልዩ ልዩ ዕቃዎች፥
13 ቀረፋ፥ቅመም፥ሽቶ፥ቅባት፥ዕጣን፥የወይን
ጠጅ፥ዘይት፥ዱቄትና ጥራጥሬ፥ከብቶች
በጎች፥ፈረሶች፥ሠረገላዎች፥ሎሌዎችና
የሰው ነፍስ እንኳን ሳይቀር የምትገዛ፥ደም
በኛቸው ባቢሎን ነበረች።
14 ነጋዴዎቹም፥ «ትወጂያቸው የነበ
ሩት የቅንጦት ዕቃዎች ሁሉ ቀሩ። ቀድሞ
የነበረሽ ክብርና ሞገስ ዘበት ሆነ። የቀድ
ሞው ክብርሽ ሁለተኛ አይመለስም!»
እያሉ ያዝናሉ።
15 እነዚያ ሸቀጣ ሸቀጥ ለእርስዋ በመ
ሸጥ የከበሩት ነጋዴዎች በሩቅ ቆመው እያ
ለቀሱና፥ 16 «ኧረ ወየው! ውብና ስስ፥ቀይ፥
ሐምራዊ፥ሐር የለበሰች፥በወርቅ፥በከበረ
ድንጋይና በዕንቁዎች ያጌጠች ሴት ወይ
ዘር፥የምትመስለዋ ታላቂቱ ከተማ፥ 17 ያ
ሁሉ ሀብቷና ግርማዋ በአንድ ሰዓት እንዳ
ልነበረ ሆነ!» እያሉ ያዝኑላታል። የመር
ከብ አዛዦች፥በመርከብ ተሳፍረው የሚሄዱ
መንገደኞች የመርከብ ነጂዎችና ነጋዴዎች
ሁሉ በሩቅ ሆነው 18 ባቢሎን ስትቃጠልና
ስትጨስ ሲያዩ፥ «ዋ፥እንደ ባቢሎን ያለ
ታላቅ ከተማ የት ይገኛል?» እያሉ አዘኑ።
19 ኀዘናቸውን ለመግለጽ አቧራ በራሳቸው
ላይ እየነሰነሱና እያለቀሱ፥ «ወየው ታላ
ቂቱ ከተማ ባቢሎን! በአንድ ሰዓት ውስጥ
እንዳልነበረች ሆነች! ከታላቅ ሀብቷ እኛን
መርከበኞቹን አካፍላን ሀብታም ያደረገችን
ታላቅ ከተማ ነበረች!» አሉ።
20 ነገር ግን ሰማያት ሆይ፥ ደስ ይበላ
ችሁ፤እናንተ ቅዱሳን፥ሐዋርያትና ነቢያት
ሆይ፥ደስ ይበላችሁ፤እግዚአብሔር በእናንተ
ላይ ስላደረሰችው ክፉ ሁሉ በባቢሎን ላይ
ፈርዶባታል፤ ፍትሕ እንድታገኙም አድር
ጓል።
21 ከዚህ በኋላ አንድ ብርቱ መልአክ
ከባድ የወፍጮ መጅ የመሰለ ድንጋይ አነ
ሳና ወደ ባሕር ወርውሮ እንዲህ አለ፥
«ታላቂቱ የባቢሎን ከተማ እንደዚህ ተገ
ፍታ ትወድቃለች፤ለዘላለምም ትጠፋለች።
22 ከእንግዲህ ወዲህ በእርስዋ ውስጥ ምንም
ዓይነት የበገና መቺዎች፥የአዝማሪዎች፥የዋ
ሽንት ተጫዋቾችና የጥሩንባ ነፊዎች
ድምፅ አይሰማም። የእጅ ሥራዎችን የሚ
ሠራ ብልሃተኛ ሰው ከእንግዲህ በክልልሽ

ውስጥ አይገኝም። የወፍጮ ድምፅም ዳግ
መኛ አይሰማብሽም። 23 ከእንግዲህ ምንም
ዓይነት ብርሃን አይበራብሽም። የሙሽራ
ወይም የሙሽሪት ድምፅ አይሰማብሽም።
ነጋዴዎችሽ የዓለም ታላላቅ ሰዎች ነበሩ።
በአስማትሽም የዓለምን ሕዝቦች ሁሉ አሳስ
ተሽ ነበር። 24 በእርሷም ውስጥ፣የነቢያትና
የቅዱሳን እንዲሁም በምድር የተገደሉት
ሁሉ ደም ተገኝቷል።»

## ምዕራፍ 19

1 ከዚህ በኋላ የብዙ ሰዎች ድምፅ ከሰ
ማይ እንዲህ ሲል ሰማሁ ፤ «ሃሌ ሉያ!
ድል ፣ ክብር ፣ ኃይልም የአምላካችን ነው።
2 እርሱ ትክክለኛና እውነተኛ ፈራጅ ነው።
በዝሙትዋ ምድርን ያረከሰችውን ያቺን
አመንዝራ ፈርዶባታል። ስለ አገልጋዮቹም
ደም ተበቅሏታል»።
3 እንደገናም፣ «ጌታ ይመስገን! ታላቂቱ
ከተማ ስትቃጠል ጢስዋ ለዘላለም ወደ ላይ
እየጨሰ ይወጣል» እያሉ ጮኹ።
4 ሃያ አራቱ ሽማግሌዎችና አራቱ እንስ
ሳት በግምባራቸው ተደፍተው ፣ «አሜን፣
እግዚአብሔር ይመስገን!» እያሉ በዙፋኑ
ላይ ለተቀመጠው ሰገዱለት።
5 ከዚህ በኋላ፣ «እናንተ የምትፈሩት አገ
ልጋዮቹ ሁሉ ታናናሾችና ታላላቆች እግዚ
አብሔር አምላካችንን አመስግኑ» የሚል
ድምፅ ከዙፋኑ ተሰማ።
6 ቀጥሎም እንደ ብዙ ሕዝብ ድምፅ ፣
እንደ ውቅያኖስ ማዕበል ፣እንደ ብርቱ ነጐ
ድጓድ የሚያስተጋባ ድምፅ እንዲህ ሲል
ሰማሁ፤ «ሃሌ ሉያ፣ሁሉን የሚገዛ ጌታ አም
ላካችን ይነግሣል። 7 የበጉ ሠርግ ስለደረሰ፣
ሙሽራዋም ስለተዘጋጀች ደስ ይበለን፤ሐሴ
ትም እናድርግ፤ክብርም እንስጠው። 8 ሙሽ
ራዋም የቅዱሳን መልካም ምግባር ምሳሌ
የሆነውን ከተልባ እግር የተሠራ ነጭና
ንጹሕ የሙሽራ ልብስ እንድትለብስ ተሰ
ጣት።»
9 ከዚህ በኋላ መልአኩ ፣ «‘ወደ በጉ
ሠርግ የተጠሩ የተባረኩ ናቸው’ ብለህ
ጻፍ» አለኝ። ቀጥሎም ፣ «ይህ የእግዚአብ
ሔር እውነተኛ ቃል ነው» አለኝ።
10 እኔም ልሰግድለት ከእግሩ ሥር ተደ
ፋሁ። እርሱ ግን፣ «ተው ፣ተው! ለእኔ አት
ስገድ! እኔ እንደ አንተና እንደ ሌሎቹ ስለ
ኢየሱስ የሚመሰክሩ ወንድሞችህ፣የእግዚአ
ብሔር አገልጋይ ነኝ። መስገድ የሚገባህ
ለእግዚአብሔር ብቻ ነው። ነቢያትን በትን
ቢት መንፈስ የሚሞላቸው በክርስቶስ የተገ
ለጠው እውነት ነው» አለኝ።
11 ከዚህ በኋላ ሰማያት ተከፍተው አንድ
ነጭ ፈረስ አየሁ። በፈረሱ ላይ፣ «ታማኝና
እውነተኛ» የሚባል ሰው ተቀምጦ ነበር።
እርሱ በጽድቅ ይፈርዳል ፤ ይዋጋልም።
12 ዓይኖቹ የእሳት ነበልባል ይመስላሉ።
በራሱም ላይ ብዙ ዘውድ ደፍቶ ነበር። በግ
ምባሩም ላይ ከእርሱ በቀር ማንም የማያው
ቀው ስም ተጽፎ ነበር። 13 እንዲሁም
በደም የተነከረ ልብስ ለብሶአል። ስሙም፣
«የእግዚአብሔር ቃል» ይባላል። 14 የሰማ
ይም ሠራዊት ከተልባ እግር የተሠራ ነጭና
ንጹሕ ልብስ ለብሰው በነጫጭ ፈረሶች ላይ
ተቀምጠው ተከትለውታል።
15 ከአፉም ሕዝቦችን የሚመታበት ስለ
ታም ሰይፍ ይወጣል። በብረትም በትር ይገ
ዛቸዋል። የእግዚአብሔርንም የቁጣ ወይን
መጭመቂያ ይረግጣል። 16 በልብሱና በጭኑ
ላይ ፣ «የንጉሦች ንጉሥና የጌቶች ጌታ»
የሚል ጽሑፍ ተጽፎበታል።
17 ቀጥሎም አንድ መልአክ በፀሐይ ላይ
ቆሞ አየሁ። እርሱም ድምፁን ከፍ አድርጎ
በሰማይ የሚበርሩትን ወፎች፣ «ወደ ታላቁ
የእግዚአብሔር ግብዣ ኑ ተሰብሰቡ! 18 የነ
ገሥታትን ሥጋ፣የጦር መሪዎችን ሥጋ፣የጀ
ግኖችን ሥጋ ፣ የፈረሶችንና የፈረስ ጋላቢዎ
ችን ሥጋ፣የልዩ ልዩ ሰዎችን ሥጋ፣የአገል
ጋዮችን ፣ የጌቶችን ፣ የትንሹን የትልቁንም
ሥጋ ብሉ!» ሲል በጩኸት ጠራቸው።
19 ከዚህ በኋላ አውሬውና የዓለም መንግ
ሥታት መሪዎች ፣ የጦር ሠራዊቶቻቸውም
በነጩ ፈረስ ላይ የተቀመጠውንና የእርሱን
ሠራዊት ለመውጋት ፣ ተሰብስበው አየሁ።
20 አውሬውና በአውሬው ፊት ብዙ ተአም
ራት እያደረገ ሰዎች የአውሬውን ምልክት
እንዲቀበሉና ለሐውልቱም እንዲሰግዱ የሚ
ያሳስተው ሐሰተኛ ነቢይ ተያዙ። ሁለቱም
በሕይወት እያሉ በዲን ወደሚቃጠል የእ
ሳት ባሕር ተጣሉ። 21 ከአውሬው ጋር ተሰ
ልፈው የነበሩትም ሠራዊት በሙሉ በነጭ
ፈረስ ላይ ከተቀመጠው አፍ በሚወጣው
ስለታም ሰይፍ አለቁ። የሰማይም ወፎች
ተሰብስበው ሥጋቸውን እስኪጠግቡ ድረስ
በሉ።

## ምዕራፍ 20

1 የጥልቁን አዘቅት መክፈቻና ትልቅ ሰን
ሰለት የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ
አየሁ። 2 እርሱም ፣ «ዲያብሎስ» ወይም

«ሰይጣን» የተባለውን ዘንዶ ፥ ያንን የድሮ
ውን እባብ ይዞ ለሺህ ዓመት አሠረው።
3 ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በዚያው
እንዲቆይ ወደ ጥልቁ አዘቅት ውስጥ
ጣለው። እንዳይወጣም ዘጋበትና በሩን በማ
ኅተም አሸገው። መልአኩ ይህንን ያደረገ
ውም ዲያብሎስ ሺው ዓመት እስኪፈጸም
ድረስ ሕዝብን እንዳያሳስት ነበር። ነገር ግን
ሺህ ዓመት ከተፈጸመ በኋላ ለአጭር ጊዜ
ይፈታል።
4 ከዚህ በኋላ ዙፋኖችን አየሁ። በዙፋ
ኖቹ ላይ ለመፍረድ ሥልጣን የተሰጣቸው
ተቀምጠዋል። እንዲሁም ፥ ስለ እግዚአብ
ሔር ቃልና ስለኢየሱስ በመመስከራቸው ፥
አንገታቸው የተሰየፈባቸውን ሰዎች ነፍስ
አየሁ። እነርሱም ፥ ለአውሬውና ለሐውልቱ
አልሰገዱም ፥ ምልክቱንም በግምባራቸው
ወይም በእጃቸው አላደረጉም ነበር። እነ
ርሱ ከሞት ተነሥተው ሺህ ዓመት ከክርስ
ቶስ ጋር ነገሡ።
5 ይህ የመጀመሪያው ትንሣኤ ነው። የቀ
ሩት ሙታን ግን ሺው ዓመት እስኪፈጸም
ድረስ ከሞት አይነሡም። 6 በመጀመሪያው
ትንሣኤ ከሞት የሚነሡ የተባረኩና የተቀ
ደሱ ናቸው። ሁለተኛው ሞት በእነርሱ
ላይ ሥልጣን የለውም። እነርሱ የእግዚአብ
ሔርና የክርስቶስ ካህናት ሆነው ከእርሱ
ጋር ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።
7 ሺው ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከታሠረ
በት ይፈታል። በአራቱ የዓለም ማዕዘን የሚ
ኖሩትን ሕዝቦች ፥ 8 ጎግና ማጎግን እያሳተ ፥
ለጦርነት ያሰልፋቸዋል። የሠራዊታቸውም
ቁጥር እንደ ባሕር አሸዋ የበዛ ይሆናል።
9 እነርሱም በምድር ሁሉ ተሠራጭተው
የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ሠፈርና የእግዚአ
ብሔርን ተወዳጅ ከተማ ኢየሩሳሌምን ይከ
ባሉ። ነገር ግን እግዚአብሔር ከሰማይ
እሳት አውርዶ ያጠፋቸዋል።
10 ያሳታቸው ዲያብሎስም እንደገና ይያ
ዛል። አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወደ
ተጣሉበት ወደ እሳት ባሕር ይጣላል። በዚ
ያም ቀንና ሌሊት ከዘላለም እስከዘላለም
ይሠቃያሉ።
11 ቀጥሎም ትልቅ ነጭ ዙፋንና በዙፋ
ኑም ላይ የተቀመጠውን አየሁ። ምድርና
ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ፤ ሁለተኛም አልታ
ዩም። 12 ታላላቆችና ታናናሾች ሙታንም
ከሞት ተነሥተው በዙፋኑ ፊት ቆመው
አየሁ። መጻሕፍት ተከፈቱ። እንዲሁም ፥
«የሕይወት መጽሐፍ» የተባለው ሌላ መጽ
ሐፍ ተከፈተ። ሙታንም እያንዳንዳቸው
በመጻሕፍቱ ውስጥ ተጽፎ በተገኘው መሠ
ረት ፥ እንደ ሥራቸው መጠን ተፈረደባ
ቸው። 13 ባሕርም በውስጡ ሰጥመው የነበ
ሩትን ሙታን አስረከበ። ሞትና ሲዖልም
ከሥልጣናቸው ሥር የነበሩትን ሙታን አስ
ረከቡ። እያንዳንዱም ሰው እንደ ሥራው
መጠን ተፈረደበት። 14 ከዚህ በኋላ ሞትና
ሲዖል ወደ እሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ።
ይህ የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው።
15 ስሙ በሕይወት መጽሐፍ ተጽፎ ያልተ
ገኘ ማንኛውም ሰው ፥ ወደ እሳት ባሕር
ውስጥ ተጣለ።

## ምዕራፍ 21

1 ከዚህ በኋላ አዲስ ሰማይና አዲስ
ምድር አየሁ። የመጀመሪያው ሰማይና የመ
ጀመሪያው ምድር አልፈዋልና። ባሕርም
ከእንግዲህ ወዲህ አይኖርም። 2 ቅድስቲቱ
ከተማ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ፥ ባልዋን ለመገ
ናኘት አሸብርቃ ብቅ እንደምትል ሙሽራ ፥
ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ
አየሁ።
3 ከዙፋኑም አንድ ታላቅ ድምፅ ፥ «ከእን
ግዲህ ወዲያ የእግዚአብሔር መኖሪያ በሰ
ዎች መካከል ይሆናል። እግዚአብሔር ከሰ
ዎች ጋር ይኖራል ፤ እነርሱም ሕዝቦቹ ይሆ
ናሉ ፤ እርሱም አምላካቸው ይሆናል። 4 ከዓ
ይኖቻቸው ላይ እንባቸውን ያብሳል። ከእን
ግዲህ ወዲያ ሞትም ፥ ኀዘንም ፥ ልቅሶም ፥ በሽ
ታም አይኖርም። ምክንያቱም በአሮጌው
ሥርዓት ውስጥ የነበሩት እነዚህ ሁሉ ነገ
ሮች ለዘላለም አልፈዋልና።»
5 በዙፋኑ ላይ የተቀመጠውም ፥ «እነሆ
እኔ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ» አለ። ቀጥ
ሎም እኔን እንዲህ አለኝ ፥ «ይህ የምነግርህ
ቃል የታመነና እውነት ስለሆነ ጻፍ።
6 አሁን ሁሉ ነገር ተፈጸመ። አልፋና
ኦሜጋ ፥ የሁሉም ነገር መጀመሪያና መጨ
ረሻ እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ
ምንጭ በነፃ አጠጣዋለሁ። 7 ድል የሚነሣ
እነዚህን ሁሉ ይወርሳል። እኔም አምላክ
እሆነዋለሁ ፤ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።
8 ነገር ግን የፈሪዎች ፥ የማያምኑ ፥ የርኩሶች ፥
የነፍሰ ገዳዮች ፥ የአመንዝራዎች ፥ የአስማተ
ኞች ፥ የጣዖት አምላኪዎችና የውሸተኞች
ሁሉ የመጨረሻ ዕድል ፥ በዲን በሚቃጠለው
የእሳት ባሕር ውስጥ መጣል ይሆናል። ሁለ
ተኛው ሞት ማለትም ይህ ነው።»
9 የመጨረሻዎቹን ሰባት መቅሰፍቶች

ከያዙት ጽዋ ውስጥ ካፈሰሱት ሰባት መላእ
ክት አንዱ ወደ እኔ ቀርቦ፥ «ወደዚህ ና፥
ሙሽራይቱን የበጉን ሚስት አሳይሃለሁ»
አለኝ። 10 በመንፈስም ወደ አንድ ከፍተኛ
ተራራ ወሰደኝ፥ቅድስቲቱን ከተማ ኢየሩሳ
ሌምን ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወ
ርድ አሳየኝ። 11 እርሷም የእግዚአብሔርን
ክብር ተሞልታ፥ «ኢያስጲድ» እንደ ተባ
ለው የከበረ ድንጋይ ታንጸባርቅና ታበራ
ነበር። 12 አሥራ ሁለት በሮች ያሉት ታላ
ቅና ረጅም የግንብ አጥር ነበራት። በአሥራ
ሁለቱም በሮች ላይ የአሥራ ሁለቱ የእሥራ
ኤል ነገዶች ስሞች ተጽፎባቸዋል። በአ
ሥራ ሁለቱም በሮች መላእክት ቆመው
ይጠብቃሉ። 13 የከተማይቱ አጥር በምሥ
ራቅ በኩል ሦስት፥በሰሜን በኩል ሦስት፥
በደቡብ በኩል ሦስት፥ በምዕራብ በኩል
ሦስት በሮች ነበሩት። 14 የከተማይቱ አጥር
በአሥራ ሁለት መሠረቶች ላይ የቆመ
ነበር። በአሥራ ሁለቱ መሠረቶችም ላይ፥
የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ስሞች ተጽ
ፎባቸዋል።

15 ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ
የከተማይቱን ዙሪያ፥በሮቿንና አጥሯን የሚ
ለካበት የወርቅ ዘንግ ነበረው። 16 ከተማይ
ቱም ርዝመትዋና ስፋትዋ እኩል የሆነ ባለ
አራት ማዕዘን ነበረች። እርሱም ከተማይቱን
በሚለካበት ጊዜ ርዝመትዋ ሁለት ሺህ
አራት መቶ አሥራ አራት ኪሎ ሜትር
ሆነ። ከፍታዋና ስፋትዋም ከርዝመትዋ ጋር
እኩል ነበር። 17 የግንቡም አጥር መልአኩ
በሚጠቀምበት በሰው መለኪያ ሰባ ሁለት
ሜትር ሆነ። 18 የግንቡ አጥር የተሠራው፥
«ኢያስጲድ» ከተባለው የከበረ ድንጋይ
ነበር። ከተማይቱም እንደ መስተዋት ከጠራ
ንጹሕ ወርቅ የተሠራች ነበረች። 19 የከተማ
ይቱ የግንብ አጥር መሠረት በሁሉ ዓይነት
የከበረ ድንጋይ ያጌጠ ነበር። የመጀመሪያው
መሠረት፥ «ኢያስጲድ» ከተባለ የከበረ ድን
ጋይ፥ሁለተኛው ከሰንፔር፥ሦስተኛው ከኬል
ቄዶን፥ አራተኛው ከመረግድ፥ 20 አምስተ
ኛው ከሰርዶንክስ፥ስድስተኛው ከሰርድዮን፥
ሰባተኛው ከክርስቲሎቤ፥ ስምንተኛው ከቢ
ረሌ፥ ዘጠነኛው ከወራውሬ፥አሥረኛው ከክ
ርስጵራስስ፥ አሥራ አንደኛው ከያክንት፥
አሥራ ሁለተኛው ከአሜቴስጢኖስ ነበር።
21 አሥራ ሁለቱም በሮች አሥራ ሁለት ዕን
ቁዎች ነበሩ። እያንዳንዱም በር ከአንድ
ዕንቁ የተሠራ ነበር። የከተማይቱ መንገድ
የተሠራው መስተዋት ከሚመስል ጥሩ
ወርቅ ነበር።

22 ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔርና በጉ
መቅደስዋ ስለሆኑ፥በከተማይቱ ውስጥ ቤተ
መቅደስ አይታይም። 23 የእግዚአብሔር
ክብር ከተማይቱን በብርሃን ስለሚሞላት
በጉም መብራትዋ ስለሆነ፥ የፀሐይ ወይም
የጨረቃ ብርሃን አያስፈልጋትም። 24 ብርሃን
ዋም ለሕዝቦች ሁሉ ያበራል። የምድርም
ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርስዋ ያመ
ጣሉ። 25 በዚያም «ሌሊት» የሚባል ነገር
የለም። የከተማይቱም በሮች ምን ጊዜም
አይዘጉም። 26 የሕዝቦች ግርማና ክብር ወደ
እርስዋ ይገባል። 27 ርኩስ የሆነ ምንም
ነገር አይገባባትም። አሳፋሪ ሥራ የሚፈ
ጽሙ፥ወይም ውሸተኞች ወደዚያች ከተማ
አይገቡም። ወደ ከተማይቱ መግባት የሚች
ሉት በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ውስጥ ስሞ
ቻቸው የተጻፉ ብቻ ናቸው።

## ምዕራፍ 22

1 ከዚህ በኋላ መልአኩ ከእግዚአብሔርና
ከበጉ ዙፋን የሚፈልቀውን እንደ መስተ
ዋት የጠራውን የሕይወት ውኃ ወንዝ አሳ
የኝ። 2 ወንዙ በከተማይቱ መካከል ሰንጥቆ
ያልፋል። በወንዙ ግራና ቀኝ በየወሩ አንድ
ዓይነት፥በዓመት ውስጥ አሥራ ሁለት የተለ
ያዩ ዓይነት ፍሬዎች፥የሚሰጥ የሕይወት
ዛፍ ተተክሏል። የዛፉም ቅጠል ሕዝቦችን
የሚፈውስ መድኃኒት ነበር።

3 ከተማይቱ ውስጥ ክፉ ነገር ዝር አይል
ባትም። የእግዚአብሔርና የበጉ ዙፋን በዚ
ህች ከተማ ውስጥ ይሆናል። አገልጋዮቹም
ያገለግሉታል። 4 ፊቱንም ያያሉ፤ ስሙም
በግምባራቸው ላይ ይጻፋል። 5 በዚያም
ሌሊት አይኖርም። እግዚአብሔር ብርሃና
ቸው ስለሚሆን መብራት ወይም የፀሐይ
ብርሃን አያስፈልጋቸውም። ለዘላለምም ይነ
ግሣሉ።

6 ከዚህ በኋላ መልአኩ እንዲህ አለኝ፥
«እነዚህ ቃሎች እውነትና የታመኑ
ናቸው። መንፈሱን ለነቢያት የሚሰጥ እግዚ
አብሔር፥በቅርቡ የሚሆነውን ነገር ለአገል
ጋዮቹ እንዲያሳይ መልአኩን ላከአል።»

7 ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላል፥ «እነሆ፥
በቅርብ ጊዜ ውስጥ እመጣለሁ። በዚህ
መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን የትንቢት
ቃሎች አምነው የሚጠብቁ የተባረኩ
ናቸው።»

8 ይህን ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ
ነኝ። መልአኩ ይህን ሁሉ ካሳየኝና ካሰማኝ

በኋላ ልሰግድለት ፈልጌ ከእግሩ ሥር ተደ
ፋሁ። 9 እርሱ ግን፣ «ተው፣ ተው! ለእኔ
እንዳትሰግድ! እኔ እንደ አንተና እንደ ወን
ድሞችህ እንደ ነቢያት፣ በዚህም መጽሐፍ
ውስጥ የተጻፈውን ቃል እንደሚጠብቁት
ሁሉ፣ እግዚአብሔርን የማገለግል ነኝ። ለእ
ግዚአብሔር ብቻ ስገድ» አለኝ።
10 ቀጥሎም እንደገና እንዲህ አለኝ፣
«ያሳየሁህ ነገር ሁሉ የሚፈጸምበት ዘመን
ደርሷል። ስለዚህ የዚህን መጽሐፍ የትን
ቢት ቃል ምሥጢር አድርገህ አትያዘው።
11 ኃጢአተኞች በኃጢአታቸው፣ ርኩሶችም
በርኩሰታቸው ይገፉበታል። በጎ ሥራ
ይሠሩ የነበሩ በጎ ሥራቸውን ይቀጥላሉ።
በቅድስና ይኖሩ የነበሩትም ቅድስናቸውን
ይጠብቃሉ።
12 እነሆ ጌታ ኢየሱስ እንዲህ ይላል፣
«በቅርብ ጊዜ እመጣለሁ፤ ለእያንዳንዱም
እንደ አገልግሎቱ መጠን የምሰጠውን ሽል
ማት ይዤአለሁ። 13 አልፋና ኦሜጋ፣ ፊተኛ
ውና ኋለኛው፣ የሁሉም ነገር መጀመሪያና
መጨረሻ እኔ ነኝ።
14 «ከሕይወት ዛፍ ፍሬዎች መብላት
እንዲችሉ በከተማይቱም በሮች እንዲገቡ፣
ልብሳቸውን አጥበው የተገኙ የተባረኩ
ናቸው። 15 ነገር ግን ርኩሶች፣ አስማተኞች፣
አመንዝራዎች፣ ነፍሰ ገዳዮች፣ ጣዖት አምላ
ኪዎች፣ ውሸተኞችና አጭበርባሪዎች ወደ
ከተማይቱ እንዲገቡ አይፈቀድላቸውም።
ስለዚህ በውጭ ይቀራሉ። 16 እነዚህን ነገ
ሮች ሁሉ እንዲነግራችሁ ወደ አብያተ ክር
ስቲያን መልአኬን የላክሁ እኔ ኢየሱስ
ነኝ። እኔ የዳዊት ሥርና ዝርያ ነኝ፣ የሚያበ
ራም የንጋት ኮከብ ነኝ።»
17 መንፈስ ቅዱስና ሙሽራይቱ «ና!»
ይላሉ። ይህንንም የሚሰማ ሁሉ፣ «ና»
ይበል። የተጠማም ሁሉ ይምጣ። የሚፈል
ግም ከሕይወት ውኃ በነፃ ይቅዳ።
18 እኔም ዮሐንስ በዚህ መጽሐፍ የተጻ
ፉትን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ የሚከ
ተለውን አስጠነቅቃለሁ። ማንም በእነዚህ
ቃሎች ላይ አንዳች ነገር ቢጨምር፣ እግዚአ
ብሔር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፉትን
መቅሰፍቶች ይጨምርበታል። 19 ማንም ከእ
ነዚህ የትንቢት ቃሎች አንድ ነገር ቢያጐ
ድል፣ እግዚአብሔር ያንን ሰው በዚህ መጽ
ሐፍ ውስጥ ከተገለጸው ከሕይወት ዛፍ ፍሬ
ከመብላትና ወደ ቅድስቲቱም ከተማ ከመግ
ባት ዕድሉን ያጐድልበታል።
20 እነዚህን ነገሮች ሁሉ የገለጸው፣
«አዎን፣ በቅርብ ጊዜ እመጣለሁ» ይላል።
አሜን፣ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ቶሎ ና!
21 የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከቅ
ዱሳኑ ሁሉ ጋር ይሁን፤ አሜን።